

# ምዕራፍ ፲፭

## የማይጨው ጦርነት

እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ምንም እንኳን ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን ወርዶ በምትኩ ደጃች ተፈሪ ሥልጣን እንዲይዙ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ቢያደርጉም አንድ የነጭ መንግሥት በአንድ የጥቁር መንግሥት በጦርነት መሸነፉ ያስደነገጣቸውና አፍሪካን ለመቀራመት ያዘጋጁትን ውጥን ያበላሸባቸው ስለመሰላቸው ቂማቸውን አልረሱም። በተለይ ጣሊያን ከአድዋ ድል በኋላ በደረሰባት ሃፍረት ቂም ይዛ ብድሯን ለመመለስ መዘጋጀት የጀመረችው ወዲያው የአድዋ ጦርነት እንደተፈጸመ ነበር። እንግሊዝና ፈረንሳይ በቅኝ ግዛታቸው የኢትዮጵያ አዋሳኝ ስለነበሩ ነገሩ በጣም እየቆረቆራቸው ሄዶ በኢትዮጵያ ባለሥልጣን ሹም ሽረት ሂደት ውስጥ በክሪያ መንገድ እጃቸው ቢኖርበትም አገሪቱ ነፃ የጥቁር አገር ሆና መታየቷ ሌሎች ጥቁሮችን "ይህም አለ ለካ!" ብለው እንዳይነሱባቸው ያሳስባቸው ነበር። ስለዚህም ኢትዮጵያ ባልተሳተፈችበት ድርድር ላይ ስለ ዓባይ ወንዝና ስለምድር ባቡር መዘርጋት ጉዳይ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ስምምነት አደረጉ።

የተፈሪ ሹመት ያስከተለው የውስጥ ጭቅጭቅና አለመግባባት የአገሪቱን የተባበረ ኃያል የቀነሰው መሆኑ ግልጽ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያንዳንዱን ግዛት በራሳቸው ሹሞች ማስተዳደር ሲጀምሩ የሕዝቡን አለመደሰት በመገንዘብ አገሪቱን በጦርነት ለመምታት ወቅቱ አመች መሆኑን ገመቱ። ቅኝ ገዥዎች በወንጌል መልዕክተኞችና በነጋዴዎች አማካይነት ሠላዮች በብዛት መላክ ጀመሩ። ጣሊያን በብዛት የጦር ኃይል መኮንኖቿዋን ለሥለላ ሥራ በወንጌል መልዕክተኞች ስም ላከች። በተጨማሪም በጎንደር፣ በደሴ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በነቀምት፣ በሐረርና አድዋ ላይ ቆንስላዎች አስቀምጣ መኳንንቶቹን ወዳጅ ለማድረግ ብዙ ስዎች አስማርታ ነበር።





ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (1928ዓ.ም.)

ቫቲካን ካስማራቻቸው የወንጌል መልዕክተኞች በተጨማሪ ለተለያዩ ሥራዎችም ከሚመጡት ስዎች መካከል ብዙ ሠላዮችም ነበሩ። ለምሳሌ በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ የቪክቶር ኤማኑኤል አጎት ዱክ ዳብሩዚ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ሲመጣ ለመታያ ለተፈሪ ለሰጠው ታንክ ነጅ የኾነው ሲኞር ዲ ማርቲን አማርኛ አቀላጥፎ የሚያውቅ ሲሆል 'ተፈሪ ይሙት!' ሲፎክር 'የጠቅል አሽከር!' እያለ በቤተ መንግሥት ውስጥ እንደልቡ እየገባና እየወጣ[13] ደህና አድርጎ ይሠልል ነበር።

ቅኝ ገዥዎቹ በኢትዮጵያ ወሰን አካባቢ ያሉ አስተዳዳሪዎችን በማግባባት ከገንዘብ ሌላ ጊሻን ሁሉ እየሸለሙ አገሪቱን ከዘመቻው በፊት ቦርቡረው ጨርሰው ነበር። መጨረሻ ላይ በአካባቢ ባሉ ቅኝ ግዛቶችዋ ላይ ጣሊያን ወታደር በብዛት አስቀምጣ ነገር መቆስቆስ ጀመረች።

ንጉሠ ነገሥቱ የዓለም ማኅበር አባል የኾነችው ኢትዮጵያ ተበደለች በማለት መልዕክተኛ እየላኩ አቤቱታቸውን ማቅረብ ጀመሩ። የማኅበሩ አባሎች እንግሊዝም ፈረንሳይም ጣሊያንን እንዳያስቀይሙና አኩርፋ ከጀርመን ጋር እንዳታብር ይጠነቀቁና የራሳቸውንም ጥቅም ያስጠብቁ ስለነበር ኢትዮጵያ ከማኅበሩ ፍትሕ አጣች። በዘመኑ ኃይለኛው የእንግሊዝ መንግሥት ሲሆን አሜሪካን ጭራሽ ማኅበርተኛም አልነበረችም። በዚህ ምክንያት የማኅበሩን ውሳኔ ሊላ የሚያስፈጽም አካል በወቅቱ ባለመኖሩ ለጣሊያን አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮ በማን አለብኝነት ጦርነት እንኳን ሳታውጅ ጣሊያን የኢትዮጵያን ድንበር በወልወል በኩል ገፍታ ገባች። አልፋ ተርፋም በሰሜን በኩል ድንበር ጥሳ አገር መያዝ ጀመረች።

---

[13] የሕይወቴ ማስታወሻ ከቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ

ከሁሉም የሚያስገርመው ደግሞ በዘመኑ የነበሩት በቫቲካን የካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ የኢጣሊያን ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ ለወረራ ሲዘምቱ፡ እንደመቃወም ዘማቹንም መድፉንም ባርከዋል። ምዕመናኑንም ለዚህ ለተቀደሰ ጦርነት ገንዘብ እንዲያዋጡ፣ ገንዘብ የሌላቸው ደግሞ የአንገታቸውን ሃብል፣ የጣት ቀለበታቸውን፣ የጆሮ ጉትቻቸውን እንዲሰጡ አድርገዋል። እውነተኛ የሃይማኖት አባት ቢሆኑ ኑሮ የሌላን ሰው አገር በግፍ ለመውረር የከጀለውን መንግሥት ማውገዝ በተገባቸው ነበር።



የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ቂም ይዞ እያለ በዘመናችን ያሉት ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ ጳውሎስ ሁለተኛ ዓለምን በሙሉ ሲጎበኙ ኢትዮጵያ ውስጥ ጉብኝት ለማድረግ ጠይቀው ሕዝብ ስላጉረመረመ ሳይሳካላቸው ቀርቷል። የአንድ ሰው ወንጀል ወደሌላ ባይተላለፍም ወንበሩ ላይ የተቀመጡት የዘመኑ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅና ቂሙን እንዲተው ማድረግ ይገባቸው ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የካቶሊክ ዕምነት ተከታዮች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ የቀረው የቫቲካን ቢሮክራሲ ከግራኝ ጦርነትእስከትሎ የተደጋገሙ ስህተቶች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ በማድረጉ ነው።

የማይቀረው ጦርነት መምጣቱ ግልጽ ሲሆን የኢትዮጵያ የጦር ኃይል ሊቋቋመው የማይችለው መሆኑ ታወቀ። አንድ ትልቅ ስብሰባ በቤተ መንግሥት ተደርጎ የጣሊያን ጦር ከፍተኛና ዘመናዊ ትጥቅ ያለው ስለሆነ ምን እናድርግ እየተባለ ሲወሳ የተሰብሳቢውን ሰው ዓይነ ውሃ የተመለከተ አንድ ተሳታፊ ተነስቶ "አቅምስ ባይኖረን ነፃነታችንን



ሳንዋጋ ልንሰጥ ነው ወይ!" ብሎ ስብሰባው መካከል ሽለላና ቀረርቶ አሰማ። የዚህን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ካባቸውን አጣፉና እንዘምታለን ብለው ስለቆረጡ ስብሰባው አበቃ። ወዲያው መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም የክተት አዋጅ ተነገረ።



የማይጨው ጦርነት አዋጅ ነጋሪት ሲጎሰም



ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል

በየአቅጣጫው የጦር አበጋዞች ተመድበው የጦርነትና የጉዞ ዝግጅት ተጀመረ። የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ስለዚህ ስብሰባ በጽሑፋቸው መካከል አያነሱም። ስለሆነም ስብሰባው ላይ የፎከረውን ሰው ስም ለማግኘት አዳጋች ሆኗል። ይሁንና የተከበሩ አቶ ከበደ እንግዳ ሰው "የምክር ቤታችን ዕድል ኃይለ ሥላሴ የጄኔቭ ቁልፍ" በሚል ርዕስ በ1953 ዓ.ም በታተመው መጽሐፋቸው ስለዚህ ስብሰባ ሲያትቱ፡ ".. ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጀግኖች

አሽከሮቻቸው ጋር የተመካከሩትን ቃል መሠረት አድርገው የከተት አዋጅ ባደረጉ ጊዜ…" ብለው ገጽ 27 ላይ አንስተውታል።

በሰሜን ዋናው የጦር ሚኒስትር ራስ ሙሉጌታ ይገዙ፣ በምሥራቅ ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል፣ በነገሌ ቦረና ራስ ደስታ ዳምጠው፣ በባሌ በኩል ደጃዝማች በየነ መርዕድ በአዝማችነት ሲሾሙ በእነሱ ውስጥም ብዙ የጦር መሪዎች ተደለደሉ። መቼም ዋናው የጦር መሪ ንጉሠ ነገሥቱ ቢሆኑም የጦር ሚኒስትሩ ሽማግሌውና ኋላ ቀሩ ራስ ሙሉጌታ ነበሩ። ልዑል ራስ ካሣም ሃይማኖተኛና ወግ አጥባቂ ስለነበሩ የራስ ሙሉጌታ ሥልጣን ወደ እሳቸው ቢዞርም ከሌሎቹ የጦር አበጋዞች በበለጠ አተኩረው ካርታ ይመልከቱ እንጂ በጦርነቱ ላይ እጅግም አልበረቱም። እንዲያውም ራስ ካሣ ተጠራጣሪ ስለነበሩ ከቤልጅግ አገር ተገዝቶ የመጣውን መሣሪያ ለወታደሩ እንዳይከፋፈል ከመጀመሪያው አውከው ነበር። ሃሳባቸው ወታደር መሣሪያውን ይዞ ተፈሪን ይከዳል ብለው በመጠርጠር ነው። ለዚህም ምክንያቱ ወታደሩ በወር የሚከፈለው ሦስት ማርትሬዛ ብር (ጠገራ ብር) ስለኾነና ቅሬታ ስለነበረው ነው። ወታደሮቹም

እንደራበኝና እንደሞረሞረኝ
ከጠገበው ጋራ ልሞት ነው መሰለኝ!

ብለው ዘመሩ ይባላል።


ደጃች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት

ጣሊያን በምሥራቅ በኩል አስቀድሞ ስላጠቃ ለጥብቀው በጀግንነት ይዋጉ የነበሩት ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት ተከበው ዕርዳታ እንዲላክላቸው ቢወተውቱም የሚደርስላቸው ሰላልተገኘ በውጊያው ተገደሉ። የግራዝማቹን መሞትና የቆራሂ መያዝን ሲሰሙ ንጉሠ ነገሥቱ በአይሮፕላን ወደ ጅጅጋ ከሄዱ በኋላ ሟቹን ደጃዝማች ብለው ሾመው ዘማቹን መክረውና ነገሮች አስተካክለው ተመለሱ። ወዲያው የሰሜኑ የጣሊያን ጦር እየገፋ መጥቶ መቀሌን ከመያዙም በላይ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ መክዳት ተሰማ። ንጉሠ ነገሥቱ ኅዳር 18 ቀን 1928 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ወደ ጠቅላይ ሠፈራቸው ደሴ ሄዱ። ደሴ እንደ ደረሱም ራስ ካሣን የጦር ሚኒስትር አድርገው ሾሙ።




ደጃች በየነ መርዕድ

ኢትዮጵያ በዘመናዊ ጦርነት የሠለጠነ በቂ የወታደር ኃይል አልነበራትም። ከአድዋ በኋላ የነበረው 600,000 ጠብመንጃ በእርስ በርስ ጦርነት ባክኖ ነበር። የተረፈውም ለዘመኑ ኋላ ቀር ስለኾነ እጅግም አስመኪ አልነበረም። አሮጌውና አዲሱ ተዳምሮ በጠቅላላው ኢትዮጵያ ውስጥ በማይጨው ጊዜ የነበረው ጠብመንጃ ብዛት በግምት 400,000 ብቻ ነበር። ፈረንሳይ በጅቡቲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ የነበረውን አንድ መርከብ ሙሉ የጦር መሣሪያ አላሳልፍም ብላ ከልክላ ጣሊያን አዲስ አበባ ሊገባ ሲል ስለለቀቀችው አዲስ አበባ ሲደርስ ጣሊያን ወስዶ እኛው ላይ ተጠቀመበት።

እንግሊዝም እንደዚሁ ኤደን ላይ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣውን መሣሪያ አግዶ ነበር። የጀርመን መንግሥት የጣሊያንን መንግሥት ወደ አክሲስ ኅብረት (ጀርመን ጃፓን ኅብረት) ውስጥ እንዲገባ ቢጋብዘው አሻፈረኝ በማለቱ በዚሁ ተናዶ በቤልጅክ አማካይነት የጦር መሣሪያ ኢትዮጵያ እንዲደርሳት አደረገ ነበር። በዚህም ውለታ የተነሳ ንጉሠ ነገሥቱ በንግግራቸው መካከል የናዚን መንግሥት ተችተው አያውቁም። እንዲያውም ለዚህ ውለታ አንዳንድ የናዚ መኰንኖች ኢትዮጵያ ውስጥ እየሾለኩ ገብተው መደበቂያ ሆኗቸው ነበር። አንድ የታወቀ የጀርመን ናዚ ኮሎኔል ዶክተር ባቦር እሥራኤሎች በሰላ ደርሰውበት ሊይዙት ሲያደቡ አምልጦ አዋሽ ወንዝ በመኪናው ገብቶ ራሱን ገደለ። ሌሎችም የንጉሠ ነገሥቱ የክርስትና ልጅ ኮሎኔል ዶክተር በቀለ ኃይለ ሥላሴ የሚባለው ጀርመናዊና እነ ኢንጅነር ሃን የመሳሰሉ በአገር ውስጥ ነበሩ።

ዘማቹ የኢትዮጵያ ሠራዊት የአይሮፕላን ጦርነት ምን ያህል ጉዳት እንደሚያደርስ ግንዛቤው አልነበረውም። የእጅ ቦንብ እንኳን የሚሰጠው ጠቀሜታና የሚያመጣው ጉዳት እጅግም አይታወቅም ነበር። የስንቁም አከፋፈልና የጦር ዝግጅቱ በጣም ኋላ ቀር በመሆኑ የኢትዮጵያ ዘማች

የራሱን ስንቅ እየበላ ተዋግቶ ሲመለስ ባሊያን በመንግሥት በኩል የተከማቸውን በአይሮፕላን አቃጠለው። በተረፈ ግን ወታደሩ በጦርነቱ ያሳየውን ቆራጥነትና ውግያ በማድነቅ ባሊያን በአይሮፕላን ባይታገዝ ኖሮ ጳግመኛ ድል ለኢትዮጵያ እንደሚሆን ባሊያኖቹ ራሳቸው በኋላ ገልጸውታል።


በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ በኩል የጦር መሪ አሿሿም ላይ ስህተት ነበር። አፄ ምኒልክ ለጦር አበጋዝነት ሹመት የሚመርጡት የጨዋ ልጅ የሚባሉትን ነበር። ጨዋ ማለት በኀብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቅ፣ በትምሕርት ያልዘለቀ፣ ማንበብና መጻፍ ከዚያ ሌላ የጸሎት መጽሐፍ መመልከት የሚችል እንጂ በትምሕርት የተራቀቀውንማ ተማሪ ነበር የሚሉት። ተማሪንም ፈሪ፣ ወላዋይ፣ ከዳተኛ፣ አድርገው ነበር የሚቆጥሩት። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ጦረኛውን ራስ ሙሉጌታን ከጦር ሚኒስትርነት ሽረው ወግ አጥባቂውንና ቄሱን ራስ ካሣን የማይገባቸውን ሥልጣን ሰለሰጡ ዘማቹ ራስ ሙሉጌታን ትቶ ወደ ራስ ካሣ ስለዞረ ራስ ሙሉጌታ አቅም አንሷቸው በጠላት ሳይሆን በወገኖቻቸው በራያና አዘቦ ተከበው ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተገደሉ። ራያና አዘቦ ከአድዋ መልስ በገዛ ወገኑ ላይ የተኮሰ ከመሆኑም በላይ ከማይጨውም መልስ ከባሊያን ጋረ ተመሳጥሮ ገንዘብ በመቀበል ተመሳሳይ ጉዳት አድርሷል።

የዘመናዊ አስተሳሰብና የጦር ትምሕርት የቀሰሙትን መሾም ሲገባቸው ንጉሠ ነገሥቱ ለራሳቸው ሥልጣን የሚታመን ብቻ ሲሾሙ ነገር አበላሹ። መጀመሪያውኑ ራስ ሙሉጌታ ምንም እንኳን ጦረኛ ቢሆኑም የተሾሙ ዕለት ቤተ መንግሥት ውስጥ ያገኟቸው ደጃች ባልቻ “ለመሆኑ አንተስ ሹመቱን ተቀበልክ?” ብለው በመገረም ጠይቀዋቸው ነበር ይባላል። ይኸ የሚያሳየው ለግዳጁ ይበልጥ የሚጠቅሙ እያሉ ራስ ሙሉጌታ ለንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን በመታመናቸው ብቻ እንደተሾሙ ነው።

ራስ ደስታና ደጃች በየነ መርዕድ የጃንሆይ የሴት ልጆች ባሎች ናቸው። ራስ ደስታ የጀግኖች አስኳል ዘር ሆነው የረባ ጦርነት ሳያደርጉ ወዲያውኑ ድል ተመቱ። መጨረሻም ላይ አጥብቆ እንደ መዋጋት ሲወላውሉ ቆይተው ወደ እናታቸው ትውልድ አገር ገብተው ከተደበቁበት ተይዘው ከራስ ካሣ ሁለት ልጆች ጋር ተገደሉ።



እንደዚሁም ደጃዝማች በየነ መርዕድ ከገቡላቸው የኤርትራ ወታደሮች ጋር ኾነው ውጊያ ላይ ተማርከው ተገደሉ። ባለቤታቸው ልዕልት ሮማነ ወርቅም ተማርከው ባሊያን አገር ተወሰዱና እዚያው በእስር እንዳሉ ሞቱ።



የክብር ዘበኛ የሙዚቃ ባንድ ከባሊያን ወረራ በፊት ሁለት ሜትር ከሰማኒያ ርዝመት ባለው ዱላ አሸከርካሪ እየተመራ (የቢኒሻንጉል ተወላጅ በኋላ ባሊያን የገደለው)

ራስ ካሣ ለንጉሠ ነገሥቱ በእናታቸው በኩል የአክስታቸው የወይዘሮ ትሰሜ ዳርጌ ልጅ ናቸው። በአባታቸውም በኩል የአባታቸው አጎት የራስ ዳርጌ የልጅ ልጅ ናቸው። ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤልም በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን ተፈሪን ንጉሥ እንዲሆኑ ውስጥ ውስጡን አድማ የመቱ ለንጉሡ ታማኝ ይሁኑ እንጂ ጦሩ የማይታዘዛቸው በአዝማችነት የማይታወቁ ሰው ነበሩ። ጃንሆይ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ ደጃዝማች ነሲቡ በሥራቸው ያለው ጦር ሳይሰማ ከጥቂት አዝማቾች ጋር ሹልክ ብለው ጅቡቲ ድረስ ሄዱና አብረው ተሰደዱ። እንደእውነቱ ድሉ የኢትዮጵያ ቢሆንና በስደት ላይ ባይሞቱ ኖሮ ለጦር ፍርድ ቤት

የሚያስቀርብ ስህተቶችም ሠርተው ነበር[14]። ባጭሩ የንጉሠ ነገሥቱ ካድሬ እንጂ ለዘመቻ ኃላፊነት የማይበቁ ሰው ነበሩ። ሆኖም ወጣትና ምሁር ስለነበሩ በኤርትራ የኢትዮጵያ ቆንሲል ጄኔራል፣ የማዕከል መካሪ ማኅበር መሪ፣ በአዲስ አበባ ከንቲባነትና የሐረር ገዥ በመሆን በወጣትነት ዕድሜያቸው ብዙ አገልግለዋል።

ወሎ በልጅ ኢያሱ መሻርና በንጉሥ ሚካኤል ተሸንፎ መማረክ፣ ጎንደር በራስ ጉግሳ መገደልና በደጃች አያሌው ብሩ አለመሾም፣ ጎጃም በራስ ኃይሉ መጋዝ፣ በሸዋም ጥቂት መኳንንቶች በአቤቶ ኢያሱ መሻር ስላኮረፉ፣ በአፋርና በሶማሌ ባላባቶች ዘንድ በአቤቶ ኢያሱ ከሥልጣን መወገድ ቅሬታ ስለነበረባቸው ለጦርነቱ ቢሠለፉም በሙሉ ልብ አልነበረም። የጎጃም ጦር በከፊል ሳይዋጋ ተመለሰ። አፋር ጭራሹኑ ሳይዘምት ቀረ። በወሎ በኩል ያለው ቆለኛ ከማይጨው የሚመለሰውን ዘማች ፈጀው። ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱም የተመለሱት በላሊበላና በመርሐቤቴ በኩል ነው።

በጣሊያኖቹ በኩል በቂ ዝግጅት አድርገው ስለነበረ የማሸነፍ ዕድሉ የእነሱ እንደሚሆን አስቀድመው አውቀውታል። በአድዋ ጦርነት የተሸነፉት በወታደር ማነስ ምክንያት መሆኑን በመገንዘብ ማይጨው ጦርነት ላይ በተሰላፊ ብዛት እነሱ ይበልጡ ነበር። ሙሶሎኒ "ወታደር አንሶ ከምሸነፍ ከድል በኋላ ወታደር አብዝተህ ነበር ተብዬ ብወቀስ ይሻለኛል" ብሎ ተናግሯል። ኢትዮጵያ የትራንስፖርት ሥራ ብቻ የሚሠሩ 12 ትንንሽ አይሮፕላኖች ስታሠልፍ ጣሊያን ግን በሰሜን ግንባር ብቻ 300 ያህል በምሥራቅ ደግሞ 150 የጦር አይሮፕላን አሠማርቷል። እ.ኤ.አ በ1935 ዓ.ም ጣሊያንና ኢትዮጵያ የመርዝ ጭስ እንደማይጠቀሙ የተዋዋሉትን ስምምነት ጥሶ ይህንኑ የመርዝ ጭስ በሕዝብ ላይ በመርጨት የሰውን ልጅ እንደ ትንኝ በመፍጀቱ ይቅርታ የማይደረግለት የጠላትነት ተግባር ፈጽሟል። ይኸም አሜሪካ ጃፓንን ማሸነፍ ሲያቅታት ሂሮሽማና ናጋሳኪ የጃፓን ከተሞች ላይ የሰፈረውን ጦር ለመፍጀት ከጣለቻቸው ሁለት የአቶሚክ ቦንቦች ባይወዳደርም ጭካኔው ግን አይተናነስም። ይኸንንም የምንልበት ምክንያት ኢትዮጵያውያን የታጠቁትንና ጠላት የታጠቀውን የመሣሪያ ዓይነት በማወዳደር ነው።

[14] የታሪክ ማስታወሻ ከደጃ ከበደ ተሰማ



ንጉሠ ነገሥቱ ደሴ ደርሰው ስምንት ቀን ከቆዩ በኋላ የጣሊያን አይሮፕላኖች እየመጡ ቦንብ እየጣሉ መሄድ ጀመሩ። ንጉሠ ነገሥቱም የአይሮፕላን መጣያ ቢተኩሱም ከአይሮፕላኖቹ ርቀት የተነሳ እጅግም ጉዳት ሊያደርሱባቸው አልቻሉም።



ጃንሆይ ደሴ ላይ ሆነው የአይሮፕላን መጣያ (ኦርሊኮን) ሲተኩሱ

ራስ ሙሉጌታ የቀዳሚ ጦር አበጋዝ እንጂ እንደ ጦር ሚኒስትርነት ኃላፊነታቸውን አልተወጡም። ካርታ እንኳን ሲያቀርቡላቸው "ይህንን መመልከት የሚወድ ራስ ካሣ ነው፤ እኔን ተውኝ" በማለት ለጦሩ ተገቢውን አመራር መስጠት አልቻሉም። እርግጥ በዘመኑበት መስመር ጀግንነታቸው የታወቀ ጦረኛ ነበሩ።

ራስ ሙሉጌታ ወታደሩን "ሌሊት እንዲጓዝ ያድርጉ፤ በቀን የሚደረገው እንቅስቃሴ ለጣሊያን ምቹ በመሆኑ ዘማቹን በአይሮፕላን ይደበድበዋል" ቢሏቸው "እኔ ሙሉጌታ! ፈርቼ ነው ሌሊት እንደ ጅብ የምሄደው?" ብለው በቀን መጓዙን ስለመረጡ ብዙ ዘማች አስፈጁ። ንጉሡም በሬድዮን መልዕክት ሲያስተላልፉ ጣሊያን መልዕክቱን እየጠለፈና እያስተረጎመ

አስቀድሞ ዝግጅት እያደረገ ዘማቹን ፈጀው። ይህ ሁሉ ሲሆን በኢትዮጵያ የጦር መሪዎች በኩል መልዕክቱ መጠለፉ እንኳ[n] አይታወቅም ነበር።



የማይጨው ዘማቾች ጃገማና ጢንቂሳ ኬሎ



የራስ እምሩ ጦር ብቻ በዘዴ ለመርዝ መርጨት የማይመች ቦታ ላይ ሰፍሮ የመርዝ ጭሱንም ነጠላውን እየቀደደና ውኃ እየነከረ አፍንጫው ላይ በማድረግ ራሱን ተከላከለ። ሆኖም ግሚሱ የጎጃም ጦር ትቷቸው በመመለሱና ደጃች አያሌውም ስለለገሙባቸው በጦራቸው መሳሳት ቢቸገሩም በሥርዓት የተዋጉና ተመልሰው ጎጃም እስኪገቡ ጦራቸው ያልተፍረከረከ የራስ እምሩ ጦር ብቻ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱም ከደሴ ተነስተው ወደ ማይጨው ሄደው የጦር አለቆቻቸውን ገና አልተዘጋጀንም እያሉ ጦርነት የሚደረግበት ጊዜ በጣም ተራዘመ። በዚህን ወቅት ጣሊያን በየዛቸው ቦታዎች ላይ ምሽጉን ይሠራ ስለነበረ ራስ ደምሰው ነሲቡ "እንዴት ምሽጉን ሲሠራ ቁጭ ብለን እናያለን? በኋላ ምሽጉ ውስጥ ሆኖ ጉዳት ያደርስብናል" እያሉ ቢጮሁ ሰሚ በማጣታቸው ወታደሮቻቸውን ይዘው በራሳቸው ውሳኔ አደጋ ሲያደርሱ በዚያው ሞቱ። በወቅቱ አዝማቾች እርስ በርሳቸውም መልዕክት ለመላላክ አይፈቀድላቸውም ነበር። ማንኛውም መልዕክት በራስ ካሣ በኩል ለጃንሆይ ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ መገናኘት እንዲችሉ ስለተደረገ ብዙ አዝማቾች ትዕግስታቸው እያለቀ ጠላት ላይ አደጋ መጣል ሲጀምሩ ራስ ካሣ በበኩላቸው ዝግጅቱ ሳይጠናቀቅ ለምን ጦርነት ትጀምራላችሁ በማለት ዳግመኛ ጥቃት እንዳይከፍቱ ዋስ ያስጠሩ ጀመር። ይኸ ሁሉ ሁኔታ ለጣሊያኖቹ ዝግጅት ጊዜ ሰጣቸው።

ጦርነቱ ማይጨው ላይ መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ለአንድ ቀን ከተደረገ በኋላ በማግስቱ ጃንሆይ የማፈግፈግ ትዕዛዝ ሰጡ። ወታደሩም የንጉሠ ነገሥቱን መመለስ ሲሰማ ጥቃት በዝቶበት ስለነበረ ወዲያውኑ አፈገፈገ። ዘማቹን እንደገና አስቁሞ ለጦርነት ማብቃት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ሲመለሱ አዘቦና ራያ ወታደሩን መፍጀት ጀምሮ ጦርነቱ ከጠላት ጋር መሆኑ ቀርቶ እርስ በርስ ሆነ። ይኸ ሁሉ ሲሆን የአልጋ ወራሽ ጦር የተባለው ከደሴ እንኳን ሳይነሳና ሳይዋጋ ተመለሰ። ንጉሠ ነገሥቱም ከደሴ በላሊበላ በኩል ስለተጓዙ ወታደሩ ንጉሠ ነገሥቱ ጠፍተውበት ጠብቆ ተበታተነ። ጃንሆይ ቤተ ክርስቲያን እየሳሙ ወታደሩ ተበታትኖ ብዙ ጊዜ ከባከነ በኋላ ጃማ ሲደርሱ ያሉበት ስለታወቀ ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ለእቴጌ ይኸንኑ ሁኔታ ስለተናገሩ ያሉበት ታወቀ። በወራቸው በመርሐ ቤቴና በዜጋመል በኩል ፍቼ ራስ ካሣ ቤት አርፈው ሌሊቱን


ብላታ ታከለ ወልደ ሃዋርያት

በመኪና ተጉዘው ሚያዝያ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ጧት ላይ አዲስ አበባ እንደገቡ ስብሰባዎች ተደርገው ንጉሡ ሚያዝያ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ማታ በባቡር ተሳፍረው ጅቡቲ ከደረሱ በኋላ በዚያ አስቀድማ ትጠብቅ በነበረች መርከብ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዙ። የንጉሠ ነገሥቱን ስደት በተመለከተ ደህና ተደርጎ የተገለጸው ቄሳርና አብዮት በሚለው በስደተኛው አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ በእጅ ጽሑፍ በተጻፈው መጽሐፍ ላይ ስለኾነ አንኳር አንኳሩን ከዚህ በታች እጠቅሳለሁ።

"በዚህ ስብሰባ ሁለት ዓይነት ሃሳቦች ቀርበው በአንክሮ ተነጋገሩባቸው። የመጀመሪያው ሃሳብ ከብላታ ታከለ የቀረበው የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና የጦር ሠፈርና የአስተዳደር ከተማ በፍጥነት ወደ ጎሬ ይዛወርና ንጉሠ ነገሥቱ የመሪነት ተግባራቸውን ለመወጣት ወደ ጎሬ ከተማ ከተሸጉ በኋላ በተለያዩ ጀግኖች መሪነት በየአውራጃዎች የአርበኝነት ውጊያ እንዲቀጥል ይደረጋል። ጎሬ ከእንግሊዝ ቅኝ አገር ድንበርተኛ ስለኾነ በዕርዳታም ኾነ በግዥ መሣሪያ ማግኘት ይቻላል። ብላታ ታከለ ይህን ሃሳብ መሠረት በማድረግ አፄ ኃይለ ሥላሴ ገና አዲስ አበባ ከመድረሳቸው በፊት በጃንሜዳ ታላቅ ንግግር አድርገው ነበር። ወደ ዋናው ከተማ እየገፋ የመጣውን የጠላት ጦር ጣርማ በር ላይ አግዶ ውጊያ ለመጀመር የተሰናዱ መሆናቸውን አስታወቁ። ይህንን የሚቃወም ሃሳብ መኖሩን ስምተው ያለልክ ተቆጥተው ነበርና 'ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ለመሄድ ቢሞክሩ የእኔ እስረኛ ይሆናሉ!' ብለው ዛቱ።"

"ሁለተኛው ሃሳብ በአንዳንድ የውጭ እንደራሴዎች የቀረበላቸውን ምክር መሠረት በማድረግ አቶ መኮንን ሃብተ ወልድ ንጉሡ ደጃች ወልደ ጻድቅ ጎሹን የጎሬ ቤተ መንግሥት እንደራሴ አድርገው እሳቸው በፍጥነት ወደ



አውሮፓ ሄደው ለዓለም መንግሥታት ያመልክቱና እርዳታ ይጠይቁ የሚል ነበር።"

በመጀመሪያ ቀን በብላታ ታከለ ሃሳብ ላይ እንዴት አድርጎ ጠላትን መውጋት ይሻላል ተብሎ አብዛኛው ሰው በየቦታው ጠላት ላይ አደጋ እየጣለ ማዳከምና በመጨረሻ ማሸነፍ ወደሚለው ሲያደላ መሽቶ ነበርና ለማግስቱ ማታ አሥራ አንድ ሰዓት ተቀጥሮ ስብሰባው ተበተነ።

በማግስቱ ስብሰባው ሲጀመር የመጀመሪያው ሃሳብ ወደጎን ይቀርና ጃንሆይ ወደ ዓለም መንግሥታት ተጉዘው አቤቱታ እንዲያሰሙ የሚለው ሃሳብ ቀርቦ ውዝግቡ ተፋፋመ። ለዚህም ክርክር ትልቅ አስተዋፅዖ ያደረጉት ራስ ካሣ ነበሩ። በመጨረሻ ላይ የመንግሥቱ ርዕሰ ከተማ ወደ ጎሬ ተዛውሮ ትግሉ ይቀጥል። ደጃች ወልደ ጻድቅ እንደራሴ ራስ እምሩ የጦር ሚኒስትር ኾነው ንጉሠ ነገሥቱ ግን ለዓለም መንግሥታት ሄደው ያመልክቱ የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ። አስቀድሞ ከስብሰባ ውጭ የተሠራ የውስጥ ምክር ስለነበረ እንደምንም ስብሰባው ተዘጋና ማታውኑ ንጉሠ ነገሥቱ ከጥቂት መኳንንቶች፣ ልዑላን ቤተሰቦችና ታማኝ አሽከሮቻቸውና ጥቂት የዲፕሎማቲክ ሰዎች ጋር በባቡር ወደ ጅቡቲ ሄደው ሚያዝያ 25 ቀን እቴጌንና ልጆቻቸውን ወደ ኢየሩሣሌም እንድትወስድ አስቀድማ ትጠብቅ በነበረችው ኢንተርፕራይዝ በምትባል የጦር መርከብ ተሳፍረው ጉዞ ጀመሩ። ጣሊያኖች ንጉሠ ነገሥቱ የሚሄዱበትን ባቡር በአይሮፕላን ለመደብደብ ፈልገው እንግሊዝ ስላልተስማማች በሠላም አሳልፈዋቸዋል።

ሁለተኛው ሃሳብ በውጭ አገር ሌጋሲዮኖች ኢትዮጵያ ቶሎ እጅ እንድትሰጥ የተጎነጎነ ምክር ቢሆንም ብዙ ሰው ቅር እያለው ውሳኔ ተደርጎበት ንጉሠ ነገሥቱ ከአጃቢዎቻቸው ጋር ሚያዝያ 23 ቀን ማታ በአምስት ሰዓት አቃቂ በባቡር ጣቢያ ላይ ከተሳፈሩ በኋላ መንገድ ጀመሩ። ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሃዋርያት ከራስ አበበ ጋር አቃቂ ሄደው ንጉሠ ነገሥቱ መሄዳቸውን ሲሰሙ ተዝለፍልፈው ወደቁ። ከተነሱም በኋላ "አገሩን ለማን ጥሎ ሸሸ!" እያሉ በንዴት እየተበሳጩ ተመለሱ። የክብር ዘበኞችም በነገሩ አዝነው የሚከተለውን ገጠሙ።

አንቺም ሂጂ ሂጂ ወደ ፈረንጆቹ
ለኛም እጊዜር አለ ለክብር ዘበኞቹ!

ንጉሠ ነገሥቱ ሐረርጌ ሚኤሶ ሲደርሱ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋሪያት ከነሠራዊታቸው ንጉሠ ነገሥቱን ሲቀበሏቸው በመሄዳቸው ቅር

መሰኘታቸው ታወቀ። ጃንሆይ ድሬ ዳዋን አልፈው ባቡሩን ያስቆሙና ከታሰሩበት ይዘዋቸው ለሄዱት ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ለራስ ገብረ ሕይወት ሚካኤልና ለሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች ምሕረት አድርገው ጉዞ ሲጀመሩ ደጃዝማች አባ ውቃውን ግን በእስር ላይ እንዳሉ ትተዋቸው ሄዱ።

በባቡሩ የተለየ ፉርጎ ውስጥ አንድ ቢዩክና ክራይዝለር በጠቅላላው አራት መኪናዎች በሌላ ፉርጎ ደግሞ የተለያዩ ሻንጣዎች ነበሩ። በሌሎች ፍርጎዎችም በርካታ ሰዎች ተሳፍረው ስለነበረ እንደገና ባቡሩን አስቁመው ምንም ከተማ በሌለበት በርሃ ብዙ ሰዎች እንዲወርዱ ተደረገ። የፈረንሳይ ሶማሌ ወሰን ከመድረሳቸውም በፊት የፈረንሳይ መንግሥት የጦር መኅሪያ የያዘ ሰው ግዛቴ አይገባም ስላለች አሥራ አምስት የንጉሠ ነገሥቱ ጠባቂ የክብር ዘበኞች አለመኅሪያችን "እንጠቅምዎትምና ይፍቀዱልን እንውረድና ለነፃነታችን እንታገል" ብለው ስለጠየቁ ተፈቅዶላቸው ወረዱ[15]።

ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ በሄዱ በሦስተኛው ቀን የጣሊያን ወታደር በጦር አዛዡ ጄኔራል ባዶሊዮ እየተመራ በየካ በኩል አዲስ አበባ ገባ። በዚህ ዕለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በመሠለፍ ልክ ጄኔራል ዲ ቦኖ አድዋ ሲገባ እንዳደረጉት ለጄኔራል ባዶሊዮም የክብር አቀባበል አደረጉለት።

ሙሶሊኒ ኢትዮጵያ በኢጣልያ የጦር ኃይል በመያዝዋ ሁለተኛው የሮም የንጉሠ ነገሥት መንግሥት (የሮማን ኤምፓየር) መመሥረቱን እ.አ.አ. ግንቦት 5 ቀን 1935 ዓ.ም ለዓለም አስታውቆ አዲሱን መንግሥት የሚያናውጥ ኃይል በምድር ላይ ሊኖር አይችልም ብሎ በታላቅ ትዕቢት ተናገረ።

የኾነው ኾኖ ብዙ አደጋ እየተጣለ ጠላትን ማስቸገርና ለውድቀትም ማድረስ ሲቻል በንጉሠ ነገሥቱ የጥድፊያ ስደት ምክንያት ብዙ ሰዎች እጃቸውን እየሰጡ ወደ ግል ኑሮ መሠማራት ጀመሩ። የምሥራቁ ጦር ወደ በርበራ ሶማሌና ወደ ኬኒያ ተሰደደ። የሰሜኑም ተበታትኖ የሞተው ሞቶ የተረፈው ወደየትውልድ አገሩ ገባ። ንጉሠ ነገሥቱ ዋና የጦሩ አዛዥ ኾነው ውጊያውን እንደመምራት ራሳቸው ለመሄድ የተሽቀዳደሙበት

[15] ጥርስ የገባች አገር ኢትዮጵያ በጆን ሐዛወይ ስፔንሰር ገጽ 95-97



ሁኔታ ብዙ ጠላቶችን እንዲያፈሩበት አደረገ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንጉሡ እንዲህ ያለ ነገር አልጠበቀም ነበር። በጦሩ ውስጥ ዋና አቀንቃኝ ሆነው የነበሩት ራስ ካሣም አብረው መሄዳቸው የሚያስገርም ነበር። እነራስ ካሣና ራስ እደፍርሰው የውጭ አገር ትምሕርት ስላልነበራቸው ሽሽት እንጂ ለዲፕሎማሲው የሚያበረክቱት ጠቀሜታ አልነበራቸውም።

የማይችሉት ጠላት ሲመጣ ቢዋጉ ትርፉ ሞት ብቻ ውጤቱም ጎጂ ይሆን ነበር የሚሉም ቢኖሩ ያለው አከራካሪ ነጥብ ንጉሡ በቂ ውጊያ አላደረጉም የሚል ነው። በእሳቸው የተፋጠነ አካሄድ ምክንያት ሲዋጉ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ ቶሎ እጅ ሰጡ። ያልሰጡትም ቢሆኑ ተስፋ ስለቆረጡ አጥብቀው አልተዋጉም የሚል ቅሬታ በሕዝቡ ዘንድ ሰፍኗል። ሌላው በኢትዮጵያ የተለመደው ሁኔታ ንጉሡ አጥብቆ ተዋግቶ ይሞታል እንጂ ሸሽቶ አይሰወርም የሚል ነው። ስለኾነም መጀመሪያ የተቻላቸውን ያህል ተዋግተው ከዚያ በኋላ ሾልከው በስደት ቢሄዱ ያስመሰግናቸዋል እንጂ አያስወቅሳቸውም ነበር የሚል አስተያየትም አለ። አፄ ቴዎድሮስ ለክብራችን ራሳቸውን ማጥፋታቸው፣ አፄ ዮሐንስ በጦርነት መሠዋታቸው፣ አፄ ምኒልክ ጠላታቸውን ብትንትኑን ማውጣታቸው፣ የሚያኮራውን ያህል በአንጻሩ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መሰደድና የኮሎኔል መንግሥቱ መፈርጠጥ ለኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ አሳፋሪ ነጥብ ነው። ይሁንና ለአገሪቱ አንድነት አስተባባሪ ሲሆን የቻለ አንድ ንጉሥ በሕይወት መኖሩ መጨረሻ ላይ ጠቅሟል። በሌላ በኩል ንጉሡ ነገሥቱ በጦርነቱ ላይ ሞተው ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በቅኝ ተገዥነትም ልትመደብ ትችል ነበር።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን የንጉሡ ወታደሮች ግራኝ አህመድ ኢብን ኢብራሒምን በጦርነት ማሸነፍ ባቃታቸው ጊዜ እያደቡ አደጋ በመጣል አዳክመው በመጨረሻ በተደረገው ጦርነት አሸነፉ። እንደሚባለው የጥሬ ሥጋ መብላት የተጀመረው ያዚያን ጊዜ ነው። ይኸም ጠላት ከርቀት ጭስ አይቶ መጥቶ እንዳያጠቃ የታረደውን ከብት ሥጋውን ሳይጠብሱ መብላት ስለጀመሩ ነው ይባላል። ስለዚህ የሽምቅ ጦርነት ኢትዮጵያ ውስጥ ድል ያስገኘ መሆኑን ከታሪክ የተገነዘበው የቻይናው አብዮት መሪ ማኦ ሴ ቱንግ እንኳን "እንደ ሃበሾች ተባበሩና ተዋጉ" ብሎ ወታደሮቹን ይመክር ነበር።



አራዳ ጊዮርጊስ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ በአንድነት ሲጸልይ

ሌላው ቀርቶ ጣሊያን አገር ታስረው የነበሩ ኢትዮጵያውያንን የኢጣሊያን ነፃ አውጭዎች እየፈለጉ ከእነሱ አንዳንድ ሁኔታን ይማሩ እንደነበረ እስረኞቹ አገራቸው ሲመለሱ ተናግረዋል። አብዲሳ አጋ የጣሊያን አርበኞችን እየመሩ ሮማ የገቡት አገራቸው ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ብዙ ታዋቂነት አላገኙም። ይኸም ብቻ ሳይሆን ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ እስረኞች ብዙ ነገር ተምረዋል። አዚናራ በምትባል ደሴት የታሰሩት ኢትዮጵያውያን ሥጋ ለመግዛት አቅም ስላልነበራቸው የሚገዙት ጣሊያኖቹ የማይበሉትንና ርካሽ የነበረውን ጨጓራ ነበር። ጣሊያኖች ጨጓራ የሚበላ መሆኑን ተመልክተው ስለነበረ አሁን ተለማምደውት ትሪፓ እያሉ ይበሉታል።





# ምዕራፍ ፲፱

## ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ዘመን

ሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ከጅቡቲ ወደ እሥራኤል አገር በመሄድ ኢየሩሣሌም አራት ሳምንት ከሰነበቱ በኋላ እቴጌንና በከፊል አጃቢዎቻቸውን ትተው እስከ ጅብራልታር ድረስ በብሪታንያ የጦር መርከብ፣ ከዚያም በንግድ መርከብ ኾነው ግንቦት 26 ቀን እንግሊዝ አገር ሳውዝ ሃምፕተን ወደብ ገቡ። እንግሊዝ አገር ሲደርሱ የብሪታኒያ መንግሥት አስቀድሞም ኢትዮጵያን ለጣሊያን መንግሥት አሳልፎ የሰጠ ስለነበረ አንድም የመንግሥት ባለሥልጣን እንዲቀበላቸው አላደረገም። የእንግሊዝ ሕዝብ ግን ከመርከብ ኾነ ከባቡር ሲወርዱ በእግርም ወዲያ ወዲህ ሲዘዋወሩ ሁሉ በጋለ ስሜት አቀባበል ያደርግላቸው ነበር።
ባዝ በሚባል ከተማ ፌርፊልድ መንገድ ዳር ንጉሠ ነገሥቱ አንድ ቤት ገዝተው የስደት ኑሮ ጀመሩ። ከዓመት በኋላ በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም በፈረንሳይ አገር አቋርጠው በባቡር ወደ ጄኔቭ ተጉዘው በሊግ ኦፍ ኔሽን ስብሰባ ላይ ተገኝተው ታሪካዊ ንግግር አደረጉ። ንግግራቸውን ሲጀምሩ ጣልያኖች በፉጨት አላሰማ ብለው በማወካቸው ከስብሰባው አዳራሽ ተባርረው ጃንሆይ ግን ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ተደረገ።

ፈረንጆች መጥቀስ አይፈልጉም እንጂ ጃንሆይ በንግግራቸው መካከል ታላቅ መልዕክት ሰንዝረው ነበር። እሱም "እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ኾነው ይመለከታሉ" ማለታቸው ነበር። ብዙ ሰዎች ይኸንን መልዕክት "አፍሪካ ላይ የተጫረው እሳት አውሮፓን ያነዳታል" ማለታቸው ነው ብለው ተረጉመውታል።




ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በስደት እንግሊዝ አገር ሲገቡ

በተጨማሪ የአውሮፓ ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያን በመናቅ እንጂ እንደ እውነቱ ከኾነ ግን የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረው በጣልያንና በኢትዮጵያ መካከል በ1928 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት ሳቢያ ነበር። ይኸንንም አፍሪካዊው ደራሲ አሊ ኤ ማዝሩዊ ዘ አፍሪካንስ ኤ ትሪፕል ሄሪቴጅ በሚለው መጽሐፉ ገጽ 276 ላይ እንደሚከተለው ገልጾታል።



"Indeed, I and other African political scientists and African historians believe that the Second World War did not begin in 1939 following the violation of the territory of Czechoslovakia and Poland. It began in 1935 following the violation of Ethiopia's sovereignty by Mussolini's Italy."

"በእውነቱ እኔና ሌሎች አፍሪካዊ የፖለቲካ ሳይንቲስቶችና የአፍሪካ ታሪክ ተመራማሪዎች የምናምነው የሁለተኛ የዓለም ጦርነት የተነሳው እ.ኤ.አ. በ1939 በቼኮዝሎቫኪያና ፖላንድ መወረር አለመሆኑን ነው። የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1935 ዓ.ም የኢትዮጵያ ልዕልና በሙሶሎኒ ጣልያን ሲጣስ ነው"



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጄኔቭ ንግግር ሲያደርጉ

እንግሊዞም ኾነ ፈረንሳይ ጣሊያንን ብዙ መነካካት ወደ ጀርመን ጓደኝነት ይገፋፉታል ብለው ስለፈሩና ራሳቸውም አስቀድመው ጣሊያን ኢትዮጵያን እንድትወር በስዌዝ ካናል በኩል መሣሪያዋንና ወታደሮችዋን እንድታሳልፍ ፈቅደው ስለነበረ ለኢትዮጵያ የጠቀመ ውሳኔ ሊገኝ አልተቻለም።

ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዝ አገር በሚኖሩበት ወቅት አመርቂ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ ብዙም ዕድል አልነበራቸውም። እሳቸውም መላ ጊዜያቸውን እንግሊዝ አገር ከመቀመጥ ይልቅ ወደ ካናዳ፣ ስዊድንና ወደ ሌላም አገር እየሄዱ እርዳታ መሰብሰብና የፖለቲካ ሰዎችን ማነጋገር መቻል ነበረባቸው። አንዱም ችግር በገንዘብ የሚገዙ ሰዎች አደጋ ሊያደርሱባቸው ይችላሉ ተብሎ ስለተገመተም ነበር። ለወጉ እንኳን በእንግሊዝ የንጉሣውያን ቤተሰብ አንድም ቀን ግብዣ ተደርጎላቸው አያውቅም ነበር። ለዚህም ምክንያቱ የብሪታኒያ መንግሥት በፊት በስውር ቀጥሎ ደግሞ በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም ኢትዮጵያ የጣልያን ግዛት መሆንዋን አምኖ መቀበሉን በይፋ ገልጾ ስለነበረ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ብሪታንያ የራሷ ጥቅም ባይነካ ኖሮ ጃንሆይ ምንም ነገር ሊያደርጉ አይችሉም ነበር። ይህም ሆኖ ጨዋነታቸውን ጠብቀው እንደማንኛውም ስደተኛ ኖሩ። በየጊዜውም ለአርበኞች መልዕክትና አዋጅ ያስተላልፉ ነበር። የጣሊያናዊ ባል የነበራቸው እንግሊዛዊቷ ሲልቪያ ፓንክረስት ከልጃቸው ጋር አገራቸው ተመልሰው ያዘጋጁት በነበረው "ኒው ታይምስ ኤንድ ኢትዮጵያን ኒውስ" በሚል ጋዜጣ ላይ በተለያየ ወቅት ጃንሆይ መግለጫ ሰጥተውበታል። የሲልቪያ ፓንክረስት ታላቅ እህት ናንሲ ፓንክረስት በንጉሥ ጆርጅ 5ኛ ጊዜ የታወቁ የሴቶች መብት ተከራካሪ ነበሩ። ሲልቪያ ፓንክረስት ከጣሊያናዊው ባለቤታቸው የወለዷቸው ሚስተር ሪቻርድ ፓንክረስት የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

በቢ.ቢ.ሲ. ራዲዮ ጣቢያ ጋባዥነት ጃንሆይ አንድ ቀን ኢትዮጵያን ለሚረዱ እንግሊዞች "እንኳን ለልደት በዓልና አዲስ ዓመት አደረሳችሁ" ለማለት በታክሲ ወደ ራዲዮ ጣቢያው ሲሄዱ የነበሩበት ታክሲ ተጋጭቶ ብራኳቸው ላይ መጠነኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ሃኪም ቤት እንውሰድዎት ብለው ሰዎች ቢጠይቋቸው በፊት ወደ ቢቢሲ ስቱዲዮ



ሄደው መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ስለመረጡ ይኸው ተፈጸሚል። ከዚያ በኋላ ሃኪም ቤት ተወስደው ታክመዋል።

በብሪታኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበሩት የቀዶ ሕክምናው ዶክተር ሃኪም ወርቅነህ እሸቴ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሌጋሲዮኑ ገንዘብ ምክንያት ሳይግባቡ ቀርተው ነበር። መጨረሻ ላይም ሃኪም ወርቅነህ (ዶክተር ማርቲን) ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ በርማ ሥራ ፈልገው ሄዱ። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በጡረታ ኖረው በ1945 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የልጅና የልጅ ልጆቻቸው ብዛት በአሁኑ ወቅት ከ52 በላይ ይሆናሉ።


ሃኪም ወርቅነህ እሸቴ (ዶክተር ማርቲን)

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ጥቂት ጊዜ እንደሠሩ እዚያው ሞተው ተቀበሩ። ኤምባሲው ውስጥ ገንዘብ እጥረት ስለተፈጠረ በጸሐፊነት ይሠሩ የነበሩት ወጣቱ አማኑኤል አብርሃም በኪስ ገንዘብ ብቻ ለመተዳደር በመቻላቸው እስከ መጨረሻው ቆዩ።

በዚህ መካከል አንድ ብርቱ የዲፕሎማቲክ ሰው በፈረንሳይ አገር ብቅ አለ። ይኸውም ወጣቱ አቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ሲሆን ፈረንሳይ አገር የነበረው የኢትዮጵያ አምባሳደር ስለከዳ የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪል ሆኖ በግል መኖሪያ ቤቱ ባንዲራውን ተክሎ የዲፕሎማቲክ ሥራውን ይሠራና ይታገል ጀመር። እንዲሁም ምሁሩ አቶ ሎሬንሶ ታእዛዝም ከጃንሆይ ጋር አብረው ከተሰደዱት መካከል የንጉሡን መልዕክት ወደ ኢትዮጵያ አርበኞች በማድረስ እየተላላኩ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ሠርተዋል።



ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝ

ሎሬንሶ ታዕዛዝ በአሥር ዓመት ዕድሜው ከሌሎች ኤርትራውያን ጓደኞቹ ከእነ ሻለቃ መስፍን የበጋ.ዕሽት፣ ጄኔራል ያዕቆብ ገብረ ልዑል፣ ጄኔራል ኢያሱ መንገሻና ሌሎችም ጋር ጠፍተው ወደ አዲስ አበባ መጥተ ሁ ተፈሪ መኮንን ትምሕርት ቤትና ስዊድሽ ሚሲዮን ገቡ። ሎሬንሶ ታዕዛዝ ፈረንሳይ አገር ተልኮ በታወቀ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሕግ ትምሕርቱን ጨርሶ ወደ አገሩ ኢተዮጵያ ተመልሶ ሲያገለግል በጠላት ወረራ ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱን ተከትሎ እንግሊዝ አገር ሄደ። የንጉሠ ነገሥቱን ትዕዛዝ በማስፈጸም ሲያገለግል ቆይቶ ከወረራው በኋላ ተመልሶ የልዑል ራስ እምሩን ልጅ አግብቶ አንዲት ሴት ልጅ ወልዷል። ከዚያም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመሆን ሲያገለግል ከቆየ በኋላ ወደ ስዊድንና መስኮብ (ሩሲያ) በአምባሳደርነት ተልኮ ሲኖር ታሞ ሲታከም ቆይቶ ሞተ። አስከሬኑ ወደ አገሩ ተመልሶ በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።






ዶክተር መላኩ በያን

በወረራው ወቅት በዚያው በእንግሊዝ አገር ሦስት ሺህ የሚሆኑ ወዶ ዘማቾች ወደ ኢትዮጵያ ሄደን እንዋጋ ብለው ቢጠይቁ ኤምባሲው ገንዘብ የለም ብሎ መለሳቸው። ዶክተር መላኩ በያንም አሜሪካን አገር ሄዶ የኢትዮጵያን መወረር ላልሰሙ በማስማትና ለአገሪቷም ወዳጅ ለማፍራት ብዙ ታግሏል። የጥቁር አሜሪካኖች ወዶ ዘማቾችን መመዝገብም ጀምሮ ነበር። ሆኖም በንጉሡና በአማካሪዎቻቸው ትኩረት ስላልተሰጠው አልተሳካለትም። ይህንንም ጥቁር አሜሪካኖች እንደንቀት ቆጥረውታል። ፕሮፌሰር ሃሮልድ ኢስሃቅ ኒው ወርልድ ኦፍ ኔግሮ የሚለው መጽሐፉ ላይ "በስደት ያሉት የኢትዮጵያ መኳንንትና ንጉሡ ባላቸው ንቀት ምክንያት ከጥቁሮች ጋር አንነጋገርም እያሉ የመላኩን ስብከት ባያደናቅፉ ኖሮ ኢትዮጵያን ለመርዳት የተነሳው ጥቁር አሜሪካዊ ተአምር በሠራ ነበር" ብሎ መጻፉን ተወዳጁ አዶ ጳውሎስ ኞኞ በጻፉት የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት መጽሐፍ ላይ ገልጸውታል።

ዶክተር መላኩ ለኢትዮጵያ ስደተኞችና ነፃ አውጭዎች የሚያገለግል ገንዘብ ለማግኘት ልዩ ቴምብርና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ፎቶግራፍ አባዝቶ በመሸጥና ዕርዳታ ለማሰባሰብ በበረዶ ወራት ከላይ እታች ሲንከራተት፣ ባለመታደል በብርድ በሽታ (በኒሞኒያ) ተለከፈ። ኢትዮጵያን ለድል በቅታ ለማየት አንድ ወር ሲቀረው ሕይወቱ አልፋለች።

ዶክተር መላኩ በያን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ድምፅ (**Voice of Ethiopia**) ጋዜጣው ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአበሔር ትዘረጋለች" የሚለውንም ጥቅስ እያተመ አሜሪካን አገር ውስጥ ለሕዝብ ያስራጭ ነበር።




የኢትዮጵያ የዓለም ፌዴሬሽን ምዝገባ ካርድና መታወቂያ

ዶክተር መላኩ በያን አርቆ አሳቢ ስለነበረ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ሕዝብም መታገል የጀመረ ብርቱ ሰው ነው። ስለኾነም የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ጭላንጭል እንዳይጠፋ እያሳመነና ተማሪ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ያምንበት የነበረውን የጥቁርን አንድነት (panAfricanism) እና የአፍሪካን ኅብረት (United Africa) አስተሳሰብ በማሰራጨት የታገለ ሰው ነበር። እሱ የፈጠረው ኢትዮጵያን ወርልድ ፌዴሬሽን ኢንኮርፖሬትድ (Ethiopian World Federation Encorporated) እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይንቀሳቀስ ነበር።



በዚህ መካከል ጃንሆይ መንግሥታቸውን ለኢጣሊያን ለመልቀቅ ውስጥ ውስጡን ይደራደሩ ነበር። እንዲያውም ውለታው ሊግ ኦፍ ኔሽን ቀርቦ የተፈረመው በሊግ ኦፍ ኔሽን የኢትዮጵያ ወኪል ስለነበረና ጃንሆይ ስላልፈረሙበት የሊግ ኦፍ ኔሽን አልቀበልም ስላለ ቀረ። ይህም 'ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ፋሽስቶች የወረራ ዓመታት' በሚለው አልቤርቶ ሳባቺ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ተዘርዝሯል። በአገር ውስጥም ራስ አበበ ይደራደሩ እንደነበረ ይታወቃል። እንዲህ ዓይነት ድርድሮች ጊዜ ለመግዛት የሚደረጉ ሊሆኑ ስለሚችሉ ውለታ እስካልተፈረመ ድረስ እንደ ስህተት ሊቆጠር አይችልም።

ቀን እየገፋ ሲሄድ ሁኔታዎች እየተለዋወጡ ሄደው ጣሊያን የገንዘብ ኪሣራ ደርሶባት በብድር ለወሰደችው የጦር መሣሪያ ዕዳ መክፈል ስላቃታት ጀርመን "ወይ ገንዘቤን ክፈይኝ አለበለዚያ ከእኔ ጋር ወዳጅነትሽን ይፋ አድርጊ" ብላ ስታስገድዳት መክፈል ስላቃታት ያላት ምርጫ የጀርመን አጋር መሆን ብቻ ነበር። ጊዜ ተለውጦ ከጣሊያን ጋር ሲጣሉ እንግሊዞች ኢትዮጵያን እንረዳለን ብለው የራሳቸውን ጠላት ለመውጋት ተሰለፉ። የዚህን ጊዜ ጣሊያንን ለማጥቃት አንዱ ዘዴ ያደረጉት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ መውጋትና ድል ማድረግ መሆኑን ስላወቁ ንጉሠ ነገሥቱን ማስጠጋት ጀመሩ።

እንግሊዞችም የጊዜ እጥረት እየመጣባቸው ስለሄደ በመጨረሻ ጦርነቱ ላይ ለመግባት ወሰኑ። ስለሆንም ጃንሆይን ወደ ሱዳን አመጡዋቸውና ለስድስት ወር ያህል ከካርቱም ውጭ "የሸሪፍ ሁሴን ቤት" በሚባለው ስፍራ ላይ እንደ እስረኛ አስቀመጧቸው። በመጨረሻ ላይ ግን ንጉሠ ነገሥቱ እዚያው ሱዳን ውስጥ ስደተኞችን እንዲያሰባስቡ ፈቀዱላቸው። ጃንሆይም ወታደሮቻቸውን አዘጋጅተው እነ አዛዥ ከበደን ከእሥራኤል አገር ጠርተው ወደ አገር ውስጥ መልዕክት ይዘው እንዲገቡና መንገድ እንዲከፍቱ አደረጉ።

እንግሊዞች ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ አገር ስለኾነች በሦስት ተከፍላ ነፃ ትውጣ። ሦስቱም የትግሬ መንግሥት፣ የአማራ መንግሥትና የኦሮሞ መንግሥት ይሆናሉ ብለው ተንኮል ጀምረው ነበር። ለዚህም ተግባር ኤርስክንና ብሮክልኸርስት የሚባሉ ሁለት እንግሊዞች ከሱዳን ወደ ካይሮ ሄደው ጄኔራል ዌቨልን አሳምነው ኢትዮጵያ ሊገቡ ሲሉ ጃንሆይ አስከለከሉ።



የኢትዮጵያ ጦር በሱዳን ልምምድ ሲያደርግ

የብሪታኒያ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት ያሰለፈው ጦር መጠነኛ የእንግሊዝ መኮንኖችና ከተለያዩ ቅኝ ግዛቶቹ ወታደሮች በማምጣት ነበር። ስለሆነም የደቡብ አፍሪካ፣ የህንድ፣ የሱዳን፣ የናይጄሪያ፣ የጋና፣ የቤልጂግና የነፃይቱ ፈረንሳይ ወታደሮች ዘምተዋል። ጥርነቱ ከተገባደደ በኋላ የብሪታኒያ አንዱ ችግር እነዚህ ወታደሮች አንድ የጥቁር መንግሥት በነፃነት ሊኖር መቻሉን እንዳያጤኑትና አገራቸው በተመለሱ ጊዜ ለሕዝባቸው የጥቁር መንግሥት መኖር መቻሉን ዓይተው ወደየአገራቸው ሲመለሱ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉትን ሕዝቦች እንዳይቀሰቅሱባቸው ነበር። በተለይ ከካልካታ የመጡት የህንድ ወታደሮች የነፃነት ስሜት በፊቱንም አሳይተው ስለነበረ ያመጧቸው ከህንድ ለማራቅና እንቅስቃሴያቸውን ለማጨናገፍ መሆኑ የታወቀ ነበር። ሆኖም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በጐጃም በኩል የኢትዮጵያን ምድር ረግጠው ኦሜድላ ላይ ሰንደቅ ዓላማ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም ሰቀሉ። የዚህን ጊዜ ሰማዩ ላይ ቀስተ ዳመና በመታየቱ መልካም ዘመን መምጣቱን አበሠረ ተብሎ ተገመተ።





# ምዕራፍ ፳

## የጣሊያን ወረራ

ጣሊያኖች ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት አደረግን ብለው ቢመጻደቁም ባኢትዮጵያውያን አመለካከት አገሪቱ ተወረረች እንጂ ቅኝ ተገገር አልኾነችም። ይኽ ከኾነማ ፈረንሳይ በዚያኑ ወቅት የጀርመን ቅኝ ግዛት በሆነች ነበር፣ ዩጎዝላቪያና ግሪክም በዚያኑ ወቅት በጣሊያን ተወርረው ነበር። የኢትዮጵያን ንጉሥ አልማረኩ፣ አልገደሉ ወይም ሕዝቡ አሜን ብሎ ባልተገዛበት ሁኔታ ቅኝ ግዛት ሊባል ይችላል? ነጭ ያልኾነ ሲሸነፍ ቅኝ፣ ነጭ የኾነ ግን ሲሸነፍ ወረራ ከኾነ ይህ አስተሳሰብ ለነጭ የሚያደላ ስለኾነ ፍትሐዊ አይሆንም።



ዘመናዊ ያልሆነው የኢትዮጵያ ጦር ወደ ማይጨው ሲዘምት

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላቶች እንግሊዝና ግብጽ እንጂ ጣሊያን አይደለችም። እንደማንኛውም ሌላ የአውሮፓ አገር ጣሊያንም ከአፍሪካ ቅርጫ ለመካፈል ስለጓጓች ሞኝነቷን የተገነዘበው እንግሊዝ ኢትዮጵያን ተወላት። እንግሊዝ ቀደም ብሎ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በገጠመው አለመግባባት ወደ ኢትዮጵያ ዘምቶ ብዙ ሁኔታ ተመልክቶ በመጣ እግሩ ሳይዋረድ ተመልሷል። ምክንያቱም በየአካባቢው የነበሩት ባላባቶች እያንዳንዳቸው ከንጉሡ እጅግ የሚበልጥ ጦር ስለነበራቸው አገሪቱን ይዞ መቀመጥ እንደማይችል ወዲያዉኑ ተረድቶት ነበር። ጣሊያን ግን ቀላል መሰሏት ኢትዮጵያን ለመግዛት ብዙ ትግል አድርጋለች። ታዲያ "የሞኝ ብትር ሆድ ይቀትር" እንዲሉ በጦርነቱ ወቅት ያዘነበችው መርዝ ይቅርታ የማይደረግለት ጥቃት ስለነበረ ሌላው የዓለም ሕዝብም ኾነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቀላሉ ሊረሳው አይችልም።



የኢትዮጵያ ዘመናዊ ጦር ወደ ማይጨው ሲዘምት

ከጦርነቱ በኋላ ኢትዮጵያ በእኩል ደረጃ ባልነበረችበት ወቅት በድርድር የተደረሰበት የ25 ሚሊዮን ዶላር የካሣ ክፍያ በምንም መልኩ በቂ አልነበረም። ጣሊያን ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ለዩጎዝላቪያ



እንድትከፍል ሲበየንባት ለኢትዮጵያ 25 ሚሊዮን ዶላር (ብር 62.5 ሚሊዮን) ብቻ እንድትከፍል መወሰኑ ያስተዛዝባል። በድርድሩ ወቅት አራቱ ኃያላን መንግሥቶች የተሸናፊዋን የጣሊያንን መብት ሲያከብሩና የግሪክና የዩጎዝላቪያን ካሣ ከፍ ሲያደርጉ በጦርነቱ በግፍ የተደበደበችውንና በመርዝ ጢስ ሕዝቧ ያለቀውን የኢትዮጵያን ጉዳት ሳያገናዝቡት በአነስተኛ ካሣ ጉዳዩን ዘግተውታል።

በተለይ ጣሊያን ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቴ ነች ብላ ማስታወቋን ስህተት እንደነበረ አምና ይቅርታ መጠየቅና ለዓለምም ማስታወቅ ነበረባት። ፈረንሳይም ብትሆን ከጅቡቲ አዲስ አበባ በተዘረጋው ባቡር በጦርነት ጊዜም ቢሆን ኢትዮጵያ የመጠቀም መብቷ በውሉ ላይ ተጠቅሶ እያለ ጣሊያን ባቡሬን ይመታብኛል በማለት ከልክላለች። በጣሊያን ወረራ ወቅት ግን የጠላት ጦር እንደፈለገው ሲመላለስበት ዝም ብላ ትመለከት ነበር። ስምምነቱ ላይ በግልጽ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያን መብት ፈረንሳይ ከጣሰች ባቡሩ በኢትዮጵያ መንግሥት ይወረሳል ይላል። ስለኾነም ፈረንሳይ ስምምነቱን ያፈረሰች ስለኾነ ኢትዮጵያ ደግሞ ጉዳዩን ዝም ማለት አልነበረባትም።

ኢትዮጵያ በማይጨው ጦርነትና በወረራው ምክንያት የደረሰባት ጉዳት እንደሚከተለው ነው።

| | |
|---|---|
| የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት | 2,000 |
| የተቃጠሉ አይሮፕላኖች | 15 |
| የፈረሱ ቤቶች | 525,000 |
| የተገደሉ የሠራዊት ብዛት | 275,000 |
| የተገደሉ አርበኞች ብዛት | 75,000 |
| በየካቲት 12 ቀን1929 ዓ.ም የተገደሉ | 30,000 |
| በፍርድ ቤት በሞት የተቀጡ | 2,400 |
| በማጎሪያ ቤት የሞቱ | 25,000 |
| በችጋር እንዲያልቁ የተደረጉ ሰዎች | 30,000 |
| የሞቱ የቀንድ ከብቶች | 500,000 |
| የጋማ ከብቶች (ፈረስ አህያ በቅሎ) | 1,000,000 |
| ግመሎች | 789,060 |

በጠቅላላው በ746,800 ሰው ላይ የሞት አደጋ የደረሰ ሲሆን በአካለ ስንኩልነት በየቤቱ ምንያህል ሰው እንደተጎዳ አይታወቅም። ለጦርነቱ ማካሄጃ የባከነው ወጭ በቁሳቁስና በሰው ጉልበት ሲተመን አያሌ ነው። በዝርፊያ የተወሰዱት የታሪክ ቅርሶችም አያሌ ናቸው። ለዚህ ሁሉ በደል በካሳ መልክ ኢትዮጵያ ያቀረበችው ኪሣራ 175 ሚሊዮን ስተርሊንግ ሲሆን የተሰጣት 25 ሚሊዮን ዶላር ሊሠራ የቻለው የቆቃን ግድብ ነው። ስለኾነም የወረራው ቀጥተኛ ተጎጂዎች በግል ያገኙት ዕርዳታ አልነበረም። በአንጻሩም ወራሪው መንግሥት አገሩን እኖርበታለሁ ብሎ በማሰብ መንገዶችንና ሌሎች የአገልግሎት ተቋሞች መሥራቱ ባይዘነጋም የጣሊያን ጦር ግን በሚሸሽበት ወቅት እንደገና አፈራርሶታል። ሊረዱ የመጡትም እንግሊዞች ቢሆኑ የተቻላቸውን ያህል ዘርፈዋል።



ጀኔራል ባዶሊዮ



በማንኛውም ችግር ላይ ኢትዮጵያ ስትወድቅ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ውሳኔ ኢትዮጵያን የሚያግዝ ሆኖ አያውቅም። ከእንግዲህም ወዲያ ከዓለም መንግሥታት በችግሯ ጊዜ ኢትዮጵያ ፍትሕ ታገኛለች ብሎ መጠበቅ ተላላነት ነው። ኢትዮጵያ ግን የዓለም መንግሥታትን ሕግና ደንብ ከማክበሯም በላይ ወታደሮቿን ኮርያ፣ ኮንጎ፣ ሩዋንዳና ቡሩንዲ ልካ በጀግንነት ተዋግታለች። ለዓለም መንግሥታት ማኅበራትም የሚጣልበትን መዋጮ በወቅቱ በመክፈል የሚወዳደራት የለም።



የኢትዮጵያ ወታደር በኮሪያ የተባበሩት መንግሥታት ዘመቻ ላይ

ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች አገር ጦርነት ገጥሞ ድል ስላገኘ ብቻ የእኔ ቅኝ ነች ብሎ ለዓለም ሕዝብ ቢያስታውቅም አንድም የተቀበለው የታሪክ ጸሐፊ አልተገኘም። በእርግጥም አንድን ነፃ አገር በጦርነት አሸንፎ ገብቶ መያዝ ወረራ እንጂ ሌላ አልነበረም።

ድንጋይ ዱቄት አርገው መንገድ የሚሠሩ
ጠብቅ ይመጣሉ ታዘበኝ ቢቀሩ


ሼህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፳፩

## የጣልያን ጊዜ

ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ባዶሊዮ በነጭ ፈረስ ተቀምጦ ጦሩን እየመራ አዲስ አበባ በገባ ዕለት በኢጣሊያን በኩል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን በኢትዮጵያ ላይ አከተመ። ንጉሠ ነገሥቱ በተቻኮለ መልኩ ሚያዝያ 23 ቀን ሌሊቱን በባቡር ሲጓዙ አድረው ሚያዝያ 25 ቀን ጅቡቲ ገብተው በመርከብ ከመኳንንቶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ እሥራኤል አገር አመሩ። ደጋፊዎቻቸው ለዓለም መንግሥታት አቤቱታ እንደሄዱ አድርገው ያቅርቡት እንጂ በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ እንደሸሹ ተቆጥሯል። ይህንን ሁኔታ በመገንዘብ ባላባቶችና የጦር አበጋዞች ሁሉ ለጠላት እጅ እየሰጡ ወደ እርሻቸውና ንግዳቸው ተመለሱ።




ኃይለ ማርያም ማሞ

ሆኖም የሕዝቡ መንፈስ ቢዳከምም አርበኝነቱ ግን ገና ጣሊያን ወደ አዲስ አበበ ለመግባት በሚጓዙበት ጊዜ ደብረ ሲና ላይ ባሻ ወልዴና ፊታውራሪ ተሰማ እርገጤ ከባለሚሎቻቸው ጋር በጠላት ጦር ላይ በጣሉት አደጋና ባደረሱት ጉዳት የደፈጣ ውጊያ ተጀመረ። አስከትሎም ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም ኃይለ ማርያም ማሞ ደብረ ብርሃን መንገድ ላይ ሰባት መኪና በማቃጠልና ወደ 140 የሚሆኑ



የጣሊያን ነጭ ወታደሮች በመፍጀት ትግሉ ተቀጣጠለ። ጣሊያን አዲስ አበባ ከገባም በኋላ የአርበኝነት እንቅስቃሴ ባይጠናከርም በየቦታው እያቆጠቆጠና እያደገ ሄደ።

የጣሊያንን ጦር እንዲያዘምት ተዘጋጅቶ የነበረው በወቅቱ ኤርትራን ያስተዳድር የነበረው ማርሻል ጄኔራል ደቦኖ በዕድሜ ገፋ ያለ፣ ጦረኛ ያልኾነ፣ ፖለቲከኛና የሰለላ ሹም የነበረ ስለኾነ ሙሶሎኒ ጦርነቱን እንዲመራ አላመነበትም። ስለኾነም የተዘጋጀውን የሰናፍጭ መርዝ በሕዝብ ላይ ለመርጨት ዝግጁ የነበሩት አረመኔዎቹ ጄኔራሎች ባዶልዮ በሰሜን፣ ግራዚያኒ በምሥራቅ ተመድበው የሙሶሎኒን ቅዠት ዕውን ለማድረግ ችለዋል።



አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒ የኢጣሊያን ንጉሥ ወንድ ልጅ መወለድን ምክንያት በማድረግ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ

የአዲስ አበባ ከተማን ነዋሪ ሰብስቦ ንግግር ሲያደርግ ቦንብ ተወርውሮበት ባይሞትም 365 ቦታ ላይ ቆሰለ። የዚህን ጊዜ ጣሊያኖች ለበቀል ባገኙት መሣሪያ በአካፋና በዶማም ጭምር ያገኙትን ኢትዮጵያዊ ጨፈጨፉት፣ ቤቱንም አቃጠሉት። በተለይ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮች የአዲስ አበባን ሕዝብ ሦስት ቀን ሙሉ ሲጨፈጭፉ ከርመው በግምት ወደ 30,000 ሰው ገደሉ።

ይህንን አደጋ የጠነሰሱት ሦስት ወጣቶች ሲሆኑ ሁለቱ ቦንብ እንዲወረውሩ አንዱ ግን መኪና አሰናድቶ ቦነብ ወርዋሪዎችን ይዞ ለመጥፋት ተዘጋጁ። በዚሁ መሠረት ግራዚያኒ ላይ ጉዳት ከአደረሱ በኋላ ተያይዘው የሸሹት ወደ ደብረ ሊባኖስ መሆኑ ተደርሶበት ፋሽስቶቹ እዚያው ድረስ ተከታትለው ሄደው ብዙ ቀሳውስት ሲፈጁ ሁለቱ ቦንብ ወርዋሪዎች ከአርበኞች ጋር ተደባለቁ። በኋላም ወደ ሱዳን ለማምለጥ ሲሞክሩ መንገድ ላይ ዘራፊዎች ገደሏቸው። ሦስተኛው ግን መኪናውን እየነዳ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ በፊርማቶሪ (ሰላይ) ጠቋሚነት ተይዞ ሰሲቃይ ቆይቶ ተገደለ።



ባለታክሲው ስምዖን አደፍርስ

ይህ ድርጊት በዓለም የዜና መገናኛ ሁሉ ስለተወሳ ለአቤቱታው ተሰሚነት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዲያውም ሃሳቡን የሰጡትና ያቀናጁት አቶ ሎሬንሶ ታዕዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አለመገዛቱንና ጣሊያንም ሠላም እንደሌለው የዓለም ሕዝብ እንዲገነዘበው ያደረጉት ጉዳይ መሆኑ ይነገራል። ፈንጂውንም የሰጧቸውና ግቢም እንዲገቡ የረዷቸው ደጃዝማች ለጥይበሱ ገብሬ ነበሩ። እነዚህ ሦስቱ ወጣቶች ቦንብ ወርዋሪዎቹ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ሲሆኑ ሦስተኛው በታሪክ ስሙ ሳይጠራ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኖረው ስምዖን አደፍርስ ነው። ምክንያቱም ይህ ወጣት ብዙ ታክሲ የነበረው ስለሆነ የእሱን ታክሲዎች



የነጠቁት ባንዳዎች ከነፃነት መልስ ባለሥልጣን ሆነው ስለነበረ የእሱ ስም መነሳት ምስጢራቸውን እንዳያጋልጥባቸው በመሥጋታቸው ነው[16]።

በሆለታ የጦር ትምሕርት ቤት ይማሩ የነበሩና ወጣትና ምሁር አገር ወዳዶች አምቦ (ሃገረ ሕይወት) ላይ ስብሰባ አድርገው አንድ የህቡዕ ማኅበር መሠረቱ። ለማኅበሩም ፕሬዚዳንት አድርገው ምሁሩን ልጅ ይልማ ደሬሳን ቢሾሙት ስለኦሮሞ ነፃነት ጉዳይ ሲያነሳ ስለዚህ ለመነጋገር ወቅቱ አይደለም በማለት ጭራሽ ከሥልጣኑ አንስተው ዶክተር ዓለመ ወርቅን ሾሙ። በኋላም ለማኅበሩ ስም ሲያወጡለት የይሁዳ አንበሳ የሚለውን ስም ቀይረው ጥቁር አንበሳ ብለውታል። በነበረው ውይይት ላይ ደጃች ታከለ ወልደ ሃዋርያት ተገኝተው የንጉሣዊ አገዛዝን በማጣጣል ስለ ሪፓብሊክ መንግሥት ምሥረታ እንነጋገር ቢሉ ይህ ጉዳይ በቆይታ እንዲያዝ ተወሰነ። በዚህን ጊዜ ታከለ ተለይተው ሲቀሩ ሌሎቹ ወደ ጎሬ ሄደው ማጥቃት ጀመሩና የጣሊያንን አይሮፕላኖች አቃጥለው ወታደሮችንም ገደሉ። በዚህ በጣሉት አደጋ ምክንያት ጎሬ ላይ ችግር ስላጋጠማቸው ራስ እምሩን አጅበው ወደ ጅማ ሲያመሩ ሲደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው በጣሊያኖች ተማረኩ። ሌሎቹ ደግሞ በየበኩላቸው ሲታገሉ ጥቃት ሲበዛባቸው ወደ ሱዳንና ወደ ኬንያ ተሰደዱ።



የጣሊያን ወታደሮች

የተማረኩት የጥቁር አንበሳ አባሎች መጨረሻ ላይ ምሕረት ተደርጎላቸው ሲኖሩ የእንአብርሐ ደቦጭ ቦንብ መጣል ባስከተለው ቂም አብዛኛዎቹ እንደገና ተሰብስበው ተገደሉ። አንዳንድ እጅ አንሰጥም ብለው የወላወሉ መኳንንቶችም ጥብቅ ክትትል ተደርጎባቸው እየታደኑ ተገደሉ። ሌሎች ደግሞ እየተደራደሩ እጅ የሰጡ በእስር ስለነበሩ የዚሁ

[16] ጦቢያ መጽሔት 8ኛ ዓመት ቁ 9

የአነ አብርሃ ደቦጭ የቦንብ ውርወራ ባስከተለው ቁጭት ተሰብስበው በእስር ወደ ጣሊያን አገር ተወሰዱ።


ጣሊያን በተቻለው ዘዴ ሁሉ ሕዝቡ በፍርሃት እንዲገዛለትና በአድዋ ጦርነት የተዋረደውን ለማካካስ ሲል ቂሙን መወጣት ጀመረ። የአድዋው ተወላጅ አውዓሎም የሚባል በስለላ ጣሊያኖችን በአድዋ ጦርነት ወቅት ከድቶ እንዲሸነፉ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ የታወቀ ስለነበረ፣ እሱን ምንም በሕይወት ባያገኙትም ተወላጆቹን እየፈለጉ በመፍጀት ቂማቸውን ተወጡ።


ጄኔራል ግራዚያኒ

የጣሊያን አስተዳደር ጭካኔ ስላበዛ በየአካባቢው አርበኞች እንደገና መንቀሳቀስ ጀመሩ። ኃይለ ማርያም ማሞ ሸዋ ውስጥ ተደራጅቶ እስከ አዲስ አበባ ድረስ እየገባ አደጋ ጥሎ ጣሊያኖችን አደናገጠ። እንዲሁም እነሻለቃ መስፍን፣ እነደጃች ባልቻ፣ ከተሰወሩበት መንቀሳቀስ ጀምረው በተለያየ ወቅት አደጋ ማድረስ ጀመሩ። አስከትሎም አዲስ አበባን ለመያዝ በእነአቡነ ጴጥሮስ ጎትጓችነት አርበኞች በአራት አቅጣጫ ገብተው አደጋ ለማድረግ ተስማምተው በሁለት አቅጣጫ ያሉት መግባት ሲጀምሩ በሌላው በኩል ያሉት በተባለው ወቅት በመገናኛ እጦትና በመወላወል ምክንያት በአንድነት ባለመግባታቸው ውጤቱ አልሰመረም። ይኸውም ደጃች ፍቅረ ማሪያም አባ ተጫን በየካ በኩል ገብተው ታላቁን ቤተ መንግሥት ለመያዝ ባዕታ ለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ደርሰው ሌሎቹ በዕቅዱ መሠረት ስላልደረሱላቸውና ኃይል ስላነሳቸው ተመለሱ። ደጃች ባልቻም በአሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ በኩል አልፈው ነፋስ ስልክ ደርሰው የማይሆን ሲሆን




ተመለሱ። በሰሜን በኩል የተሰለፉት ሁለቱ የራስ ካሣ ልጆች ደጃዝማች አበራ ካሣና ወንድ ወሰን ካሣ ደግሞ በራስ ሥዩም አግባቢነት እጃቸውን ለጣሊያን ሰጡ። የሞተው ሞቶ የሸሸው ሸሽቶ ውጥኑ ሳይሳካ በመቅረቱ የጣሊያንን አስተዳደር ይበልጥ አበረታው። አቡነ ጴጥሮስ ግን አልሸሽም ብለው አዲስ አበባ ቁጭ ካሉበት ቤታቸው ተይዘው "ለጣሊያን ተገዙ" ብለው ሕዝቡን እንዲሰብኩ ቢጠየቁ ጭራሽ "ለጣሊያን የተገዛህ ውጉዝ ሁን!" ብለው ስላሉ ፍርድ ቤት ቀርበው ተፈረደባቸውና በሞት ተቀጡ። ችሎቱን የመራው ጣሊያናዊ የመሃል ዳኛ ኮንቴ ዴ. ላ. ፖርቶ፣ የቀኝ ዳኛ፣ ብላታ አየለ ገብሬ፣ የግራ ዳኛ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ፣ አስተርጓሚዎች (ትርጁማኖች) ደጃዝማች አርአያ ዋሴና ፊታውራሪ ሮዛርዮ ነበሩ። የተሰየሙት ዳኞች አቡነ ጴጥሮስ ላይ በአንድ ድምጽ የሞት ፍርድ ፈርደውባቸው ሕዝብ ፊት በመትረየስ ተረሸኑ። አቡነ ጴጥሮስ በተረሸኑበት ዕለት መሣሪያ ለሸፍታ አቀብላችኋል ተብለው የተያዙ አራት ወንድና አንድ ሴት ከአፍንጮ በር እስር ቤት ተወስደው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበቴ ቤቱ አጠገብ ተሰቀሉ።


አስተርጓሚው ዘርዓይ ድረስ

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጣሊያን ዋና ከተማ በሆነችው በሮማ ውስጥ በአስተርጓሚነት የሚሠራው ዘርዓይ ድረስ አንድ ቀን ከአንድ ታላቅ መኮንን ቤት ጎራዴ አምጣ ተብሎ ተላከ። በአጋጣሚ ጎራዴው እላዩ ላይ በተጻፈው ስም የራስ አሉላ የነበረ መሆኑን ተረዳ። ይህችን ጎራዴ ይዞ ሲመለስ ጣሊያኖች ከሰገሃር ነቅለው ወስደውት የነበረውን የይሁዳ አንበሳ የተባለውን ሃውልት አስቀምጠው ሲሳለቁበት ዓይቶ ንዴቱ ግንፍል ይልበትና በአካባቢው ያለውን ሰው ሁሉ በያዘው ጎራዴ አስፈራራ። ከዚያም ሐወልቱ ላይ ወጥቶ ይቆምና "እናንተ ጣሊያኖች ነፃነታችሁን ካገኛችሁ ገና ጥቂት ጊዜ በመሆኑ ስለነፃነት የምታውቁት ነገር አንድም ስለሌለ ነውራችሁ እዚህ በምታደርጉት ተገልጿል" እያለ ሲናገር አንድ ወታደር ተኩሶ እግሩን

አቁስሎ ያዘው። ከዚያም ዕብድ ነው ብለው የአእምሮ ህሙምተኞች ሆስፒታል አስገቡት። ዘርዓይ ድረስ የፈጠረው ሁኔታ ጣሊያኖችን ስላስቆጣቸው በንዴት ጣሊያን አገር ከነበሩት እስረኞች 147 ያህሉን ወደ አዚናራ የእስር ደሴት ሲወስዱ ሌሎቹን ደግሞ ሰብስበው ወደ ሞቃድሾ አመጧቸው። ከነፃነት በኋላ ዘርዓይ ድረስ ወደ አገሩ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ተወስኖ ሲመጣ ሲል ከትባት ነው ብለው በመርፌ መርዝ አድርገውበት ገደሉት። በኋላም ለስሙ ማስታወሻ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ ዘርዓይ ድረስ ተብላ ተሰየመች።



የኢትዮጵያ ካርታ በጣልያን ጊዜ

የጣሊያን መንግሥት በመጀመሪያ ድል አድርጎ የገባውን ባዶሊዮን፣ ከእሱም ቀጥሎ በጥቂት ቀን ውስጥ ግራዚያኒን ጠቅላይ ገዥ በማድረግ ኢትዮጵያን፣ ኤርትራንና የጣሊያን ሱማሌን በአንድነት የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት በማለት ስድስት ክፍለ አገሮች ፈጥሮ ማስተዳደር ጀመረ። ከነዚህ ስድስት ክፍለ አገሮች ውስጥ አዲስ አበባና አካባቢዋ



አንዷ ነበረች። የቅኝ ግዛት ቢሮውም አዲስ አበባ ዋናው ፖስታ ቤት ፊት ለፊት የሚገኙት ሁለት ፎቅ ቤቶች ሲሆኑ የሙሶሎኒ ጽሕፈት ቤት ይባሉ ነበሩ። በኋላም እነዚሁ ፎቅ ቤቶች የፍትህና የአገር ግዛት ሚኒስቴር በመባል ይታወቁ ነበር።

አርበኞች በተቻላቸው መጠን ተጋድለው ቢያደርጉም እጅ ሰጥተው የገቡ መኳንንቶች ግን ደሞዝ ተቆርጦላቸው ለጣሊያን ገብረው ይቀመጡ ነበር። በተለይ ራስ ኃይሉ በውስጣቸው የባንዳ ወታደር ስለ ነበራቸውና እሳቸውም አልገብርም ያለውን መኳንንት በማግባባት ብዙ አገልግሎት ለጣሊያን ሰጥተዋል።

የቄሣር መንግሥት የወር ደሞዝ ይከፍላቸው የነበሩት የሚከተሉት ናቸው

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ | ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት | 40,874 ሊሬ በወር |
| 2ኛ | ደጃ. ኃይለሥላሴ ጉግሣ | 25,000 ሊሬ በወር |
| 3ኛ | ሼክ ኤል ሆጃሊ | 25,000 ሊሬ በወር |
| 4ኛ | ራስ ሥዩም መንገሻ | 22,900 ሊሬ በወር |
| 5ኛ | ደጃ አያሌው ብሩ | 16,000 ሊሬ በወር |
| 6ኛ | ሡልጣን ሙሐመድ ሃንፋሪ | 15,000 ሊሬ በወር |
| 7ኛ | ደጃ. ሆማና ጆቴ | 15,000 ሊሬ በወር |
| 8ኛ | ደጃ. ዮሐንስ ጆቴ | 15,000 ሊሬ በወር |
| 9ኛ | ሡልጣን አብዱላሂ አባ ጂፋር | 8,000 ሊሬ በወር |
| 10ኛ | ሡልጣን አባ ጆቢር አብዱላሂ | 8,000 ሊሬ በወር |
| 11ኛ | ራስ ጌታቸው አባተ | 7,000 ሊሬ በወር |
| 12ኛ | ደጃ. ታየ ጉልላቴ | 1,000 ሊሬ በወር |

ከወር ደሞዝ በተጨማሪ የሜዳሊያ ሽልማትና ጉብኝት ተችረዋል።

1ኛ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት የኢጣሊያ ኮከብ ሜዳሊያ
2ኛ ለሡልጣን አባ ጆቢር የአረብ አገሮች ጉብኝት
3ኛ ለደጃ. አያሌው ብሩ የኢጣሊያ ኮከብ ሜዳሊያ

በዘመኑ እጅ ሰጥተው የገቡና የቄሣር መንግሥት ሠራተኛ የነበሩ በርካታ ሰዎች እንደነበሩ ዕሙን ነው። በጋዜጠኛነት በአስተርጓሚነት በአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሥራ ተሰማርተው የነበሩና ደሞዝ ያገኙ ከነበሩት ታዋቂ ሰዎች መካከል ከብዙ በጥቂቱ፣ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ አቡነ አብርሃም (መምህር ደስታ)
2ኛ አቡነ ይስሐቅ
3ኛ ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ
4ኛ አቶ ይልማ ዴሬሳ
5ኛ አቶ ከበደ ሚካኤል
6ኛ ብላታ አየለ ገብሬ
7ኛ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ ወዘተ..

በዚያው መጠን የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በድሏቸዋል ያላቸውን ሰዎች ጣሊያን ሹመት መስጠት ጀምሮ ነበር። ስለሆነም ደጃች አባ ውቃውን ራስ ብሎ ሾማቸው። ራስ ኃይሉ ዋናው ታዋቂና የበላይ መኳንንት ተደርገው ስለታዩ ሙሶሎኒ እምቢ ባይል ኖሮ ለማንገሥም ታስቦ ነበር። እስትውም በግል ንጉሠ ነገሥቱ ላይ ቂም ስለነበራቸው ብቻ አገራቸው በጠላት ስትወረር ዋና አስተናባሪ በመሆን አምስት ዓመት ሙሉ ጣሊያንን ሲያገለግሉ ኖረዋል። ራስ ሥዩምም መኳንንቶችን ለጣሊያን እጅ እንዲሰጡ በማግባባት ብዙ አገልግለዋል። በመሠረቱ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቅያሜ የነበራቸውና የሚጠሉዋቸው ቢሆኑም አገራቸውን ለምን ይክዱ እንደነበረ አይታወቅም። በተቃራኒው ደግሞ እንደ ደጃች ባልቻ ያሉ ጀግኖች አለመውደዳቸው ግልጽ የነበረ ቢሆንም ከምኒልክ ጋር አብሬ የገነባሁትን አገር ጠላት ሲያጠፋው ዝም ብዬ አላይም ብለው በ80 ዓመት ዕድሜያቸው በአርበኝነት ተሠማርተው በውጊያ ላይ ተገደሉ።


ፀሐይ ዕንቆ ሥላሴ

ጣሊያኖች ወርነት ከጀመሩ አንስቶ መንገድ መሥራት፣ ከገቡም በኋላ ለየመስተዳድሩ ጽሕፈት ቤትና ለባለሥልጣኖቻቸው መኖሪያ ቤት ማነጽ ጀመሩ። አዲስ አበባ ውስጥ በተለይ ካዛንቺስ ፖፖላሬና በላይ ዘለቀ መንገድ ብዙ ቤቶች ተሠርተዋል። በጅማም አዲሱ አራዳ በሚባለው ሠፈር የሠሯቸው በርካታ ቤቶች አሁንም አሉ። በጎንደር ከተማ በጣሊያን የተሠሩትን ሃምሳ ቤቶች ጣሊያን ተሸንፎ



በ1934 ዓ.ም ሲወጣ በንዴት ሕዝቡ የጠላት ቤት ነው ብሎ አፈራረሰው። በአሁኑ ወቅት በጎንደር ከተማ ጨዋ ሠፈር ውስጥ ሳይፈርሱ የቀሩ ፎቅ ቤቶች ቢገኙም ነዋሪዎቹ ፎቅ ቤት ላይ ሙቀጫ ሲወቅጡበት ምድር ቤት ያሉት ኩበት ሲያጨሱበት ቤቱ እየፈራረሰ ይገኛል።

አገሩን ለብዙ ዘመን የሚያስተዳድሩ መስሏቸው ጣሊያን አገር ያሉ ኩባንያዎቻቸውን እያጫረቱ ብዙ ሥራ ላይ ጠምደዋቸው ነበር። በኋላ ግን መንግሥታቸው ስለከሰረ ኩባንዮቹን ሳይከፍላቸው ቀርቶ ብዙዎቹ ከሰሩ።


ራስ አበበ አረጋይ

ከፋፍለህ ግዛ የሚለውን ፍልስፍና ሥራ ላይ ለማዋል በአዋጅ የነፁና የጥቁር ተግባሮችንና የሕብረት ኑሮን ማናጋት ጀመሩ። ምንም እንኳን ወደ ኮሎኒያቸው የላኩት ወታደር ወደ 300,000 ያህል ቢሆንም ሚስቶቻቸውና እሬሞኛዎቻቸው በአካባቢ ስለሌሉ ወታደሩ በተወሰነበት ማዕቀብ አልተደሰተም። ለተለያዩ ሥራዎች የመጡት ጣሊያኖች ሁሉ የሚኖሩት በየትናንሽ ጎጆ ቤትና በየመንደሩ ስለነበረ በጣሊያኖችም ጠባይ የመቀራረብ ሁኔታ ሊገታ ባይችልም መንግሥታቸው ግን የተጋቡትን ጥቁሮችና ነጮችን እስከማፋታትና የእስራትና የገንዘብ ቅጣት መጣልም ሞክሮ ነበር። በአዲስ አበባና በአሥመራ የመጠጥ ቤት መብዛትን፣ የሴትኛ አዳሪዎች ቁጥር መበራከትንና የአባለዘር በሽታ መስፋፋትን አስከተለ።

"ከፋፍለህ ግዛ" መልኩ ብዙ ስለኾነ ክርስቲያኑን እንደጠላት እንዲመለከቱ ሙስሊሞቹን እናንተን ከጭቆና ልናወጣ ነው የመጣነው በማለት መስጊድ መሥራትና ማደስ ጀመሩ። አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን የአንዋር መስጊድ የሠሩት ኢጣሊያኖች በገንዘባቸው ነው። በተጨማሪም አማራውን እንደጠላታቸው በማየት በእሱ ላይ ኦሮሞዎችን ለማነሳሳት

ብዙ ደክመዋል። ኦሮሞዎች መጨረሻ ላይ ጣሊያንን ስላላመኑት ሊግባቡ አልቻሉም። በኦሮሞ አካባቢ የነበሩትንም አማሮች በሰፈራና በማጎሪያ (Concentration Camp) ማገትም ጀምረው ነበር። በኋላ ረሃብ ሊመጣ ይችላል ብለው ስለፈሩ እንደገና መሬት እየሰጡ እርሻ ላይ እንዲሰማሩ አደረጉ። የተቸገሩ አማሮች ለጣሊያኑ ወታደር እየሆኑ ማገልገል ሲጀምሩ ጥሩ ወታደር ኾነው ስላገኟቸው እንዲያውም ወደፊት ጣሊያን ላላት የኮሎኒ ማስፋፋት ዕቅድ ጠቃሚ ናቸው በማለት በርትተው ማሠልጠን ጀምረው ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ የዘር መድልዎ (አፓርታይድን) ሥራ ላይ ለማዋል የጣሊያን መንግሥት ሙከ ፡ አድርጎ ነጭ የሆቴል ቤት አሳላፊ ለጥቁር እንግዳ እንዳያሳልፍ ጥቁርና ነጭ አብረው አንድ ሆቴል ውስጥ እንዳይስተናገዱ ከልክሎ ነበር። ነገሩ በጊዜ ማጠር ተቀጨ እንጂ ለም መሬቶችን ለነጭ ሰፋሪዎች ደልድሎ ነበር። እንዲሁም የንግድንም ዓይነት ለመለየት ሞክሮ አልኾነለትም። የመታከሚያ፣ የመኖሪያ፣ የመገበያያ፣ ቦታዎችም ተለይተው ነበር። ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ የአገሬው ሰው ገበያ (ማርካቶ ዲ ኢንዲጅኖ) የነጮቹ ገበያ ፒያሳ ተባለ። የአገሬው ሰው መታከሚያ (ሆስፒታሌ ዲ ኢንዲጅኖ) ተክለ ሃይማኖት በርበሬ በረንዳ ፊት ለፊት ሲሆን የጣሊያኖቹ ሃኪም ቤታቸው ሃኪም ቦራ (ራስ ደስታ ሆስፒታል) ነበር። ሌላውም የነጮች ሃኪም ቤት የአሁኑ ቤተ መጽሐፍት ወመዘክር ነበር።

ኢትዮጵያውያኖች በየምክንያቱ በመጨቆናቸው እያመረሩ ስለሄዱ ጣሊያንን እየከዱ በስፋት በአርበኝነት ላይ በመሰማራታቸው ከየከተማዎች በስተቀር ጣሊያኖችን ሊያፈናፍኗቸው አልቻሉም። በጐጃም ከደብረ ማርቆስ፣ በከፋና ኢሉባቦርም ከጅማና ከጎሬ ከተማ በስተቀር ጣሊያን አልነበረም። ወደ ጅቡቲ የሚያመራውን የባቡር ሃዲድ የቡልጋና የደብረ ዘይት አካባቢ አርበኞች በየቦታው እየነቃቀሉ ጉዳት ማድረስ ጀመሩ። ኤርትራ ውስጥ ተቀጥረውና ሠልጥነው ይዘዋቸው ያመጧቸው ወታደሮችም ገና ጦርነቱ ሳይጀመር አንስቶ መክዳት ጀምረው ስለነበረ የአርበኞቹን መበርታት ሲመለከቱ በብዛት መደባለቅ ጀመሩ። ከየጎሣው ሁሉ በወታደርነት ቀጥረው ያሠለጠኗቸውም እየከዱዋቸው ከአርበኞቹ ጋር ስለተደባለቁ ጣሊያኖች ስጋት ገበቷቸው ተጨማሪ ጦር አምጥተው የነጭ ወታደሩ ብዛት 500,000 ኾነ።



ለብዙ ጊዜ የሚሆን ስንቅ ።

ምንም የናታችን የኢትዮጵያ አርበኞች ስመ ጥሩ፣ልበኩሩ ስለምለሚቱ ሀገራቸው ወተት የሆነ ደማቸውን ማፍሰስ እንጂ ምንአበላ፣ምንእጠጣ የማይሉ በእግዚአብሔር ታምነው ንጉሠ ነገሥታቸው ባዘዛቸው ሥፍራ እየሄዱ ጠላታቸውን እመድ እያደረጉ መምጣታቸውን ባውቀው አንድ አንድ ሰው ይፈልገው እንደሆነ በማለት እድሜና በርከቱ ያለውን ለሽክምም ቀላልነት ያላቸውን የማውቃቸውን የስንቅ ስራዎች ከዚህ ቀጥዬ ጽፌ አቀርበሰሁ ።

፩ኛ ፤ የብርንዶ ሥጋ ዱቄት ፬ እጅ። ፪ኛ ፤ ጨውና ቅመሙ ሞቅ ስርሮለው አብሮት የተቀመመ ብትን ድልህ ለሥጋው ዱቄት ከራት አንድ የሚሆን እንደ ብዛትና ማነሣቸው የሚችላቸውን ድስት ጥዶ መጀመሪያ የቀይ ሽንኩርት ዱቄት በርከት አድርጎ ማቁላላት ቀጥሎ ድልሁን መጨመር ሲበስል ቅቤ በርከት አድርጎ ጨምሮ በጣም ማብሰል ቀዝቃዛ ውሀ አይወድምና እጉን ሙቅ ውሀ አስናድቶ የሥጋውን ዱቄት እንዲዋሀድ እየነሰነሱ ሲወፍር ከውሀው እየጨመሩ ነዋሪ ነውና ጨዉን እየቀመሱ መጨመር ነው ።

ሌላውንም ቅመም እስቲጣፍጥ ማድረግ ነው ነገር ግን ሲሰራ ውሀ እንዳይበዛ መጠበቅ ነው በስሱ ሲወጣ ወፍሩ የገንፎ ያህል እንዲሆን ያስፈልጋል ከበሰለ በኋላ ሲሆን ቆርቆሮ አለዚያም በስራት የተገጠመ ሳጥን ነፋስ የማያስገባ ታጥቦ የደረቀ እጥፍ አቡጀዴ አንጥፎ ከዚያ ገልብጦ እስቲበርድ ታግሶ ከላይም እጐናጥፎ በስራት መክደን ነው እድስት ከገባ ጀምሮ ተበልቶ እስቲያልቅ ከቢላዋና ከጭልፋ በቀር እጅ አይነካውም ንፋስና ውሀም አይወድም ለመብላት በሚያስፈልገው ልክ በቢላዋ ቀፈፍ አድርጎ በልኩ ውሀ ሲፈላ ጣል ማድረግ ነው ጥሩ ወጥ ይሆናል ።

፪ኛ የአሣ ስንቅ

አጥቦ በጠጅ አለቀልቆ ትንሽ ትንሽ ተፍትፎ በሽሀላ ምጣድ በደረቅ እንጨት በንጥር ቀበእያሉ እያነደዱ በሰንዴ ከክና በነጭ ሽንኩርት በዘይት ሆዱን ፍርከስ አድርጎ ፩ ጊዜ በልቡ፩ ጊዜ በጀርባው በቢላዋ እያገላበጡ ድርቅ እስቲል ጠብሶ ሲወጣ ሲቀርብ ቁንዶ በርበሬና ጨው በስራት ቀብቶ እገልባጣ እንቅብ ላይ እንዳይገናኝ እልፍ እልፍ አድርጎ ደርድሮ የሰንዴ ከክ ነስንሶ ቀን ነፋስ ከሚገባው ቤት ሌሊት እቡጀዲድ አልብሶ በውርጭ ፭ ቀን ማሰንበት ሲወጣለት ከዚያ ወዲያ ነፋስ በማያስገባ ሳጥን ንጹሕ እቡጀዲ አንጥፎ እንዳይገናኝ እልፍ እልፍ እያደረጉ ፩ ተርታ ዓሣ አንድ ነጠላ እቡጀዲ እንዲህ እያረጉ እያነባበሩ ሲሞላ ነፋስ እንዳያስገባ በሥራት ማኖር ውኃ አይወድምና ሲበላ ትኩስ ለማድረግ ብትፈልግ በመጥበሻ ዘይት አድርጎ ጥዶ ዘይቱ ሲቀልጥ ዓሣውን ጣል ጣል አድርጎ ሳይቆይ ማንሣት ነው ሳይጠበስም ጥሩ ነው። እኔ እንቺም ስንዘምት ከታኅሣሥ ፭ ቀን እስከ ፲ ቀን ተሠርቶ ይዤው የሄድኩትን ዓሣ በንመለስ ምንም ሳይለውጥ በ ፯ ወር በግንቦት አለቀ ይህንም ብዙ ሰው ቀምሶታል ።

ከ ፤ ቀ ከከሣ ሀብተ ወልድ ከቶራ መስክ ሰው

በአርበኞች የተበተነ በራሪ ወረቀት

በአንጻሩም የቪክቶር አማኑኤል ወኪል ዱካ ዳውስታ ሙሶሎኒን "አርበኞችን በፍቅር ብናስጠጋቸው ይሻላል" ብሎ አሳምኖ አዲስ አስተዳደር ጀምሮ ነበር። በዚሁ መሠረት ጣሊያን ከአርበኞች ጋር መደራደር፣ ገንዘብ መስጠትና ከበሬታ መስጠት ስለጀመረች፣ በባንዳነት ከጣሊያን ጋር ከሚሠሩት ይልቅ አሁን አርበኞቹ ገበርዲን እየለበሱ ከነሱ በበለጠ ክብር ይታዩ ጀመር። በዚህን ጊዜ አንዳንድ ባንዳዎች አርበኝነት የሚያስከብር መሆኑን ሲመለከቱ ወደ አርበኝነቱም የተቀላቀሉ ነበሩ።

በዚህ ሁኔታ ላይ ጣሊያን ከጀርመን ጋር ስላበረች እንግሊዝና ፈረንሳይ መልሰው ለጣሊያን ጠላት መሆናቸውን አርበኞች ሲሰሙ ተስፋ ማግኘት ጀመሩና ፍልሚያው ተባባሰ። አስከትሎም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሱዳን መምጣታቸው ሲሰማ አርበኛው እየበዛ ሄደ። የእንግሊዝ ዕርዳታ፣ የጃንሆይ በሱዳን በኩል መግባት መሰማት ሲጀምር ጣሊያኖች መበታተኑን ትተው በየትልልቅ ካምፖች ኃይላቸውን እያደራጁ መቀመጥ ጀመሩ። በአንጻሩም አርበኞቹ እንደልባቸው መገናኘትና በኅብረትም የጣሊያንን ካምፖች እያጠቁ ማሸነፍም ማባረርም ቻሉ። በጠቅላላው ድሉ ወደ ኢትዮጵያ ሰለዞረ የጣሊያን ወታደር ወዲያው ተሸነፈ። የጣሊያኖችን ተግባቢነት በመመልከት መጨረሻ ላይ የጣሊያን ወታደር ተሸንፎ እጁን ኒሰጥ ኢትዮጵያውያን ጭካኔ አላሳዩዋቸውም።

በነበረው ግብግብ ብዙ አርበኞች ቢሞቱም በየአካባቢው ተርፈው ዝና ካተረፉና ከነጻነት በኋላም በጣም ታዋቂ ከነበሩት መካከል በጣም ስማቸው የገነነ ቢኖርም በአርበኝነት ብዙ ጀግንነት የሠሩና ያልታወቁ ስላሉ በጠቅላላው የተዋጋው ሁኔታ ያመቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለኾነ ታሪኩ የጥቂት ሰዎች ብቻ አለመሆኑ ዕሙን ነው።

አንድ ሕብረተ ሰብ ከሌላ ሕብረተ ሰብ ጋር አብሮ መኖር ሲጀምር ብዙ የሚለዋወጠው የኑሮ ሁኔታ ይኖራል። ለምሳሌ ቱርኮች መካከለኛ ምሥራቅን ሲያስተዳድሩ ብዙ ዓይነት የአመጋገብ ስልት አስተምረው ሄደዋል። ከነዚሁም ተርኪሽ ኮፊ፣ ሽዋርማ፣ የሚባሉት ሁሉ የቱርኮች የባህል አመጋገብ ውጤቶች ናቸው። በኦስትርያ በሚኖሩበትም ወቅት ጥለውት የሄዱት ባህል አልፎ ተርፎ አውሮፓንም አጥለቅልቋል። ዛሬ ፈረንሳዮች የሚወዱት ክሯሳ የሚባለው ብስኩት ቱርኮች በጨረቃ ተምሳሌት ለቁርስ የሚጋግሩት ብስኩት ነው።



በኢትዮጵያም ውስጥ ሕዝቡ ከጣሊያኖች የአመጋገብ ልምድ እንደ ፓስታና ማክሮኒ ያሉትን መጀመሪያ ቢጠየፈውም እየለመደው ሄደ። ሻይ መጠጣትና ፋርኖ ወይም ፓኔ የሚባልም የዳቦ ዓይነት መብላት ተለመደ። ጣሊያኖችም አይናገሩት እንጂ ፒዛ የሚባለውን ምግብ ለመሥራትና ለዓለም ለማስተዋወቅ የቻሉት እንደቂጣ፣ አነባበሮና አምባሻ ከመሳሰሉት የኢትዮጵያውያንን የዳቦ አሠራር ተመልክተው ይመስላል። ይኸንንም የምልበት ምክንያት ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በፊት ፒዛ የሚባል ምግብ በጣሊያኖች የማይታወቅ ስለነበረና ጣሊያኖች የምግብ አሠራርን በብዛት ከውጭ ስለሚወስዱ ነው። እነሱ ለዓለም ያስለመዱት ምግብ ጀላቲ ወይም አይስ ክሪም የሚባለውን ብቻ ሲሆን፣ ጣሊያኖች ፓስታ የሚሉትን መደበኛ ምግባቸውን ማርኮ ፖሎ ወደ ቻይና በተጓዘ ጊዜ ቻይናዎች የሚሠሩትን ኑደልስ ዓይቶ አገሩ ሲመለስ ስላስለመዳቸው ነው።



# ምዕራፍ ፳፱

# የድል ጉዞ ወደ አገር ቤት


አዛዥ ከበደ ተሰማ የጃንሆይን መምጣት ለአርበኞች እያበሠሩና መንገድ እየጠረጉ በጎንደር አድርገው ወደ ጐጃም ገቡ። በየመንገዱ የገጠማቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ሪፖርት እያደረጉና ሊደረግ የሚገባውን እየጠቆሙ ወደ መሃል ዘለቁ። አስፈላጊ ሲሆንም ትናንሹን ጉዳይ ራሳቸው ውሳኔ እየሰጡበት የተቃረኑትን አርበኞች እያስማሙና እያስታረቁ ጥሩ ሥራ ሠሩ። አብሯቸው ይጓዝ የነበረው የእንግሊዝ ኮሎኔል ሳንድፎርድ ሁሉም ነገር ከሱ ቁጥጥር ውጭ መሆኑ ስላላስደሰተው ማልታ ሊገባ ፈልጎ ቢሞክርም የተወሳሰበ ስለኾነ ሊገባው ባለመቻሉ እንዲሁም ለአዛዥ ከበደ የሚሰጠውን ክብር ሊያገኝ ስላልቻለ መጨረሻ ላይ ዝምታን መርጧል።

ንጉሠ ነገሥቱ በአሜድላ አድርገው ወደ ጐጃም ተጉዘው ደብረ ማርቆስ ሚያዝያ 22 ቀን 1933 ዓ.ም ገቡ። ጎንደርን ትተው በጐጃም መምጣትን የመረጡት የጎንደር አርበኞች እና ደጃች ታከለ ወልደ ሃዋርያትና ሌሎችም "የሸሸ ንጉሥ አይነግሥም ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም" ብለው ተቃውሞ አሳይተው ስለነበረ ነው። ነገር ግን እንደነ ኒጋሽ በዛብህ፣ ኃይሉ በለው፣ መንገሻ ጀምበሬና አሞራው ውብነህ ያሉት ንጉሡን ይደግፉ ስለነበረ ጐጃም ድረስ ሄደው ተቀብለዋቸዋል።

እንግሊዞች በጎንደር አድርገው ወደ ኤርትራ ተሸቀዳድመው ገቡ። ከደቡብ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር በሐረር በኩል ተንደርድሮ አዲስ አበባ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ገብቶ በላይኛው ግቢ የብሪታኒያን ባንዲራ (ዩኒየን ጃክ) በታችኛው ግቢ ደግሞ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውለበለበ። በዚሁ ዕለት ማታ በፊት ለፈረንጆች ብቻ በተወሰነው ጊዮሳ ባለው ትሪያኖን ሆቴል ቤት ኢትዮጵያውያን የማሊያንን ድል



መሆን በመመልከት በደስታ ተንጋግተው መግባት ሲጀምሩ የነበሩት አሳላፊዎች አንታዘዝም በማለታቸው አለመግባባት ተፈጠረ።



ጃንሆይ አሜድላ ላይ ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ

በዚህ ምክንያት እንግሊዞች ትጥቃቸውን ካልፈቱ ማሊያኖች ጋር በመወገን በአካባቢው ባገኙት ኢትዮጵያዊ ላይ ሁሉ መተኮስ ጀምረው የቆሰለው ቀስሎ 150 ሰው ተገደለ። ይህም ስለሆነ ብዙ ሰው ቅር ብሎት የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት በጉጉት መጠበቅ ጀመረ። ተንጉሠ ነገሥቱ ግን ማሊያን አዲስ አበባ የገባበትን ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ጠብቀው በክብር አዲስ አበባ ገቡ። የደርግ መንግሥት ግን የጃንሆይን ታሪክ ለማሳነስ ሲል እንግሊዞች አዲስ አበባ የገቡበትን ቀን እንደ ነፃነት በዓል ለ17 ዓመት ሲያከብር ቆየ። ኢትዮጵያዊ መሪ በቦታው ሳይኖር የወጭ ኃይል ሥልጣኑን እያዘዘበት ባለ ሁኔታ ላይ የነፃነት ቀን መባሉ ትክክል አይመስልም ነበር።

ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ ላላችሁ ፡ ታማኞችና ፡ ነፃ ፡ የሆናችሁ ፡ ኢትዮጵያውያን ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ያሉት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ሁሉ ፡ እጃቸውን ፡ ሰጥተዋል ። የቀረ ፡ ጦራቸውም ፡ ወደ ፡ ምዕራብና ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ሸሽቷል ፤ አሁን ፡ አዲስ ፡ አበባ ሰላም ፡ ሆኗል ። የኢትዮጵያ ፡ ባንዲራም ፡ እንደገና ፡ በግቢ ፡ ላይ ፡ ትውለበለባለች ።

በአዲስ ፡ አበባና ፡ በቅርቢያው ፡ ያሉት ፡ ኢጣልያኖች ፡ እጃቸውን ፡ ሰጥተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከአገሬችሁ ፡ ከየክፍሉ ፡ ገና ፡ ማስወገድ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ብዙ ፡ የኢጣልያን ፡ ወታደሮች ፡ አሉና ፡ በለዚህ ፡ አገር ፡ ወዳጅና ፡ አፍቃሪ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ አገሩን ፤ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ እርዳታውን ፡ ሳያቋርጥ ፡ እንዲሠራ ፡ ያስፈልጋል ። ከናንተ ፡ ውስጥ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ በሰሜንና ፡ በምሥራቅ ፡ የሚኖሩቱ ፡ ኢጣልያኖችን ከደብረ ፡ ብርሃንና ፡ ከደሴ ፡ መኸከል ፡ ይውጓቸው ፤ አደጋም ፡ ይጣሉባቸው ።

በምዕራብና ፡ በደቡብ ፡ ባሉት ፡ የምትኖሩትን ፡ ባለቀምትና ፡ በጅማ ፡ በሆሉ ፡ ባለው ፡ ወረዳ ፡ ኢጣልያኖችን ፤ ይወጓቸው ፡ ኢጣልያኖችን ፡ ተከታትለው ፡ ለማጥፋት ፡ የሚሔዱ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮችና ፡ ከሚያኖች ፡ የመሰሉ ፡ ላይ ፡ አትተዘሱባቸው ።

ጃንሆይ ፡ በጎጃም ፡ ነው ፡ ያሉትና ፡ የኢጣሊያንን ፡ ጦር ፡ በፍጹም ፤ አለቀ ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ከተማቸው ፡ እንዲመጡላችሁ ፡ እናንተ ፡ ሁላችሁ ፡ በያላችሁበት ፡ የኢጣሊያንን ፡ ጦር ፡ እያደከማችሁ ፡ ውጉት ፡ ሚያዝያ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ።

የእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፤
አ ፡ ቢ ፡ ከኒንግሃም ።

*April 9th 1941*

A. B. CUNNINGHAM. LT. GEN.

D. A. P. - ADDIS ABABA - 2000-3

በካኒንግሃም የተበተነ በራሪ ወረቀት

የአዲስ አበባ አገባባቸው ሥነ ሥርዓት ሲወጠን አንዱ "በነጭ ፈረስ"፣ ሌላው "በመኪና ይግቡ" እያለ ሃሳብ ሲያቀርብ ጃንሆይ "በመኪና ነው የምንገባው!" በማለታቸው ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ግልጥ አልፋ



ሮሚዮ መኪናቸውን አቅርበው በእዚያ ተሳፍረው በአርበኞች ታጅበው በደመቀ ሰልፍ መካከል ወንዱ በሆታ ሴቱ መሬት እየሳመ በእልልታ ተቀበላቸው።



ጃንሆይ መናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ ሲገቡ

ሃበሻ ሁለት ነጭ ታይገቡም አይቀር
አንደኛው በፍቅር አንደኛው በጦር
ሼህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፳፫

## ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት መልስ

ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት እንደተመለሱ አስተዳደሩን እንደገና ማስተካከል ሲጀምሩ በርካታ ሳንካዎች አጋጥሟቸው ነበር። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ:-

1ኛ የአርበኞች፣ የባንዳዎችና የስደተኞች አለመግባባት
2ኛ የገንዘብ አለመኖርና የእንግሊዞች ጣልቃ ገብነት ነበሩ።

## የአርበኞችና የስደተኞች አለመግባባት

ከስደት መልስ ንጉሠ ነገሥቱ አስተዳደሩን ሲያመቻቹ ሹመት ላይ ውዝግብ መነሳት ጀመረ። አርበኛው "እኛ በሞትንበት ማን ይሾማል" ሲል ስደተኛው ደግሞ "ይኸ ያልተማረ፣ ቋንቋ የማያውቅ፣ ጫካ የከረመ፣ ባላገሩን ሲዘርፍና ሲያስለቅስ የኖረ ምን አስተዳደር ያውቃል" ብሎ ያናንቀው ጀመር። በሌላ በኩል በባንዳነት ብዙ ትምሕርት ያገኘ፣ ቋንቋ የሚያውቅና የሥራ ልምድ ያካበተ ሹመት የሚገባው ለእኔ ነው ማለት ጀመረ። ይህንን ችግር ለማስወገድ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ "አራት መደብ የምትችል ቀርበህ ተፈተን" ብለው ሲያስታውቁ ስደተኛና ባንዳ ፈተና እያለፈ ሥራ ሲይዝ አርበኞች ሥራ ፈት ኾነው ቀሩ። በዚህ አጋጣሚ ብዙ ኤርትራውያኖች ለጣሊያኖች በረዳትነት ያገለግሉ የነበሩ ሥራና ሃብት ሲያገኙ የጋሪ ነጅነቱንም ሥራ በብዛት ተሠማሩበት። እንዲሁም ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ስደተኛ ስለነበሩ ሌላ ስደተኛ ወይም ባንዳ በሾሙ ቁጥር በአርበኞች ዘንድ አደሉ እየተባሉ ታሙ።



ለተለያዩ የሹመት ቦታዎች የተለያዩ መመዘኛዎች ስለሚያስፈልጋቸው አንዳንዱ በተወላጅነት ሌላው በትምህርት አለበለዚያም በጀግንነትና በተለየ ሙያ ስለሚሆን አመራረጥ ላይ ከፍተኛ ጥበብንና ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነበር። ለምሳሌ የአገረ ገዥነት ሹመት በብዛት በተወላጅነት የሚወሰን ነበር።



ጃንሆይ በቤተ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ

የሹመቱ ድልድል በጣም ለተወሰኑ አርበኞች ሥፍራ ሲሰጣቸው ለብዙ ባንዳዎችና ስደተኞች ሥልጣን አጎናጽፏቸዋል። በዚህም የተነሳ በባለሥልጣኖች መካከል ጎራ እየተለየ መናቆርም ተጀምሮ ነበር። ብዙ ባንዳዎች በጃንሆይ መንግሥት ባለሥልጣን ለመሆን በመቻላቸው ቅሬታ ያቆሩ ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃል። ሆኖም ብዙ ሰው መናገር ስለማይደፍር በሆዱ ሲይዘው እንደ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ያሉ የቋንቋ ስጦታ የነበራቸው ሰዎች ደግሞ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ መግለጽ ችለዋል። ሌላው ትልቁ ቅሬታ ጣሊያን ሠርቶት የሄደው ቤት በግል ባለቤትነት ሲታደል በድልድሉ ጊዜ በብዛት ለስደተኞችና ለባንዳዎች በመሰጠቱ ነው። ቤት ከደረሳቸው መካከል ኤርትራውያኖችም ነበሩበት። ጣሊያን ከሠራቸው ቤቶች መካከል

በርካታዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ ካዛንችስ አካባቢ የሚገኙ ሲሆን በኋላ በችሮታ ከተሰጡት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

<u>የንጉሣውያን ቤተ ሰብና መሳፍንት</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | ራስ እሥራት ካሣ | ስደተኛ ተማሪ |
| 2ኛ) | ራስ ገ/ሕይወት ሚካኤል | የእ/መነን አጎት |
| 3ኛ) | ልጅ ደስታ ብርሃነ መስቀል | የራስ ካሣ የልጅ ልጅ |
| 4ኛ) | ልጅ አርአያ አበበ | የጃንሆይ ዘመድ |
| 5ኛ) | ኮሎኔል አበበ ወልደ ሥላሴ | የጃንሆይ የክርስትና ልጅ |

<u>በንጉሡ የተቸሩ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | አቶ በለጠ ገብረ ጻድቅ | ስደተኛ |
| 2ኛ) | አባ ማርቆስ ኢጋጅየለው | ስደተኛ ካህን |
| 3ኛ) | አቶ መንበረ ያየህ ይራድ | ስደተኛ |
| 4ኛ) | አቶ ገብረ አብ ቢያድግልኝ | |
| 5ኛ) | ወ/ሮ ፈለቀች | ስደተኛ |
| 6ኛ) | አቡነ ዮሐንስ | ባንዳ |
| 7ኛ) | አቶ አበበ ረታ | ስደተኛ |
| 8ኛ) | አቡነ አብርሃም | ባንዳ |
| 9ኛ) | ጄኔራል ኃኘው ከበደ | |
| 10ኛ) | አቶ አባተ | |
| 11ኛ) | ብላታ ዘውዴ በላይነህ | ስደተኛ |
| 12ኛ) | ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ | ዲፕሎማት |
| 13ኛ) | ቢትወደድ አስፍሃ ወልደ ሚካኤል | የጣሊያን አስተርጓሚ |
| 14ኛ) | አቶ አካለ ወርቅ ሃብተወልድ | ስደተኛ |

<u>ለኤርትራውያኖች የተሰጠ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | አቶ ዓውአሎም ፈካክ | |
| 2ኛ) | አቶ ዘካርያስ | |
| 3ኛ) | ደጃች ተድላ ባይሩ | |
| 4ኛ) | ራስ ኃይለ መለኮት | |
| 5ኛ) | ብ/ጌታ ኤፍሬም ተ/መድህን | ስደተኛ |
| 6ኛ) | ጄኔራል ያዕቆብ ገ/ልዑል | ስደተኛ |
| 7ኛ) | ጄኔራል ኢያሱ መንገሻ | ስደተኛ |
| 8ኛ) | አፈ ንጉሥ ሐጎስ | |
| 9ኛ) | አቶ ጳውሎስ ብርሃኔ | |
| 10ኛ) | አቶ ጴጥሮስ ጎይቶም | |

<u>በአርበኛነትና በመሳሰሉት ለአገር ውለታ የሠሩ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | ወ/ሮ ቆንጂት | የራስ አበበ ባለቤት እስረኛ |
| 2ኛ) | ብ/ ጄኔራል ኃ/ማርያም ግዛው | ስደተኛ |
| 3ኛ) | ራስ እምሩ ኃ/ሥላሴ | አርበኛ/እስረኛ |



| | | |
|---|---|---|
| 4ኛ) | ደጃዝማች አሉላ በቀለ | አርበኛ |
| 5ኛ) | ደጃዘማች አልማው | አርበኛ |
| 6ኛ) | ልጅ ዳንኤል አበበ | እስረኛ |
| 7ኛ) | ደጃዝማች ገብረ ኪሮስ | አርበኛ |

<u>እንዲሁም በላይ ዘለቀ መንገድ (ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ) አካባቢ የጣሊያን ፖለቲካ ቢሮ ጽሕፈት ቤቶችን</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | ደጃች መኮንን ደስታ | ስደተኛ |
| 2ኛ) | ወ/ሮ ሙስወርቅ ባንት ይርጉ | |

የተቀሩት ለኤርትራውያኖች ቢሰጡም መጨረሻ ላይ ግን ምትክ ቦታ እየተሰጣቸው ቤቶቹ ተመልሰው ለመንግሥት መሥሪያ ቤትነት ውለዋል።

በተጨማሪም ባንኮ ዲ ናፖሊ የነበረበት ፎቅ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በአጠገቡ ያለው ፎቅ ለደጃዝማች ከበደ ተሰማ ተሰጥቶ ነበር። ይህ ፎቅ አሁን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሃይጅንና የፋርማሲ መምሪያዎች ሆኗል። ኢትዮጵያ ሆቴል አጠገብ የአንበሳ ቡና ቤት ያለበት ፎቅ የልዑል ማህለ ሥላሴ ነበር።

ሊሎችም የታወቁትን ቤቶች ለመግለጽ ያህል የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጣሊያን ሠርቶት በሆቴልነት ሲያገለግል ከኖረ በኋላ ለልዕልት ተናኘ ወርቅ ተሰጥቶ መንግሥት ኪራይ እየከፈላቸው ይገለገልበት ነበር። ልዕልት ተናኘ ወርቅ ብዙ ንብረት የተሰጣቸው ስለነበሩ በጣም ባለጸጋ ሆነው እንደነበር ይታወቃል። አልፈው ተርፈው ወንዶ ገነት የተባለውን የሽርሽር ቦታ ልዕልት ተናኘ ስለወደዱት ጃንሆይን ጠይቀው ሚስተር ማታኖቪች ከሚባሉ በስደት ከምስራቅ አውሮፓ መጥተው በኢትዮጵያዊነት ከሚኖሩ ግለሰብ ተወሰዶ ተሰጣቸው። ለሚስተር ማታኖቪች በምትክ የተሰጣቸውንም ቦታ ደርግ ስለወረሰባቸው እኚህ ሰው አንድ ዓይና ስለነበሩ በአንድ ዓይናቸው አለቀሱ ይባላል። ሚስተር ማታኖቪች ኢንጂኔር ስለነበሩ የቀይ ባሕርን ከሩዶልፍ ባሕር ጋር በማገናኘት መርከብ እንዲሄድበት ለማድረግና 300 ግድብ በመሥራት አገሪቱን ከችግር ለማውጣት ዕቅድ አውጥተው በጃንሆይና በደርግ ዘመን የሚሰማቸው አጥተው ነገሩ ትኩረት ሳያገኝ ቀረ።

አርበኞች ግን ያገኙት ነገር ኢምንት ሲሆን እንዲያውም ከራስ አበበ አረጋይ ወታደሮች በከፊል ወደ ሸዋ ሮቢትና ወደ አርሲ ተልከው የእርሻ መሬት አከፋፍለዋቸው እያሰ በወባ በሽታ (በንዳድ) አለቁ። ጥቂት አርበኞች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ በየባለገሩ በምስለኔነት፣ በወረዳና በአውራጃ ገዥነት እየተሾሙ ተበታተኑ። ብዙዎቹም በማዕረግ ስምና በሜዳልያ ብቻ ተሸንግለዋል። የሚያሳዝነው የሴት አርበኞች ጥቂቶች ብቻ ሜዳሊያ ሲያገኙ የማዕረግ ስም እንኳን አለማግኘታቸው ነው። ወ/ሮ ከበደች ሥዩምና ወ/ሮ ቀለመ ወርቅ ጥሩነህ በአርበኞቹ የደጃዝማችነት ማዕረግ ቢለገሱም በመንግሥት ስለአልጸደቀላቸው በማዕረጉ አልተጠሩበትም። ስለሆነም አንድም ደጃዝማች ወይም ፊታውራሪ ወይም ቀኝ አዝማች የምትባል ሴት አርበኛ አልነበረችም። ይሁንና አርበኞች ለከፈሉት መስዋዕትነት የሚገባቸውን ወሮታ እንዳላገኙና እንደተጎዱ ስለቀሩ ክፉኛ አማረሩ። የአርበኞቹን ቅሬታ ለመግለጽ ዮፍታሄ ንጉሤ የሚከተለውን ተቀኙ።

> "አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ
> የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ"

አንድ ሰው አገሩ ስትወረር መዋጋት ግዴታው ነው። የሚዋጋውም በገንዘብ ወይም በንብረት ለመካስ ስላልኾነ ከነፃነት በኋላ አስተከፈለኝም ብሎ መናደድ ተገቢ አይደለም። ሆኖም የጠላት ንብረት ለግለሰቦች ከታደለ ቅድሚያ ለአርበኞች መስጠት ፍትሃዊ ይሆን ነበር።

## የብሪታንያ ጣልቃ ገብነት

ብሪታንያ ኤርትራንና ኦጋዴንን ከመያዝ በተጨማሪም በቅኝ ግዛቶቻቸው ጠረፍ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ አገር እየቆረሱ ወሰን ማስፋት ጀመሩ። በገለብ በኩል የተወሰደው መሬት ኢትዮጵያን ከሩዶልፍ ሃይቅ ተጠቃሚነት አግልሏታል። እስከ አሁንም ድረስ ቦታው በኬንያ ውስጥ እንደተከለለ ነው። በዚህም ምክንያት የገለብ ሕዝብ አኩርፎ ንጉሠ ነገሥቱ ስጉብኝት በሄዱ ጊዜ በባላባታቸው በፊታውራሪ ነመርሙስ



ከስከስ አማካይነት "ምነው አገራችንን ቆርሰህ ሰጠህ? አሁንስ የቱን ልትሰጥ ነው የመጣኸው?" ብሎ ጃንሆይን አሳፍሮ መልሷቸዋል።



የብሪታንያ (እንግሊዝ) ወታደሮች

አፄ ምኒልክ በገለብ በኩል ናስማስር (ውጅግራ) ጠብመንጃ ከጋሻ ጋር አድርገው በሲሚንቶ የቀበሩት የድንበር ምልክት ኬንያ ውስጥ 40 ኪሎ ሜትር ያህል ገብቶ ይገኛል። ስለኾነም የገለብ ሰዎች አሁን ዘመን ድረስ እንደመሪያቸው የሚቆጥሩት ምኒልክን እንጂ ሌላ መሪ አያውቁም። በዚህም የተነሳ አሁን ድረስ ሲምሉ 'ምኒልክ ይሙት!' ይላሉ። አንድ ወቅት የገለብ ባላባት ፊታውራሪ ነመርሙስ ከስከስ የእንግሊዝ አይሮፕላን ወሰን አልፋ ስትበር ተመልክተው በአንድ አልቤን ጥይት መተው ጥለዋት ፓይለቱን ከማረኩት በኋላ በምሕረት ለቀውት ወደ ኬንያ እንደተመለሰ ይታወቃል።

በሞያሌ በኩል አሁን በከፊል ኬንያ ውስጥ የኾነው የአየር ማረፊያ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ እንደነበረ ይነገራል። ከዚህም ሌላ በወሰኑ አካባቢ የነበሩ ጠቃሚ የሆኑ ቦታዎች በብሪታንያ ተወስደው አሁን በኬንያ ግዛት ውስጥ ተጠቃልለዋል። በፊት የአካባቢው ሰዎች ፊታቸውን የሚቀቡት የተለየ አፈር ያለበት አንድ ተራራ አሁን ኬንያ ውስጥ ስለተከለለ የአካባቢው ሰዎች ያንን አፈር ከኬንያ እየገዙ መጠቀም ተገደዋል። በፊት ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የቱርጋና ጎሣ በወሰን መገፋት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ለሦስት ተከፍሎ የኢትዮጵያ

ቱርጋና፣ የኬንያ ቱርጋናና የሱዳን ቱርጋና ተብለው ይጠራሉ። እንደዚሁ ሁሉ በሱዳን በኩል መሬት ከኢትዮጵያ በየምክንያቱ እየተወሰደ በአሁኑ ወቅት በምሥራቅ ሱዳን ወሰን አካባቢ የአማርኛ፣ የኦሮምኛና የትግርኛ ተናጋሪ ሕዝብና የቦታ ስም ይገኛል።

በተደጋጋሚ ሱዳኖች (ደርቡሽ) ከአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ በውስጥ ችግር ስትጠመድ የወሰን ጭቅጭቅ እየፈጠሩ እንደምንም ብለው መሬት ለማግኘት ይሞክራሉ። በ1952 ዓ.ም ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰው የጋምቤላ አውራጃ ምትክ በስሜን የሚገኘውን የሰቲት ሁመራ አካባቢ ለሱዳን እንዲሰጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲመከሩበት ሲደረግ ሃሳቡ ገና እንደተነሳ የጎንደር ተወካይ ሽጉጡን አወጥቶ ማን ነው መሬታችንን ቆርሶ ለባዕድ የሚሰጠው ብሎ ተቆጣ። በዚሁ ምክንያት ጉዳዩን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲቆይ አደረጉት። እንደ እውነቱ ከኾነ ከሰላ የምትባለው ከተማና የሁመራ መሬት በጠቅላላው ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ እንደነበረና እንግሊዝ ወስዶት አፄ ዮሐንስ ለማስመለስ ቢሞክሩም አልቻሉም።

የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሰምተው ከጣሊያን እየከዱ ወደ ሱዳን የመጡትን ኢትዮጵያውያን እንግሊዞች በማሰር ሰብአዊ ርህራሄ በሌለው መልኩ ያጉላሏቸው ነበር። ከጣሊያኖች ጋር ሆነው የተማረኩትንና ንጉሡን ፍለጋ ከድተው በመጡት ወታደሮች መካከል ምንም ልዩነት አይደረግም ነበር። የኢጣሊያን ምርኮኞች ግን በተሻለ እንክብካቤ ይያዛሉ። እንዲያውም ጣሊያኖቹን ሥልጣን እየሰጡ አስተዳደር ላይ ሲያስቀምጧቸው ከኢትዮጵያውያን ጋር በሚፈጠር አለመግባባት ተደማጭነት የነበራቸው እነሱ ሆነው ተገኙ። አንድ ጊዜ ጣሊያኖቹ እንግሊዞቹ ፊት ሰባት ኢትዮጵያውያንን በጥይት ሲገድሉ ምንም አልተደረጉም። በዚህ ቅሬታ ሱዳን ውስጥ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያንና የብሪታንያ ባንዲራ ይዘው ሠላማዊ ሰልፍ በካርቱምና በሌሎችም ከተሞች ስላደረጉ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት እንዲበረበር ተደርጎ የግል ንብረታቸውን በወታደሮች ተዘርፈዋል[17]።

[17] ያቺ ቀን ተረሳች ከሕይወት ጎዳና



በኬኒያ የነበሩትን የኢትዮጵያ ስደተኞች እንግሊዞች እያሰሩ መንገድ ያሠሯቸው ነበር። በኋላም አገራቸውን ነፃ ለማውጣት ሲሰበሰቡ እንግሊዞች በየወሰናቸው ላይ ጣሊያኖች እያጠቁ መሬት መያዝ ጀምረው ነበርና መጀመሪያ የእንግሊዝን ጦርነት ኢትዮጵያውያን እንዲዋጉላቸው አድርገው ካጠናቀቁ በኋላ አብረዋቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምቱ አድርገዋል። በጠቅላላው ስንመለከተው እንግሊዞች ሊረዱን ይሁን ከጣሊያኖች ተረክበው ሊገዙን የመጡበት አኳኋን ግልጽ አልነበረም።

ጣሊያኖች ከተሸነፉ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ብሪታንያ በየቦታው የፖለቲካ መኮንኖች በመሾምና በጦርነት ወቅት ምክትል አስተዳዳሪ የነበሩት ብርጋድዬር ላሽ ጃንሆይን ቢሮአቸው ድረስ እንዲመጡ እንደማዘዝም ሞክረው ነበር። እንረዳለን ብለው የመጡት እንግሊዞች የኢትዮጵያን መንግሥት ምሥረታ ዕውቅና ላለመስጠት የጠላት ይዞታ አስተዳደር (Enemy Occupied Territory) በማለት እየጠሩ ራሳቸው አስተዳደሩን ሊያዙበት ፈልገው ነበር። ከቃላቶቹ እንደምንረዳው የመጡት እኛን ለመርዳት ሳይሆን ጣሊያን በወቅቱ የእነሱ ጠላት ስለነበረ እሱን በኢትዮጵያ ምድር ለመውጋት ነበር።

ከዚህም በላይ የተሾሙት የብሪታንያ ኦፊሰሮች ንብረት መዝረፍን ትልቅ ዓላማ አድርገው ይዘውት ስለነበረ በተለይ የማርትሬዛ ብርና ወርቅ ሲገኝ ለመውሰድ ይታገሉ ነበር። በተጨማሪም አዲስ አበባ ውስጥ የግሪክ ዝርያ ያላቸውን ሰብስበው አንድ "የዘበኛ ኃይል" የሚባል ጓድ ፈጥረው በየሰው ቤት በኃይል እየገቡ የጠላት ንብረት ነው በማለት የቤት ዕቃ ይወስዱ ነበር[18]። ይሁንና በየቦታው በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ኃላፊነት የተሰጣቸው ሹሞች የተቻላቸውን ያህል ተከላክለው አድነዋል።

ከታሪክ ማኅደር እንደምንረዳው ትልቁ አሌክሳንደር ንግሥት ሕንደኬ ሦስተኛን ሊያገባ ድርድር ጀምሮ ጋብቻው ሳይሳካ ሞተ። በዚህ ምክንያት ተፈጥሮ በነበረው መግባባት ግሪኮች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ መልክ በብዛት አክሱም ላይ ተንሰራፍተው ነበር። በአክሱም ቤተ መንግሥትም የግሪክ ቋንቋ ተለምዶ ነበር።

[18] ያቺ ቀን ተረሳች ከሕይወት ጎዳና



ጃንሆይ ከእንግሊዝ የጦር መኮንኖች ጋር

ራስ ተፈሪ መኮንን በአልጋ ወራሽነት በ1916 ዓ.ም ኢየሩሳሌምን በመጎበኝት ላይ እያሉ "ግሪኮች በጎልጎታ ውስጥ ብዙ ክፍል ቦታ አሏቸው ማለትን ስለሰማን ከዚሁ አንድ ክፍል ለኢትዮጵያ መነኮሳት መቀደሻ ርስት አድርገው እንዲሰጡልን አዲስ አበባ በሚኖረው በግሪክ ቆንሲል ጄኔራል በዶክተር ዘርቦስ በኩል በኢየሩሣሌም ያሉትን የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ አቡነ ድምያኖስን ብንጠይቅ የአብርሐም ገዳም ከሚባለው አንድ ክፍል ርስት አድርገን እንሰጣለን ስላሉ እኛም በበኩላችን ለግሪክ ገዳም ጥቅም የሚሆን ቦታ ኢትዮጵያ ላይ እንሰጣለን ብለን በሃሳቡ ተስማምተንና ተዋደን ቀጥሎ ያለውን ውል ተጻጽፈን ተፈራረምን...ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሳይሆን ቀርቶ ይህ ውል ወደ ፍጻሜ አለደረሰም" የሚለው በሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 64 እስከ 66 ላይ ይገኛል። በዚህ ባልጸደቀው ውል መሠረት ለግሪክ መነኮሳቶች ሳይሆን አገር



ውስጥ ለገቡ ግሪኮች ሁሉ አዲስ አበባ ከራስ መኮንን ድልድይ አንስቶ በአርበኞች መንገድ እስከ ገፈርሳ ድረስ መሬት እየተሰጣቸው የበረዶ፣ አረቄና የሻከላ ፋብሪካዎች እየከፈቱ ሃብታም መሆን ጀመሩ። ቀጥሎም በአምቦ መስመር ነቀምትና አልፎም ደምቢ ዶሎ ድረስ መሬት ተመርተው መኖር ጀመሩ። እነሱም ተስፋፍተው ኢሉባቦር፣ ጋምቤላ፣ አሶሳና ቤኒ ሻንጉል ድረስ ገቡ።

ግሪኮች በማይጨው ጦረነት ላይ ቀደም ብሎ ለጣሊያን በሰላይነት፣ በወረራውም ወቅት እንደገና ተንሰራፍተው በመነገድ፤ እንግሊዝም ሲገባ እሱ ባቋቋመው የዘበኛ ኃይል ውስጥ በመሰለፍ በዘረፋ ተሰማርተዋል። ከጦርነቱ በፊትም ሆነ በኋላ ደርግ ንብረታቸውን እስከውረሰባችው ጊዜ ድረስ ንግዱን በመቆጣጠር ነጋዴዎች በመሆን በሠላም ኖረዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ከኢትዮጵያ ወጥተው ሄደው ጣሊያን አገር እንደገና ሹመታቸውን እንዲያጸድቅላቸው ደጅ ጥናት ላይ ነበሩ። በመጨረሻ ስላልተሳካላቸው አገራቸው ግብጽ ሄደው ተቀመጡ። ጦርነቱ ሲያልቅ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ግን ኩባዊው ኮሎኔል አልሽንድሮ ዴል ባዬ ከራስ ሙሉጌታ ጋር ዘምቷል። ስዊድናዊው ካርል ጉስታቭ ቮን ሮዝን መጥተው በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ሥር አባ ቃኘው የሚባል የቀይ መስቀል ፎከር አይሮፕላን ተረክበው ቁስለኞች በማመላለስ አገልግሎት አበርክተዋል። ከወረራው በኋላም የኢትዮጵያን አየር ኃይል አቋቁመዋል። በደርግ ዘመነ መንግሥትም አገራቸው ሰዊድን እያሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ረሃብ ሲገባ ተመልሰው መጥተው ዕርዳታ ላይ ተሠማርተው ኦጋዴን ውስጥ ከመቶ አለቃ ዳዊት ኃይለ አብና የስዊድኑ ፓይለት ሚስተር ክርስቲያን ክርስትንሰን ጋር በአይሮፕላን አደጋ ኦጋዴን ውስጥ ሞቱ።

የሩሲያው ንጉሥ ዳግማዊ ኒኮላስ እ.ኤ.አ. በ1917 ተገድሎ ሥልጣኑን ኮሚኒስቶች ሲረከቡ የአርመን ዜጎች በዓለም ተበተኑ። ኢትዮጵያ ውስጥም ብዙ አርመኖች መጥተው አገሬ ነው ብለው ተቀመጡ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ከእንግሊዝ ኤምባሲ አንስቶ እስከ ራስ መኮንን ድልድይ ድረስ ግራና ቀኙን መሬት መርቷችው በንግድ ሥራ ተሠማርተው ይኖሩ ነበር። ከቀን ብዛት ብዙዎቹም አማርኛ

አቀላጥፈው መናገር በመቻላቸው በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የታወቁ ከበርቴዎች ሆነው ነበር። የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን፣ ትምሕርት ቤትና የስፖርት ክበብ አቋቁመው ይኖሩ ጀመር። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ አርመኖቹና ሌሎችም በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ሕንዶች፣ ፓኪስታኖችና እሥራኤሎች ንብረታቸውን በደርግ መውረስ ሳቢያ ወደ ሌሎች አገሮች ተሰደዱ።

በዙዎች የውጭ አገር ሰዎች ከኢትዮጵያዊ ሴቶች ልጅ ይውለዱ እንጂ ሴቶቻቸው ግን ኢትዮጵያዊ ባል አያገቡም ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች ከአርመኖች፣ ከሕንዶች፣ ከግሪኮችና ከአረቦች መካከል ለኢትዮጵያ ነፃነት የታገለ አልተገኘም። ዶክተር ጂ. ዳሲዮስ የሚባለው ግሪካዊ ግን በዓለም ቀይ መስቀል አባል በመሆን ከስዊድኖች ጋር በመምጣት ዶክተር ነኝ ብሎ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ከጦርነቱም በኋላ በዚሁ ሙያ ሲኖር የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር የነበሩት ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ በአገር ውስጥ ያሉትን የነጭ ህክምና ዶክተሮች ማስረጃ ሲያስመረምሩ እሱም ሆነ ከሌሎቹ ነጮች መካከል ብዙዎቹ ዶክተር ሆነው አልተገኙም።

በተጨማሪም እንግሊዞች የጠላትን (የጣሊያንን) ንብረት መዝረፍ ብቻ ሳይሆን ነባር የኢትዮጵያን ንብረቶችንም እየነቀሉ መውሰድ ሲጀምሩ ከአርበኞች ጋር በተፈጠረው ጠብ እስከ ጦር መማዘዝ ተደርሶ ነበር። የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን መሣሪያዎች ነቅለው ሊወስዱ ሲሉ አርበኞች ራስ መኮንን ድልድይ ሥር መሣሪያ ጠምደው በማድፈጥ አስጥለዋቸዋል። ዘረፋው የግል መኪናዎችንና ሊንቀሳቀስ የሚችልን ብረታ ብረት ጭምር ያካተተ ነበር። ይባስ ብሎ አዲስ አበባ ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ጣሊያኖች በሙሉ መኪናቸውን እያሽከረከሩ ጃንሜዳ እንዲሰበሰቡ ካደረጉ በኋላ ቁልፉን መኪናው ላይ እየተው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አዝዘው መኪናውን ወደ ኬንያና አልፎም እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ አግዘውታል። ሊወስዱት ያልቻሉትን መኪናና ብረታ ብረት ኢትዮጵያ እንዳትጠቀምበት በባሕር ውስጥ ጨምረዋል። በየቦታው ባሉ ሃይቆችና ኩሬዎች በተለይ በአዋ ወንዝና በቢሸፍቱ ሃይቅ ውስጥ የከተቱት በርካታ ያለ መኪናና ብረታ ብረት አሁንም እንደሚገኝ ይታመናል።



በኤርትራ ውስጥ ያደረጉት ዘረፋና ውድመት ደግሞ በጣም የከፋ ነበር። አሁን የኡምድሩማን ሬዲዮ ጣቢያ ከኤርትራ ነቅለው የወሰዱት ሲሆን በምሥራቅ አፍሪቃ በጣም ትልቁና ዘመናዊው ዳቦ መጋገሪያ ከምጽዋ ተነቅሎ ተወስዷል። ከምጽዋ አሥመራ የተዘረጋው የዕቃ ማመላለሻ ቴሌፌሪክ የሽቦ መስመር ወላልቆ ሲወሰድ የቀረውም እንዳይሠራ ተበጣጥሷል። ሊወስዱ ያልቻሉትን ብረታ ብረት ቀይ ባሕር ውስጥ ጭምረውታል። ተንሳፋፊ የመርከብ መውረጃና መውጫ ከኤርትራ ወደብ ተጎትቶ ወደ ኤደን ተወስዷል። በአስገራሚ ሁኔታ በብረታ ብረት ብቻ ሳይወሰኑ በአይሮፕላን እያሳደዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የዱር አራዊቶች ወደ ኬኒያ ነድተዋቸዋል።

በወቅቱ በነገሩ ያልተከፋ ሰው አልነበረም። በብሪታኒያ ዘረፋና አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ መግባትን የጠሉ አርበኞች የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አይደለንም እንዋጋለን ብለው መሣሪያቸውን መወልወል ስለጀመሩ ከድል መልስ ከአንድ ዓመት በኋላ ነገሩ ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ ንጉሠ ነገሥቱ አስግቷቸው በሬዲዮ ለሕዝቡ ንግግር በማድረጋቸው ውጥረቱ በረደ። ከዚህም ደባ ለመከላከል ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዞች ሳያውቁ በድንገት ማልታ ሄደው ከአሜሪካን ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት ጋር መክረው እንግሊዞች እንዲወጡና በምትካቸው አሜሪካኖች እንዲገቡ አደረጉ። ለማንኛውም እንግሊዞች እስከ 1937 ዓ.ም ድረስ ጣልቃ መግባታቸውን አላቆሙም ነበር።

ለአራት ዓመት ያህል የብሪታንያ አምባሳደር ልክ እንደ አገረ ገዥ ከሌሎች አምባሳደሮች በላይ ሆኖ ይታይ ነበር። ዳኞች፣ የባንክ ሠራተኞችና ወታደር አሠልጣኞች እንግሊዞች ሆኑ። ፖሊስና የጸጥታ ሠራተኞች በእነሱ ቁጥጥር ስር ዋሉ። መኪና ቀደም ብሎ በቀኝ በኩል ይነዳ የነበረው በግራ በኩል ኾነ። የውጭ አገር ትምህርት የሚሰጠው አስቀድሞ በፈረንሳይኛ የነበረው ሙሉ በሙሉ እንግሊዝኛ ኾነ። በትምህርቱ መካከል የእንግሊዝ ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ ይሰጥ ነበር።

በተጨማሪም ጄኔራል ዊንጌት የሚባለውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማቋቋም ከየትምህርት ቤቱ በራሳቸው መመዘኛ ተማሪዎችን እየሰበሰቡና ነፃ የትምህርት ዕድል እየሰጡ ለወደፊት አገሪቱን የሚመሩትን የእንግሊዝ አፍቃሪ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት በዘመኑ ስውር ደባ ሲሠሩ ኖረዋል። ስለኾነም ብዙዎቹ ተማሪዎቻቸው የመንግሥት

ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በመሆንና የሚኒስትርነትና የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ቦታዎች ለመያዝ ችለዋል። ነገር ግን በትምህርት ቤቱ ከተማሩት መካከል አገር ወዳዱ ስለበዛ ዓላማቸው እጅግም አልተዋጣለትም። ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ድግሞ ትምህርት ቤቱ ለኮሌጅ ያበቃቸው ተማሪዎች ከኮሌጁ በመጀመሪያው ዓመት ከሚባረሩት መካከል በአማካይ ቁጥራቸው ይበልጥ ነበር። ይህ የሚያሳየው ትምህርት ቤቱ ተማሪዎቹን በቋንቋ፣ በብሪትሽ ታሪክና ሥነልቦና መቅረጽ እንጂ ዕውቀትን በማስተላለፍ በኩል ጥረት የማያደርግ መሆኑን ነው። አንዳንድ ግብዞች በዚያ ትምህርት ቤት ስለተማሩ ብቻ ራሳቸውን እንደተለዩ ብልህ ሰዎች በማድረግ የሚኩራሩበት አልታጡም።

እንግሊዞች አገሪቱን ለመከፋፈል ባይሆንላቸውም ኤርትራንና ኦጋዴንን እንደያዙ ቀሩ። ኤርትራ ከአፄ ዮሐንስ ሞት ጀምሮ የባልያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ከእናት አገሯ ጋር እንዳትቀላቀል ኢትዮጵያን ልንረዳ መጣን ያሉት እንግሊዞች ተሽቀዳድመው ኤርትራን ለይተው ማስተዳደር ጀመሩ። ኦጋዴን ግን የጉልበት ነገር ሆኖ እንጂ የኢትዮጵያ አካል ስለነበረች ከመቆየት በስተቀር ምንም ሕጋዊ መብት ስላልነበራቸው እስከ 1947 ዓ.ም ድረስ ወታደራቸውን አስቀምጠው ቆዩ።

ይኸም እንደውለታ ተቆጥሮ አዲስ አበባ ውስጥ በእንግሊዝ መኮንኖች፣ በመሣፍንቱና በወቅቱ በነበረው ጠቅላይ ሚኒስትር ስም የተሰየሙ ብዙ የመታሰቢያ መንገዶች አሁን ድረስ እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህም ቸርችል፣ ካኒንግሃም፣ ስመትስ፣ ኤደን፣ ኪንግ ጆርጅ፣ ንግሥት ኤልሳቤጥ፣ ወዘተ.. የሚባሉት ጎዳናዎች ናቸው። የኢትዮጵያ አርበኞች ላደረጉት ተጋድሎ የተሰየሙላቸው መንገዶች ቢኖሩም ሰዋራና ትናንሾች ስለሆኑ ሕዝቡ የሚያስታውሰው ስም የራስ አበበን መንገድና በደርግ ጊዜ የተሰየመውን የበላይ ዘለቀን መንገድ ብቻ ነው። በእንግሊዞቹ ስም የተሰየሙት መንገዶች በዚያው ስም መቅረታቸውን እንደ ጨዋነት የሚቆጥሩት አልታጡም። እነሱ ግን ብሪስቶል ኢንግላንድ ውስጥ የኢትዮጵያ መንገድ በሚል ስያሜ የተሰጠፈውን ናዚ ጀርመን በቦንብ ካፈራረሰው በኋላ ያንን ስም መልሰው መንገዱ ላይ ለመለጠፍ ስለ አልፈለጉ ሙዚየም ውስጥ አስቀምጠውታል።




# ምዕራፍ ፳፬

## አዲስ ዘመን

ንጉሠ ነገሥቱ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከስደት መልስ አዲስ አበባ ሲገቡ ባደረጉት ንግግር መጪው ዘመን አዲስ ዘመን መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበሥረው ነበር። ኢትዮጵያም አዲስ በተቋቋመው የዓለም መንግሥታት መሥራች አባል አገሮች ውስጥ አንዷ ሆነች። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደገና በአዲስ መልክ ሲዋቀሩ ሌሎች አዳዲስ ተቋሞች እንደየአስፈላጊነታቸው ተቋቋሙ። በ1936 ዓ.ም አዲስ ገንዘብ በንጉሠ ነገሥቱ ምስልና በይሁዳ አንበሳ ቅርጽ ተዘጋጅቶ በዓመቱ ሥራ ላይ ዋለ።

እንደ ክብር ዘበኛ፣ የጦር ሠራዊት፣ የአየር ኃይል የወታደር ማሠልጠኛዎችን፣ ፖሊስ፣ ፊናንስ፣ የአየር መንገድ የመሳሰሉ ተቋሞችን አደራጁ። ከኤርትራ መዋሃድ በኋላም የባሕር ኃይል ተመሠረተ። በተለይ ከትምሕርት ቀጥሎ አንዱ ከፍተኛውና ሊመሰገኑበት የሚገባ ሥራ የአየር መንገድንና የንግድ መርከብን በቀለጠፈና በዘመናዊ ሁኔታ መመሥረታቸው ነበር። ሆስፒታሎችም በቂ ባይሆኑም በዘመናዊ መልክ ተሠሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ለአዲስ ሥራዎች መሠረት መጣል፣ የተጠናቀቁትን መመረቅ፣ አንዱና ትልቁ ሥራቸው ኾነ። አዳዲስ ሚኒስትሮች በየመሥሪያ ቤቶቻቸው ሥራቸውን ማቀላጠፍ ቢጀምሩም የአገሪቱንና የሕዝቡን ችግር በዘላቂነት የሚፈታ ነገር ሊሠራ ግን አልተቻለም። በእርሻ በኩል ሠርቶ ማሳያና ማሠልጠኛዎች ቢቋቋሙም የመሬት ይዞታው ላይ መሻሻል ስላልተደረገ ለውጡ አልታይ አለ።



የኢትዮጵያ የባሕር ኃይል መኮንኖች

እንደዚሁም ከአዲሱ ዘመን አስተዳዳሪዎች መካከል ከፊሎቹ ራሳቸው ዘራፊ እየሆኑ ገበሬውን ማስቆጣት ጀመሩ። አንዳንድ አገረ ገዥዎች ደግሞ ጥንት የቀረውን አሳሽ የሚባሉ ሹሞች በየአውራጃው እየሾሙ አልዘረፍ ያሰውን በራሳቸው ሥልጣን ማጉላላት ጀመሩ። በአርበኝነት ወይም በስደት ያልተሰማራውንና ልጆቼን ላሳድግ ብሎ የተገኘውን ሥራ እየሠራ የኖረውን ሕዝብ ሁሉ እንደ ባንዳ በመቁጠር ርስቱን መንቀል፣ እምቢ ካለም ማንገላታት ጀመሩ። ትንሽ ቆየት ብሎ በኃላፊነት ሥልጣን ላይ ያሉትም ሰዎች የሃብት ማጋበስ በሽታ እየተጠናወታቸው ስለሄደ በሚሾሙበት ቦታ ሁሉ ዘመዶቻቸውን እያስቀመጡ የመንግሥትን ገቢ ለራሳቸው ማጎቀረት ጀመሩ። መታያና ጉቦ በመጠየቅም ከሕግ ውጭ ፈቃድ ሰ ቆጠት ወይም መከልከል አንዱ መጥፎ አሠራራቸው ኾነ። በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ በሚቋቋሙ ኩባንያዎች ያለምንም ክፍያ አክስዮን ካልሰጠኸኝ ፈቃድ አልሰጥም እስከማለት ደርሰው አገር ውስጥ ሊቋቋሙ የሚችሉ ፋብሪካዎች ወደ ጎረቤት አገር እንዲሸሹ አደረጉ። በገጠርም ለም የእርሻ መሬቶችን ባለሥልጣኖች መሻማት ጀምረው መሰን



ትገፋሁ፣ ርስቴን ተነጠቅሁ፣ የሚለው አቤት ባይ እየተበራከተ ሄደ። በተለይ እንደ ጅማና አርሲ ባሉ ጠቅላይ ግዛቶች የመሬት ሽሚያው ዓይን ያወጣ ዘረፋ እየኾነ በመሄዱ ሕዝብና መንግሥት ሆድና ጀርባ እየሆኑ ሄዱ። በተለይ በአርሲ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነባር ደኖች ለየሚኒስትሮች ስለተከፋፈሉ ዛፉን እየቆረጡ በመሸጥ ባለሃብት ሲሆኑ የአገሪቱን ደን አራቆቱ።

ሌላው አከራካሪ ነጥብ የጠላት ንብረት ሁኔታ ነበር። ይህንን ንብረት እንዲመዘግብና እንዲቆጣጠር የተቋቋመው መሥሪያ ቤት ቀጥታ በጃንሆይ ቤተ ርስት በሚሰጥ ትዕዛዝ በመመራቱ አስተዳደሩ መልክ ያልያዘ ነበር። በቦታ አደላደልም ላይ አሠራሩ በዘፈቀደና ውሉ በማይታወቅ መልኩ ከመሆኑም በላይ ሲያስፈልግም የግለሰብ ንብረት በትንሽ ጥፋት ይወረስ ነበር።

አፄ ምኒልክ የግል መሬት እንዲይዙ ተብለው ሲመከሩ "መላው ኢትዮጵያ የማን ኾነና እኔ በግሌ መሬት እይዛለሁ?" ብለው በመመለሳቸው በምኒልክ ስም የተያዘ አንድም መሬት አልነበረም። የእናታቸውን የዘር ርስት ወራሽ ቢሆኑም ገበሬው እያረሰ ሲኖር በግብር ምክንያት ከምስለኔው ጋር ተጋጨቶው ጉዳዩ አፄ ምኒልክ ዘንድ ሲቀርብ "ፈጣሪዬ የመላ ኢትዮጵያ አባት ስለአደረገኝ እሱም ከልጆቼ አንዱ ስለኾነ በስሙ ሊገብር ይችላል" ብለው መረቁለት። እንዲያውም እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ የነበሩት ንጉሦች የግል መሬት የሚባል አልነበራቸውም። ነገር ግን ቦታዎች ለየመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ይደለደሉ ነበር። በአዲሱ ዘመን ግን ብዙዎቹ ለግል ሰዎች በግዴለሽነት በመሰጠታቸው የዞታው ቀንሷል። ለምሳሌ የቤተ መንግሥት ከብት የሚደልብበት የወረገኑ መሬት እንዶዴ የሚባል ቦታ አሁን ቦሌ ተብሎ የሚጠራው ላይ ነበር። መሬቱም ባለቤትነቱ በራስ አሥራተ ካሣ ስም ዞሮ እሳቸውም ሸጠው ተጠቅመውበታል።

እላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች በትግራይ፣ በጎጃምና በባሌ ሽፍትነት ተጀምሮ ወታደር ጸጥታ ለማስከበር ሲላክ ባላገሩን አስቆጥቶ ይመለስ ጀመር። ከነዚህም ሌላ በጃንሆይ መሰደድ ያማረሩና ቂም የያዙ ሰዎች ንጉሡን ለመገልበጥ ማሤር ጀመሩ። እነሱም ዓላማቸው ሳይሳካ እየቀረ ተይዘው እየተፈረደባቸው ይታሠሩና ይጉላሉ ጀመር።

ይኸ ሁሉ ሲሆን በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጸጥታ ጥበቃ ሥራ ላይና የንጉሠ ነገሥቱን ዝና በማስተጋባት ፍጹም የኾነ አስተዳደር እንደነበረ ይሰብኩና ያሳምኑ ጀመር። አድር ባዮችም የንጉሡን ዝና በማራገብ ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ ሕዝቡን ግራ አጋብተውታል። ምሁሮች ምንም ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት አላቋረጡም። የፖሊሱና የጸጥታ ሠራተኛው በሙሉ አገሪቱን ሳይሆን የሚጠብቀው መሪውን ብቻ ስለኾነ ብዙ ሰዎች ተጎዱ። ፖሊስ ወገኑን ደብድብ! ግደል! ሲሉት ሳያንገራግር በያዘው መሣሪያ ሁሉ መቀጥቀጥ ልምዱ አደረገው። አንዳንዴ የፖሊሱ ኃይል ሲያንስ ወታደርም እየተደረበ ትዕዛዝ እስከተሰጠው ድረስ ወገኑን ማስቃየት ግዴታን እንደመፈጸም ይቆጥረው ጀመር። አንዳንድ አገሮች ወታደሩ በራሱ ሕዝብ ላይ እንዳይዘምትና የዴሞክራሲ መብቱ ላይ ባልቃ እንዳይገባ ሕገ መንግሥታቸው ይከለክላል።

አንዳንድ ሹሞች ምንም ቢሠሩ የማይመሰገኑና በጥፋት ጊዜ ግን የሚወቀሱ ነበሩ። በዚህ የተነሳ በሕዝቡ ዘንድ 'ንጉሠ ነገሥቱ ምንም ጥፋት ቢያደርጉም ጥፋተኞቹ ሚኒስትሮቹ ናቸው' እየተባለ በሰፋት ይነገር ነበር። ከሚኒስትሮችም ሌላ የታወቁ እንደ አባ ሃና ያሉ ሹማምንት ነበሩ። አባ ሃና ጂማ የጃንሆይን የግል ንብረት ከመቆጣጠር በተጨማሪ የንጉሠ ነገሥቱን ደህንነት ለመጠበቅ የራሳቸው የስለላ ድርጅትም አቋቁመው እንደነበረ ይታወቃል። ለዚህም አገልግሎታቸው የመንግሥት ፕሮቶኮል ከሚያውቃቸው ብዙ ባለሥልጣኖች ይበልጥ ይከበሩና ይፈሩ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና ሲቋቋም ጣሊያን መሥርቷቸው የሄደውንም፣ በራሳቸው በእንግሊዞችም ዕርዳታ የተቋቋሙት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ዘመናዊ የኾነ አሠራርን ጀምረው ሕዝቡ ተስፋ አድርጎና በተገኘው ድልም ረክቶ ንጉሠ ነገሥቱን እያመሰገነ መኖር ጀመረ። አገሪቱን ሌሎች አገሮች የደረሱበት የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሚችለው ተባብሮ መሥራቱን ቢያያዘውም መንግሥቱን የሚመሩት ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ የራሳቸው የኾነ ችግር ስለነበረባቸው በተፈለገው የሥልጣኔ እርምጃ ለመግፋት አልተቻለም። ጃንሆይን የከበቧቸው ባለሥልጣኖችም አብዛኞዎቹ ስደተኞችና ባንዳዎች በመሆናቸው በአርበኞች ይተቹ ስለነበረ ደስተኛ አልነበሩም።



ጃንሆይ በፊትም የልጅ ኢያሱን ሥልጣን አወሳሰዳቸውና በኋላም የስደት አካሄዳቸው ስላልተወደደላቸው መልሰው ሥልጣናቸውን ለማጠናከር ቀደም ብለው የሰጡትን መብት መንፈግ ጀምረው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በክብር ዘበኛ፣ ልዩ ካቢኔ፣ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሥር ፖሊስና ብዙ ግለሰቦችም ለስለላ እየተመለመሉ ተሰማሩ። እንዲያውም ጃንሆይ ደህና የጀመሩትን የሥልጣኔ ጎዳና ሕዝቡ በንቃት እንዳይገፋበት ራሳቸው መልሰው መግታት ጀመሩ። የንግግር ነጻነትን እንደማደፋፈር ጃንሆይን ሰድበሃል እየተባሉ ሰዎች በአደባባይ ይገረፉም ጀመር። ስለ ጃንሆይ ጥሩ መናገር እንጂ በመጥፎ ስማቸውን ማንሳት የሚያስፈራበት ወቅት መጣ። ስለኾነም ንጉሡን የሚተች ኢትዮጵያን እንደከዳ እየተቆጠረ ሁሉም ሆዱ እያወቀ ለመኖር ሲል ብቻ በመፈራራትና በመተማማት ኑሮውን ቀጠለ። በዚህም ምክንያት አገሪቱ በሥልጣኔና በምጣኔ ኃብት ወደ ኋላ እየቀረችና የተወሳሰቡ ችግሮች ውስጥ እየገባች ሄደች። ብዙ ተቋሞች ጥራት ባለው አደረጃጀት ይመሥረቱ እንጂ መስፋፋት ግን አልቻሉም። የቀለጠፈ አሠራር ዘርግተው ቢያካሂዱም ጠቀም ያለ አገሪቱን ከድህነት ሊያወጣ የሚችል የጎላ ዕድገት አልታየም። ምክንያቱም መንግሥት ገንዘብ ስላልነበረው ነው ቢባልም ይኸ ጉዳይ በተለይ ራሱን የቻለ የሚያነጋግር ነጥብ ነው። ለምሳሌ ለየክብረ በዓሉ ከመጠን ያለፈ ወጭ፣ ለጉብኝትና ለእንግዶች ማስተናገጃ የሚፈሰው ገንዘብ፣ በድርጎ መልክ የሚሰጥ ገንዘብ፣ ለየወይዛዝርቱ የክብር መጠበቂያ እየተባለ ሳይሠሩ የሚከፈል ደሞዝና የመሳሰሉት አላስፈላጊ ወጭዎች ነበሩ።

በቀረጥ የሚሰበሰበው ገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ እየተረሳ ልክ እንደንጉሠ ነገሥቱ የግል ኃብት ስለሚቆጠር መንግሥትን ለመምራት በተሰጣቸው ኃላፊነት የሚያደርጉት ማናቸውም ነገር በግላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ውለታ እንደዋሉለት ይቆጠር ነበር። የትምህርት ታክስ ሕዝቡ እየከፈለ ጃንሆይ ልጄን አስተማሩልኝ ብሎ እንዲያስብ ተደረገ። ሆኖም ጃንሆይ የትምህርትን ሁኔታ ቅድሚያ ሰጥተው በጣም ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ በማድረጋቸው ይመሰገናሉ። ያም ሆኖ ግን በአጠቃላይ የተጠበቀውን ያህል ዕደገት በወቅቱ ባለመታየቱና በተደጋጋሚ በተከሰቱ በደሎች የሕዝቡ ቅሬታ ተባብሶ የጃንሆይን መንግሥት እስከ ማናጋት ደረሰ።

ዳሩ ግን አሁንም ብሆን ሳይጠቀስ የማይታለፈው ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ለማፍራትና ክብሯን ከፍ ለማድረግ ብዙ ሥራ መሥራታቸው ነው።

1ኛ) በ1939 ዓ.ም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በሰብል መበላሸት ምክንያት በብሪታንያ ረሃብ በመግባቱ በኢትዮጵያ ስም ጃንሆይ አንድ ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ ዕርዳታ ለግሰዋል።

2ኛ) ደቡብ አፍሪካን ከአፓርታይድ ነፃ ለማውጣት ለሚታገሉት ብሔርተኞች መጠለያ ከመስጠት ሌላ ብዙ ዕርዳታ ተደርጓል። ለስደተኞች በትምህርት ሚኒስቴር ሥር በየክፍለ አገሩ በአስተማሪነት ከመቀጠር ሌላ ለታጋዮች የወታደር ሥልጠናና ዕርዳታ ይሰጥ ነበር። በተለይ ለትግሉ መሪዎች ደመወዝ በመስጠትና እቴጌ ሆቴል በማስቀመጥ እንክብካቤ ተደርጎላቸዋል። ከመካከላቸው ሚስተር ኔልሰን ማንዴላና ሌሎችም ኮልፌ በፊጥኖ ደራሽ ተቋም ውስጥ ሠልጥነዋል።

3ኛ) ናምቢያ ነፃነት ከመውጣቷ በፊት በነበረው ውዝግብ ኢትዮጵያና ላይቤርያ ለሁለት ጠበቃ አቁመው ለዘጠኝ ዓመት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሲከራከሩ ቆይተዋል።

4ኛ) የኬንያ የማኦ ማኦ (ሰው ሰው ነው) ሕቡዕ ነፃ አውጭ ድርጅት መሪ ለነበሩት ሚስተር ጆሞ ኬኒያታ ሰባት ዓመት ሙሉ ታስረው በነበረ ጊዜ ለሴት ልጃቸው በየወሩ 250 ሺልንግ በኢትዮጵያ ጄኔራል ቆንሲል አማካይነት ይሰጥ ነበር።

5ኛ) ኬኒያ ላይ ደርሶ ለነበረው ረሃብ ማስታገሻ እንዲሆን በኬኒያ የብሪታኒያ ተወካይ ለነበሩት ለሰር ሃምፍሬይ 250 ሺህ ሺልንግ ዕርዳታ ተሰጥቷል።

6ኛ) በቀዳማዊ ኢድሪስ ጊዜ ሊቢያ በደረሰባት ረሃብ የተነሳ የኢትዮጵያ መንግሥት ዕርዳታ አበርክታለች።



7ኛ) የገናሌና የዋቤ ሸበሌ ወንዞች ሶማሊያን ባጥለቀለቁበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይል አይሮፕላኖች ምግብ በማድረስና ሰው በማዳን ሥራ ላይ ተሰማርተው አገልግሎት ሰጥተዋል።

8ኛ) በተባበሩት የዓለም መንግሥታት ውሳኔ መሠረት ከ22 አገሮች መካከል የክብር ዘበኛ ወታደሮችን በቃኘው ሻለቃ ስም ኮሪያ ላይ በማዝመት ኢትዮጵያ ታላቅ ኃላፊነቷን በጀግንነት ተወጥታለች።

9ኛ) ለአፍሪካ ያለባትንም ኃላፊነት ለመወጣት ስትል ኢትዮጵያ ጦር ሠራዊቷን በተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ሥር ኮንጎ ከማዝመቷም ሌላ በጦር ኃይሉ አዝማችነትና መሪነት አገልግሎት ሰጥታለች።

10ኛ) የአፍሪካን አገሮች ለመርዳትና ለማቋቋም ለብዙ ተማሪዎች የነፃ ትምህርት ዕድል በምስጥት በአየር ኃይል፣ በሐረር ጦር አካዳሚ፣ በዩኒቨርስቲ፣ በአየር መንገድ እየተቀበለች ለብዙ አፍሪካውያን ውለታ ሠርታለች።

11ኛ) በቢያፍራና በናይጄሪያ መንግሥት መካከል የተነሳው የመገንጠል ጥያቄ ያስከተለውን የእርስ በእርስ ጦርነት ለማስቆም በአስታራቂነት ንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

12ኛ) በደቡብና በሰሜን ሱዳን የነበረውን ጦርነት በአስታራቂነት ንጉሠ ነገሥቱ ገብተው ጦርነቱን ለማስቆም ችለው ነበር።

13ኛ) በስሃራዊ ድንበራቸው ምክንያት አልጀሪያና ሞሮኮ በተጣሉ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ የአስታራቂነት ተግባር አከናውነዋል።

14ኛ) የአፍሪካ አገሮችን ሰብስበው ማኅበር በመፍጠር እንዲዋሃዱና በአንድነት ተደራጅተው ኃይል እንዲያገኙ ንጉሠ ነገሥቱ አስተባብረው ጽሕፈት ቤቱንም አዲስ አበባ እንዲሆን አድርገዋል።

14ኛ) ለታንዛኒያ የንቅናቄ መሪ ለሚስተር ኒሬሬ የወር ደመወዝ ተቆርጦላቸው ይከፈላቸው ነበር። በዚህ ውለታ ከነፃነት በኋላ የውጭ አገር ሰዎች ከታንዛኒያ ሲባረሩ 600 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ክሊማንጃሮ ተራራ አጠገብ በግብርና የመኖር መብታቸው ተጠብቆላቸዋል።

15ኛ) ከኬኒያ መንግሥት ጋር በነበራቸው ጥብቅ ግንኙነት ሳቢያ በኢትዮጵያ መንግሥት ለኬኒያ ኤምባሲ የሚሆን 10ሺህ ሜትር ካሬ መሬት ተሰጥቷቸዋል። እነሱም በምትኩ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ መሥሪያ የሚሆን ቦታ ሰጥተዋል።



# ምዕራፍ ፳፫

## የኤርትራ ታሪክ ዳሰሳ

የኢትዮጵያ ንጉሥ ካሌብ በነገሡበት በ6ኛው ክፍለ ዘመን የየመን ክርስቲያን ሕዝብ ከፍልስጥኤም በፈለሱ አይሁዶች ጥቃት ሲበዛበትና በሰንዓ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ማፈራረስ ሲጀምሩ በአካባቢው ከነበሩ ክርስቲያኖች ዕርዳታ መጠየቅ ጀመረ። የዚህን ጊዜ የግብፁ የአሌክሳንድርያው ፓትርያርክ የኢትዮጵያውን ንጉሥ ካሌብን 'እባክህ ለየመን ክርስቲያኖች እርዳታ ላክ' ብለው ስለጠየቁት ሰባ ሺ ወታደር ይዞ ዘመተና ድል አድርጎ ክርስቲያኖችን አዳናቸው። ከዚያም አፄ ካሌብ ባለሟሉን አብርሃን ከአሥር ሺ ወታደር ጋር የመን ላይ ትቶት ተመለሰ።

አብርሃ ከቀን ብዛት ራሱ የየመን መሪ ሆኖ ለአፄ ካሌብ መታዘዝ አቆመ። በመሃሉ ንጉሥ ካሌብም ሥልጣኑን ለወራሹ ትቶ መነነ። ከእርሱም በኋላ የተነሱት የመንግሥት ወራሾች በኃይል ማነስና በውስጥ ችግር ሲወጠሩ የመን የቀሩት ኢትዮጵያውያኖች የየመንን አገር ለመቶ ዓመት ያህል ማስተዳደር ቀጠሉ። የየመን ሰዎች አረብ ባልኾነ መሪ መግዛትን ያልወደዱት ብሔርተኛ አረቦች ከፋርስ (ኢራን) ሰዎች ጋር ተመሳጥረው የመን ላይ ይዘምቱና ኢትዮጵያውያንንና ክርስቲያን አረቦችን ፈጁዋቸው። በዚህ ወቅት ክርስቲያን አረቦችና ሃበሾች የሞተው ሞቶ የቀረው ወደ ኢትዮጵያ፣ ሳውዲ አረብያና ወደ ሌላ አገሮች ተበተኑ። በተለይ ወደ ሳውዲ አረብያ የተበተኑት በሠላምና በመግባባት ሲኖሩ አልፈው ተርፈው መካን ከወረራ ለማዳን በውትድርና ማገልገል ጀምረው ነበር። ሳውዲ አረብያ ገና በጣኦት የሚያመልኩ ከበርቴ ነጋዴዎች የተንሰራፉበት አገር ስለነበረች የክርስትናና የአይሁድ ሃይማኖት ጭቅጭቅ መነሳት ሲጀምር ሁሉቱንም ላለመቀበል ሲከላከሉ ረጅም ዘመን አሳልፈዋል። በዚህ ግብግብ አካባቢው ሲታመስ ቆይቶ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን መካ ከተማ በነቢዩ ሙሐመድ የሚመራ

የእስላምና ሃይማኖት ንቅናቄ ይነሳና የአዲሱ ሃይማኖት አማኞች ባእት አምላኪዎቹን ፈርተው ወደ መዲና ይሸሻሉ። በዚያኑም ወቅት ነቢዩ ሙሐመድ የቅርብ ቤተሰቦቻቸውን ለደህንነታቸው ወደ ሃበሻ አገር ንጉሥ ይልካሉ። መጨረሻ ላይ ሙስሊሞቹ ከመዲና ተነስተው መካ በድል አድራጊነት ከገቡ በኋላ በዚያ አካባቢ ሌላ ሃይማኖት ያለው ስለሚገደል ወይም ለመኖር የፈለገው ሁሉ ሰለመ።

በአሥር ዓመት ውስጥ እስልምና የአረብን አገር በሙሉ አጥለቅልቆ ወደ ፍልስጥኤምና ግብጽ ተዛመተ። በቀይ ባሕርም ላይ ሌላ እስላም ያልኾነ ኃይል እንደበፊቱ መንቀሳቀስ ተቸገረ። ከ8ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ምጽዋና አዱሊስ በእስላሚ በቱርክ ተያዙ። በተለይ ቱርኮች የኢትዮጵያን የባሕር ዳርቻ መቆጣጠር ሲጀምሩ የኢትዮጵያ መርከበኞች ስለተቸገሩ በየቦታው እየሄዱ ዘረፋ ጀመሩ። በተለይ ዛሬ ጄዳ የሚባለውን ከተማ የኢትዮጵያ መርከበኞች አከታትለው ስለዘረፉት አረቦቹ ፈርተው ሃበሾች የአረብን አገር ወረው የነቢዩ ሙሐመድን አጽም ወስደው ሊያቃጥሉ ነው ብለው ስላስወሩ ሁሉም ተረባርቦባቸው መርከበኞቹ ተፈጁ።

ነቢዩ ሙሐመድ ዘመዶቻቸውን በክፉ ቀን ከለላ የሰጠችውን አገር ሙስሊሞች እንዳይወሩ ወይም የጅሃድ ጦርነት እንዳያደርጉባት አዝዘው ስለነበረ የቀይ ባሕር ድንበረተኛ የነበረችው ክርስቲያኗ ሃበሻ ወይም ኢትዮጵያ ባትወረርም ደካማ ሆና ቀረች። ሌላውን የአካባቢ አገር ቱርክ እያሸነፈች ስታስገብር ምጽዋንና አዱሊስን አልፋ ለማስገበር የማይሆንላት ስለኾነና ባሕሩ ላይ ኃይል ስላላት ዝም ብላ ቁጭ አለች። በጊዜ ብዛት በቀይ ባሕር መካከል ያሉትን የዳህላክ ደሴቶችን ስም በሙሉ ለውጣ የአረብኛ ስም ሰጠች። የአፋርን ሕብረተ ሰብ ሃይማኖት እስላም አድርጋ ወደ መሃል ኢትዮጵያ በተንቀሳቃሽ ነጋዴዎች መስበክ ጀመረች። የሃበሻና የሶማሌ ሙስሊም ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ለማስጨበጥ ቱርኮች ግራኝ ሙሐመድን እየረዱ የውስጥ ብጥብጥ አስነሱ። የኋላ ኋላ ግን ቱርኮች እየደከሙ ሲሄዱ ምጽዋን ለግብጾች ጥለው ሄዱ። ግብጾች የሚመሩት ከቱርክ ዘር በሆኑ ንጉሥች ስለነበረ ብዙም አልገደዳቸውም። መጨረሻ ላይ ግብጾች በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥር ሲወድቁ የግብጽ ግዛት ሁሉ የእንግሊዞች ሆነና ምጽዋም ላይ ማዘዝ ጀመሩ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከምጽዋ ከተማ ሌላ ግዛቱ በሙሉ የኢትዮጵያ እንጂ ማንም ወደ ውስጥ ገብቶ ለማስገበር አልቻለም። ወደ ምጽዋ በሚወስደው መንገድ ነፋሲት ወረዳ አርብ ዕሮብ መንገድ ላይ



የሚገኘው የደብረ ቢዘን ገዳም በቄሣር መንግሥት የኢትዮጵያ አካል ለመሆኑ ተመዝግቦ ይገኛል።



አፄ ኃይለሥላሴና ክቡር አቶ አክሊሉ ሃብተወልድ

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት እንግሊዞች የፈረንሶዮችንም መስፋፋት ለመገደብ ጣሊያኖችን ምጽዋ አስገብተዋቸው ቦር ስላሉ ጣሊያኖች ቀላል መስሏቸው በተደጋጋሚ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ በዙ ሙከራ ቢያደርጉም ከሽፎባቸዋል። በአንድ ወቅት ግብጾች ደጋው ላይ ወጥተው ስለተገኙ ተፈጁ። ግብጾችም በ19ኛው ክፍለ ዘመን 15 ጊዜ ጦርነት ከፍተው በኢትዮጵያውያን ተሸንፈዋል። ከዚህም ጦርነት አንዱ የአፋር ሰዎች አድብተው የግብጽን ወታደሮች በአዳል በርሃ መፍጀት ነበር። በዚህ መካከል ግብጾች ለ11 ዓመት ሰርገው ገብተው ሐረርን አስተዳድረዋል። የሐረር ሰዎች ሙስሊም ስለነበሩ የግብጾችን ሙስሊምነት ብቻ በመመልከት የውጭ ጠላት መሆናቸውን ዘንግተው ምንም ሳይከላከሉ ተቀበሉዋቸው። በኋላ ግን ግብጾች በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል በአፄ ዮሐንስ ስለተሸነፉና ኃይላቸውም ስለተመናመነ በሠላም እንደገቡ ሁሉ በሠላም ሐረርን ለቀው ወጡ። ያ ግብጾችን እያጨበጨበ

የተቀበለው ሕዝብ ግን አፄ ምኒሊክ የአገሪቱን ድንበር ከቅኝ ገዥዎች ለመከላከል ወደ ሐረር ሲዘምቱ ወግቷቸዋል።

አሰብ ላይ በንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመን ሠፍሮ የነበረውን የጣሊያን ወታደር ምናልባት ከርቀቱና ከበርሃማነቱ የተነሳ ይሆናል ለማባረር እርምጃ ሳይወሰድ ቀረ። ሆኖም ከመረብ ወዲያ ያለውን ግዛት በአጼ ዮሐንስ ተሹመው የነበሩት ራስ አሉላ በመከላከል በጣሊያንና በግብፅ መስፋፋት ላይ ጦርነት እያካሄዱ አልበገር ብለው ቆዩ። በተለይ በዶግአሊ ወደ 500 ነጭ የጣሊያን ወታደር ሬሳ በመረፍረፍ ጣሊያኖችን አስደነገጡ። በዚህም ምክንያት በወቅቱ የነበረው የኢጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ሥራ ለቀቀ። ስወታደሮቹም ማስታወሻ ሮማ ከተማ መካከል ያለውን አደባባይ ፒያዛ ዲ ቺንኩዌ ቼንቶ (የአምስት መቶዎቹ አደባባይ) ብለው ሰይመውት እስከ አሁን በዚህ ስም ይታወቅበታል።

ከብዙ ዘመን በኋላ ዶጋአሊ አጠገብ ባለው መንገድ በሰዎች ላይ የመኪና አደጋ በተደጋጋሚ በመድረሱ በርካታ ሰዎች የአዕምሮ ሕመምተኞች እየሆኑ ጸጸረት ሆስፒታል ውስጥ ሲገቡ "የሙት መንፈስ (GHOST) መኪናችን ውስጥ ገብቶ አነጋገረን" እያሉ ይናገሩ ጀመር። ጣሊያናዊው ኢንጂኔረ ብራንካ ይኸው በተመሳሳይ ሁኔታ ሲገጥመው የሙት መንፈሱን አነጋግሮ ጄኔራል ቦቴን መሆኑንና "በሥርዓት አልተቀበርኩም" ብሎ ስለገለጸለት የዚሁ ጄኔራል አስከሬን አንደገና በጣሊያን ባንዲራ ተጠቅልሎ በሥርዓት እንዲቀበርና ሐውልት እንዲሠራለት በመደረጉ ችግሩ አቆመ።

ሰዎች አጼ ዮሐንስን እየመከሩ ጥርጣሬ ላይ ስለጣሉዋቸው ራስ አሉላን ከባሕር ነጋሽ ግዛት አንስተው ራሳቸው ጠቀለሉት። ስለሆነም በቅርብ የባሕር ነጋሽን ሁኔታ የሚከታተል ባለመኖሩ የየአውራጃው አስተዳዳሪዎች ከጣሊያኖች ጋር መግባባትን እየፈጠሩ ስላስቸገሩና በአካባቢው ጣሊያን እየጎለበተ ስለሄደ አፄ ዮሐንስ ጣሊያንን ለማባረር 70,000 ጦር ይዘው ሲሄዱ ምሽጉን ሠርቶ ስለጠበቃቸው ከበውት ተቀመጡ። በርሃው መካከል ለሁለት ወር ያህል ወታደራቸው በተቀመጠበት ወቅት ሙቀቱን ባለመቻሉና ስንቅም ስላለቀባቸው በዛውም ድርቡሽ ጎንደርን መውረሩን ሲሰሙ እመለስበታለሁ ብለው ወደ ደጋው ወጡ። አጼ ዮሐንስ ከድርቡሾች ጋር ጦርነት ገጥመው ደህና እያሸነፉ እያሉ ቆሰሉና ጦራቸው ተፈታ። መኳንንቶቻቸው ቁስለኛውን



አጼ ዮሐንስን ይዘው ሲሸሹ መንገድ ላይ ሞቱባቸው። አሁንም ድርቡሾቹ ደርሰውባቸውና ብዙ መኳንንቶቻቸው ሲከላከሉ በማለቃቸው የአጼ ዮሐንስን ጭንቅላት ቆርጠው ወስደው ለአለቃቸው ግዳይ አቀረቡለት። የኸንን አልቃሽ እንደሚከተለው ተቀኝታበታለች።

አፄ ዮሐንስ ይዋሻሉ
መጠጥ አልጠጣም እያሉ
እኛም ሲጠጡ አይተናል በርግጥ
ራስ የሚያዞር መጠጥ
ንጉሥ ሁኑ ቢሏቸው በመግለ
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ

ይህንን የአጼ ዮሐንስን መገደል የሰማው የጣሊያን ጦር ተንደርድሮ አሥመራ ይገባና ከመረብ ወዲያ ያለውን አገር ያዘው። ከአፄ ዮሐንስ ቀጥሎ የነገሡት አጼ ምኒልክ መረብን ዘሎ ግዛታቸውን ጣሊያን እንዳይዘው ስምምነት ይፈራረሙና ጣሊያንን መረብ ወንዝ ላይ ለማስቀረት ሞከሩ። ነገር ግን የጣሊያን ሃሳብ መላ ኢትዮጵያን በቅኝ ለመያዝ ስለነበር ምቹ ወቅት ጠብቆ ለመውረር ተነሳ። ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ በራስ መንገሻና በአፄ ምኒልክ መካከል ውርስ ለእኔ የገባል የሚል የውስጥ ሽኩቻ ስለነበረ አፄ ምኒልክ መሣሪያ ከጣሊያን እየተቀበሉ ይዋዋላሉ። በአንጻሩ ራስ መንገሻ ከጣሊያን ጋር ለወዳጅነት ይማማላሉ።

ምኒልክ ጦራቸውን አጠናክረው ወደ ሰሜን ሄደው ትግራይን በሦስት ከፍለው ሹሞቻቸውን መድበው ተመለሱ። ከጣሊያን ጋር የተዋዋሉትን ውል አፄ ምኒልክ በመሰረዛቸው ጣሊያን ወሰን ገፍቶ መግባት ሲጀምር ኃይላቸውን አስተባብረው ጠብቀውት ስለነበር በ1888 ዓ.ም አድዋ ላይ በተደረገው ጦርነት ድል ይመቱና የአውሮፓን ቅኝ ገዢዎች በሙሉ አስደነገጧቸው። በዚህም ሳቢያ ለኢትዮጵያ መንግሥት ቅኝ ገዥውች ዕውቅና ለመስጠት ተገደዱ። አፄ ምኒልክ ገፍተው ሄደው ኤርትራን ማስለቀቅ የማይቻል መሆኑን የተረዱት ጣሊያኖች 18,000 አዲስ ጦር መላካቸውንና በዘመኑ በነበረው ድርቅ ሳቢያና ጦሩም የስንቅና የውሃ ችግር ስለገጠመው ሌላ ዘዴ ወጠኑ። ይኸውም ድርቡሾችን በጣሊያን ላይ አስነስቶ በከሰላ በኩል ሲዋጉና ጦራቸው ሲከፈል ምኒልክ በአሥመራ በኩል ለመምታት ነበር። ድርቡሾች እራሳቸው በውስጥ ችግር ተዳክመው ጦርነቱን ስለተውት

ምኒልክም ቀደም ብለው የጀመሩትን የአውሮፓን ሥልጣኔ ወደ አገር ውስጥ ማምጣት ገፋበት። አፄ ምኒልክ አድዋ ላይ ድል ከአደረጉ በኋላ ኤርትራን ባለማስለቀቃቸው እስከ አሁን ድረስ የኤርትራና የትግራይ ሰዎች ቅሬታ አላቸው። ምክንያቱም የባሕር ነጋሽን አሸንፈው ቢጠቀልሉት ኖሮ የትግርኛ ተናጋሪዎች ሲያብሩ ኃይል ስለሚያገኙ መንግሥቴን ይወስዱብኛል ብለው ነው ጦርነቱን ያልገፉበት ብለው ጠርጥረዋል። በነበረው ሁኔታ ገፍተው ቢሄዱ ኖሮና ቢሸነፉ ውጤቱ ጎጂ ሊሆን እንደሚችል አስቀድመው በማወቃቸው እንጂ ሌላ ዘዴ ሊያገኙለት ለሚችሉት ለውስጥ የሥልጣን ትግል ብለው አንድ ግዛታቸውን በቀላሉ የሚለቁ ንጉሥ አይመስሉም።

ጣሊያኖች በአድዋ ድል መመታት ተቆጭተው ስለነበርና ጣሊያን በፋሽስት ብሔርተኞችና በዱቼ ሙሶሎኒ መሪነት ኃይል ተሰምቷቸው ስለሄደ ከአርባ ዓመት በኋላ ነገር እየቆሰቆሱ ጦርነት ከፈቱና ኢትዮጵያን በ1928 ዓ.ም ወረሩ።

የጣሊያን መንግሥት ከጀርመን ጋር አጋር በመሆን በእንግሊዝና ፈረንሳይ ላይ ጦርነት ስለከፈተ ወዳጆቻቸው የነበሩት የቅኝ ገዥዎች አሁን የኢትዮጵያ ረዳት ሆኑና ጣሊያኖች ተሸንፈው ኢትዮጵያ ነጻነቷ ሲመለስ ለዕርዳታ የመጣው እንግሊዝ ቶሎ ብሎ ኤርትራን ይዞ ማስተዳደር ጀመረ።

ከድል በኋላ የጣሊያን የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ለድርድር ሲቀርብ ኢትዮጵያ ኤርትራን ግዛቴ ነች ትመለስልኝ ብላ መከራከር ጀመረች። አሰማሚዎቹ ካቀረቡዋቸው የተለያዩ ሃሳቦች መካከል አሰብን ያለምንም ችግር ኢትዮጵያ ትውሰድና ስለሌላው እንወያይ ቢባልም ኢትዮጵያ ግን የአሰብ ጉዳይ ከመላው የኤርትራ ጉዳይ መለየት የለበትም ብላ ሰላሳሰበች የአሰብ ጉዳይ ሞተ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በኤርትራ ውስጥ በተፈጠረው "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ትግልና በእነ አቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ዲፕሎማሲ ትግል ታህሣሥ 2 ቀን 1943 ዓ.ም ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን ለአሥር ዓመት እንድትዋሃድና ከአሥር ዓመት በኋላ ምርጫ እንዲደረግ ተወሰነ። የፌደሬሽኑ ወቅት ሲያልቅ በኤርትራ ምክር ቤት ውስጥ ውሳኔ ተላልፎ ከመስከረም 1 ቀን 1952 ዓ.ም ጀምሮ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተዋሐደች።



አንድን ውሳኔ መቼም መቶ በመቶ ሁሉም ስለማይደግፈው ጥቂት የፓርላማው አባሎች አጉረምርመው ወደ ጎረቤት አገር ሄደው ለኤርትራ ነጻነት ለመዋጋት እንቅስቃሴ ጀመሩ። ሕዝቡ በየወረዳው ድምጽ አልሰጠበትም ብለው የሚከራከሩም ነበሩ።

ከፌዴራሽን ጀምሮ ለአንድነት ሲታገሉ የነበሩት ሰዎች በሹመት መካስ ሲገባቸው በአንጻሩ ሲወላውሉና ሲያስቸግሩ ለነበሩት ከበሬታውና ሥልጣኑ ስለተሰጠ የተከፉ ሰዎች በቤት ውስጥ ሲነጫነጩ፥ ልጆቻቸው በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጭፍን ጥላቻ እያቆሩ አደጉ። በተጨማሪም በእንደራሴነት ከመሃል አገር የሄዱት ራስ አንዳርጋቸው መሳይና ራስ አሥራተ ካሣን የመሳሰሉት የሃብት ዘረፋ ውስጥ ገብተው ስለነበረ ኢትዮጵያዊነት ላይ የነበረውን የሰዉን አመለካከት ለወጡት ተብሎ በወቅቱ ተገምቷል። ጃንሆይም ኤርትራን ለማስመለስ የተደከመውን ያህል ለማፍረስ ሰዎች ሲጥሩ ምንም ሳይመስላቸው ከማለፋቸው ሌላ እንዲያውም ነገሩን በሹም ሽር አባባሱት። ከዚህም ሌላ ከውጭ በተገኘ ብድር የአሰብ ወደብ ተሠራና የምጽዋ ወደብ ሥራ ፈታ።

በአሥመራና በደጋው ኤርትራ የተሠማሩ ሠራተኞች በአካባቢው ኤኮኖሚው ስለደከመ ወደ መሃል አገር ቢመጡና ቢያመለክቱም ችግራቸውን ዞር ብሎ የሚመለከት ባለሥልጣን ጠፋ። ስለሆነም ብዙዎች ኤርትራውያኖቹ ተቸገሩ። በወቅቱ በስርቆትና በማጭበርበር በአዲስ አበባ ውስጥ ማጅራት መቺው ስለበዛ ለማስፈራራት በየቦታው የአጠና መስቀያ ተተክሎ ብዙ ሰው በስቅላት የሚቀጣበት ጊዜ ስለነበረ ተስፋ ሲቆርጡ በየጎረቤት አገር ሥራ በመፈለግ ተሰደዱ። በአገር ውስጥም ባሉት ኤርትራውያኖች ውህደቱ ባመጣባቸው አኗኗር ተስፋ መቁረጥ ተጀምሮ እንዲያውም የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ብ. ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት ወገኖቼን ሳጉላላ የኖርኩት ለዚህ ኖሯል ወይ ብሎ በመጻጻት ራሱን ገደለ ተብሎ ተወሳ። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች



ብ.ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት

የለም ቢሮው ውስጥ ተገድሎ ነው የሚሉም አሉ። ይሁንና ቅር ተሰኝቶ እንደነበረ ይታወቃል። በጠቅላላው ኤርትራውያኖች ከኢትዮጵያ መለየትንና የኤርትራን መንግሥት ለመመሥረት ወሰኑ።

ይህ ሁሉ ተዳምሮ የነጻ አውጪ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ሲጀምሩ ጸጥታ ሊያስከብር የሄደውን ወታደር ከየተለማራበትና ከሚፋለምበት ቦታ "ተዋቸውና ተመለሱ!" እያሉ የሚገቷቸው ባለሥልጣኖች ተፈጠሩ። በተጨማሪም በሙስሊም የነጻነት ተዋጊ መሪዎችና በክርስቲያን ጀሌዎች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ሌላ በክርስቲያኖች የሚመራ ነጻ አውጪ ድርጅት ተቋቋመ። በዚህ ወቅት አዲሶቹን መሪዎች የመንግሥት ባለሥልጣን የሆኑት ይረዷቸውና ያበረታቷቸው ጀመር። የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሚያበረታቷቸው ለሁለት ነገር ነበር። አንዱ በሙስሊሞች የሚመራውን ነፃ አውጭዎች አዳሱ በክርስቲያኖች የሚመራው ነፃ አውጭ እንዲቋቋመውና ሚዛን እንዲጠብቅ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ በመሃል አገር በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉትን የሚቀናቀን ነፃ አውጭ እንዳይነሳ ለፖለቲካ መጠቀሚያ እንዲሆኑ ነበር። በዘመኑ በቃኘው ሻለቃ ስም የአሜሪካን ጦር ሠፈር አዛገሮችም ለነፃ አውጭዎቹ በመጠኑ እርዳታ አልነፈጓቸውም ይባላል። ምክንያቱም እንደተለመደው ኢትዮጵያ ግዙፍ አገር እንዳትሆን ለመከላከል በሚደረገው የእንግሊዞች ደባ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ይመስላል።

በመሃሉ የ1966 ዓ.ም አብዮት ፈንድቶ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊቶች የበታች መኮንኖች ሥልጣን ሲይዙ ተደጋጋሚ ስህተቶች መሥራት ጀመሩ። አንዱ ስህተት ኤርትራዊ የኾነውን ተወዳጅ ጄኔራል ርዕሰ ብሔር አድርገው ከሾሙ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ለሥልጣን ሽሚያ ሲሉ በስበብ አስባቡ ስለገደሉት የብዙ ኤርትራውያንን ልብ አሸፈቱ። ቀጥለውም የተማረው ኃይል ሥልጣናችሁን ለሕዝብ ስጡ እያለ ሲያስቸግራቸው "ዕድገት በሕብረት" የሚል ዘመቻ አውጀው ተማሪውን በውድም በግድም በመላው ኢትዮጵያ ሲያዘምቱ የኤርትራ ተማሪዎች ግን ሸሽተው ከነፃ አውጭ ጋር በማበራቸው 1,500 ብቻ የነበረው የሽምቅ ተዋጊ ጦር ወዲያው 45,000 ሆኖ ታላቅ የተቃዋሚ ኃይል ተፈጠረ። ደርግ የሾመው ኮሎኔል ዘነበ አስፋው የሚባል እሥመራ ውስጥ የነበረውን ወጣት ስላስበረገገው ሙሉጭ ብሎ ወደ ነፃ አውጭዎች ገባ። ይባስ ብሎ



እነሱን ለማደን ተዘጋጅቶ የነበረው የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ የኮማንዲስ ጦር በደርግ ችላ ስለተባለ ለሽማቂዎቹ ገብቶላቸው ትልቅ ኃይል ሆኑ። በተጨማሪም ነጻ አውጭዎቹ በአስታራቂ እጅ ለመስጠት ወደ ከተማ ሲመጡ ወታደሮቹ መንገድ ጠብቀው ስለተኮሱባቸው አምርረው በትግላቸው ቀጠሉ። የኤርትራ ተወላጅ የሆኑትን ከባሕር ኃይልና ከአየር ኃይል ሰብስበው አዲስ አበባ አራተኛ ክፍለ ጦር ሲያስሩ የኤርትራ ሕዝብ ቁርጥ ውሳኔ አድርጎ በመላ ኃይሉ ለነፃነቱ መታገሉን ቀጠለበት። እንደ ዶክተር በረከት ሃብተ ሥላሴ ያሉ በሹመት ያልተደሰቱ ምሁሮች በመሰደድ በውጭ አገርም ስለኤርትራ ፕሮፓጋንዳ በመንዛትና እስከ መጽሐፍ ድረስ በመጻፍ የኤርትራን ነፃነት በሚችሉት ለቀረው ዓለም በማሳመን ግፊቱ እየበረታ ሄደ።

በንጉሡ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ሊወገድ የሚችለውን የነፃ አውጭ ድርጅት ባለሥልጣኖች እንዲጠፉ ስለማይፈልጉ ወታደሩ ተከታትሎ ሊመታቸው ሲቃረብ 'ተመለሱ!' እየተባለ የሚባለው አሠራር በደርግም ጊዜ በመቀጠሉ ጥቂት ወታደሮች ነገሩ ይመራቸውና በኋላ ለይ ከፋኝ በሚል ስያሜ ሸፈቱ። ራስ አሥራተ ካሣ እንደራሴ በነበሩበት ጊዜ የጦር መማሪያ የመንግሥት ሹሞች ለነፃ አውጭዎቹ ሲያቀብሉ በጸጥታ ሠራተኞች ስለተደረሰበትና ይህንን ጉዳይ ብ/ጄኔራል ተሾመ እርገቱ ሲከታተሉት እያሉ በመሃሉ በነፃ አውጭዎቹ ተገደሉ። ይኸ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ ኮማንደር እስክንድር በተለይ ደግሞ ራስ አሥራተ ካሣ በግልጥ መኪና ያለአጃቢ ከምጽዋ አሥመራ ብቻቸውን ይጓዙ ነበር። በጊዜው ሰዎች የሰጡት ትርጉም እንደራሴው ከነፃ አውጭዎቹ ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው አድርጎ ነው። ሆኖም ራስ አሥራተ ካሣ ከቦታቸው መሻራቸው አልቀረም። የጃንሆይ መንግሥት ሲለወጥ ዋና የመማሪያ አቀባይ የክፍለ ሃገሩ የፖሊስ ጄኔራል እንደነበረ ተደርሶበታል።

የአብዮቱ መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባንዲራ በመሳም አገር ወዳድ እየመሰሉ የኤርትራን ጦርነት በሥልጣን ላይ ለመቆየት ተጠቀሙበት። በመጀመሪያ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጦር ሠራዊት ቦይስካውት በነበሩ ጊዜ የባሕር ኃይል ወታደር በሚመለምልበት ወቅት ከጓደኞቻቸው መካከል ብዙዎቹ ሲመለመሉ እሳቸው በተፈጠረው አለመግባባት ስለተመለሱ በባሕር ኃይል ላይ የግል ቂም ነበራቸው። ሃምሳ አለቃ ለገሠ አስፋው የደርግ አባል

ከሆኑ በኋላ የባሕር ኃይልን ኀብ'ኝተው ሲያበቁ ገና መኮንን ስላልነበሩ መኮንኖች ክበብ ውስጥ እንዳይገቡ ስለታገዱ የግል ቂም በባሕር ኃይል ሠራዊት ላይ ቋጥረው ነበር። ምንም ውስጥ አንገባም እያሉ የልብ ወለድ መጽሕፍትን የሚያነቡ መርከበኞችን የምዕራባውያንን መጽሐፎች ያነባሉ በሚል ሰበብ ረሸኑዋቸው። የኤርትራን ችግር ለመቋቋም የባሕር ኃይልን ማስፋፋት ቀርቶ ሞራላቸውን ለመግደል ባሕረኞቹ የመርከበኛ ልብስ እንኳን እንዳይለብሱ ተከልክለው የተፈቀደላቸው ከብዙ ዓመት በኋላ ነበር። በዚህም ምክንያት የባሕር ኃይሉ ብዙ የመከላከል ድርሻ ሊኖረው ሲችል ደካማ ተደረገ። ስለ ባሕር ኃይሉ መጠናከር ጉዳይ ውይይት በሚከፈትበት ጊዜ ሁሉ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አካባቢውን በጦር ሠራዊት አስጠብቀዋለሁ እያሉ ያውኩ ነበር።

በመሠረቱ በኤርትራ የነበረውን ችግር ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አይፈለግም ነበር። ምክንያቱም በመሃል አገር ተቃዋሚ ሲነሳ በሕዝብ እንዳይታቀፍ የገንጣዮች ተባባሪ ነው በማለት ለፕሮፓጋንዳ ስለሚጠቅም ነበር። እንዲያውም አዲስ አበባ ችግር የተፈጠረ ዕለት ማታ በቴሌቪዥን ኤርትራን በተመለከተ መግለጫ ይሰጥ ነበር። ሆኖም እየከበደ የመጣውን ችግር ለመወጣት የወታደሩን ብዛት ከመጨመራቸውም በላይ የአገሪቷን ቅሪት በጦር መሣሪያ ግዢ አባክነው በኃይል አጠፋቸዋለሁ ካሏቸው ነፃ አውጪዎች ጋር ተደጋጋሚ ዘመቻዎች አደረጉ። ከጦሩ ውስጥም አገር ወዳድ መኮንኖችን ለራሳቸው ሥልጣን ስለሚፈሯቸው ገና ሥልጣን ከያዙ ጀምሮ በየምክንያቱ ማስገደሉን ቀጥለው ነበር። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ብ/ጄኔራል ታሪኩንና ሌሎችንም እስገድለው የራሳቸውን ካድሬዎች ሥልጣን ላይ እያስቀመጡ የወታደሩን ሞራል ገደሉ። ብ/ጄኔራል ጌታቸው ናደው የኤርትራ ክፍለ ጦር አዛዥና የክፍለ አገሩ አስተዳዳሪን አዲስ አበባ አስጠርተው ቦሌ ያለው መኖሪያ ቤታቸውን አስከብበው በረንዳቸው ላይ ገና ብቅ ሲሉ ተኩሰው ገደሉዋቸው። ምክንያቱም ኤርትራ ያለው ጦር ውስጥ የነበረው የአየር ወለድ ይከዳል ተብሎ ስለተፈራ ነበር። አስከትሎም ቤተሰቦቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ልጃቸው የመቶ አለቃ ጳውሎስ ጌታቸውንም ሳይቀር አስረዋቸው ነበር። ሌላው ደግሞ የጦር ግንባር ሥራውን እየተወ እኛን ለጉብኝት ስንመጣ የማይቀበለን ንቆን ነው በማለት ተቆጥተው ብ/ጄኔራል ታሪኩን ሌላ ምክንያት በመስጠት ጦሩ ፊት



ራሳቸው ኮሎኔል መንግሥቱና የጦር ምኒስትሩ በወሰኑት ብቻ አስገድሉ። ኮሎኔል መንግሥቱም በዚህ ግድያ ሰበብ የወታደሩን ምላሽ ስለፈሩ ሰግተው ወደ ምጽዋ በመሸሽ ሁኔታውን መርከብ ላይ ኾነው ራቅ ብለው ሲያዳምጡ ቆይተው አደጋ ላይ የማይወድቁ መሆኑን ካጣሩ በኋላ ተመለሱ።

ኤርትራ ውስጥ የነበረው ጦር በጣም ከመሰቃየቱም ሌላ ወታደሩ ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ እረፍት ተሰጥቶን ስለማያውቅ ቤተሰቦቻችንን አላየንምና የዓመት ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ይመቻችልን ብሎ ወኪሎቹን ቢልክ የተላኩትን መልዕክተኞች አስረሸኗቸው። ወታደሩ መካከል ንዴት ቢኖርም መተማመን ስላልነበረ በኅብረት ያደረገው ነገር አልነበረም። በተገደሉት መኮንኖች ምትክ የተሾሙት ጄኔራሎች ገንዘብ እየተቀበሉ ወታደሩንና ጥቂት የቀሩትን ሃቀኛ መኮንኖች እሳት ውስጥ መጨመር ጀምረው በመጀመሪያ ምጽዋ ላይ የባሕር ኃይሉን ጦር አታለው የጠላት ጦር ግቢያቸው ውስጥ አስገብተው ሌሊት ባላሰቡት ወቅት አስፈጅተው ምጽዋን በነፃ አውጭዎች አስያዙ። ወታደሩ ብዙ ነገር ዓይቶ ተቀይሞና ተስፋ ቆርጦ ስለነበረ በሚቀጥሉት ዘመቻዎች አማራጩ መሸነፍና እጅ መስጠት ብቻ ኾነ።

መጨረሻ ላይ ጥቂት የቀሩት ጄኔራሎች መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ ተደማድመው ገና ሙከራ ሊያደርጉ ሲሉ ዘመኑ አሾክሻኪዎች የበዙበት ስለነበረ ተያዙ። በዚህን ጊዜ ኤርትራ ውስጥ የጦር አዛዥ የነበሩትን ጄኔራል ደምሴ ቡልቶን ወታደሩ አንገታቸውን ቆርጦ በአሥመራ ከተማ አዞረው። ጄኔራል ደምሴ ቡልቶ ከኮሪያ ዘመቻ ጀምሮ አገሪቱን በተለያዩ ዘመቻዎች ያገለገሉ ጀግና መኮንን ኾነው እያለ ገና ለገና የመንግሥቱን ሥልጣን ተቃውመዋል በመባል ያለፍርድ መገደላቸው የአረመኔ ሥራ መሆኑ ባይካድም ለመሪ ካድሬዎቹ ግን ይህ ዘግናኝ ተግባራቸው እንደ ጀብዱ ተቆጥሮላቸው ተሸመውበታል።

ብ/ጄኔራል ተሾመ ዕርገቱን ነፃ አውጭዎች ሲገድሉ መታወቅን አገኙበት። ተ/ጄኔራል ጌታቸው ናደውን ደርግ ሥልጣን እንዲያዘ ሲገድል ነፃ አውጪዎቹ ተስፋ አገኙ። ብ/ጄኔራል ታሪኩን ደርግ ሲገድል ደግሞ ሎቤ ረገጡ። የጄኔራል ቡልቶን ራስ ተቆርጦ በካድሬዎቹ አማካይነት አሥመራ ላይ ሲዞር የኤርትራ ነፃ

አውጭዎች ሕልማቸው እንደሚሰምር አረጋገጡ። ስለኾነም የኤርትራን ሕዝብ መገንጠል ያመቻቹት የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች መሆናቸው ግልጽ ነው።

በሌላም በኩል የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት በኤርትራ ነፃ አውጭ ሽምቅ ተዋጊዎች በመታገዝ ሽሬ ላይ ወታደሩን ድል አደረገው። የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩት የደርግ ተወካይ ባለሥልጣን በፊት የቀይ ሽብር የበላይ አስፈጻሚ የነበሩት የሻምበል ለገሠ አስፋው ዕውቀትም ብልጠትም ያልነበራቸውና ባልገባቸው ኮሙኒዝም የሰከሩ ስለነበሩ በ1981 ዓ.ም ትግራይን ለቀው ጦሩንና የመንግሥት ሠራተኞችን ወደ ወሎ አስተዳደር እንዲሄዱ አደረጉ። እሳቸውም ሸሽተው አዲስ አበባ ገቡ።

አፄ ዮሐንስ መሞቻቸው ሲቃረብ አንድ ቀን አፄ ምኒልክ በቅሏቸው ላይ ሲፈናጠጡ በሕልማቸው ስላዩ ዘውዱ ወደ ሸዋ መሄዱን አውቀውት ነበር። ታዲያ አፄ ዮሐንስ ሰዎች ሰብስበው "ዘውዱ ወደ ሸዋ ይሄዳል ግን ከመቶ ዓመት በኋላ ይመለሳል" ብለው ትንቢት ተናገሩ ይባላል። እንደ ትንቢቱም እሳቸው በ1881 ዓ.ም ሲያርፉ በ1981 ዓ.ም ደግሞ ሕውሐት ትግራይን ያዘ።

ከ1981 እስከ 1983 ዓ.ም የትግራይን አስተዳደር ደርግ ለሕውሃት ስለተወላቸው እነሱም ወታደር የሚመለምሉበትና የሚደራጅበት ስፊ አካባቢ አግኝተው በሰፊት ተዘጋጅተው የተማረኩ ወታደሮችን በማደራጀትና ሌሎች ነፃ አውጭዎችን በማስተባበር ኢሐዴግ የሚል ፓርቲ መሥርተው ወደ መሃል አገር በመግፋት አዲስ አበባን ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ያዙ። ለአገሬ እሞታለሁ እያሉ ይደነፉ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ለአምስት ዓመት ስደት መሄድ ለፖለቲካ ጥቅም ሲሉ የስም ማጥፊያ ዘመቻ እንዳላደረጉ ሁሉ በአይሮፕላን ወደ ብላቴ ለጉብኝት የሚሄዱ በማስመሰል ወደ ኬንያ ሸሹ። ከአገር ከወጡ በኋላ መኮብለላቸው ተገለጸ። አትፍረድ ይፈረድብሃል እንደሚባለው ኮሎኔል መንግሥቱም ተሰደዱና ይኸው እሳቸው ከንጉሠ ነገሥቱ የስደት ዘመን ከእጥፍ በላይ ቆዩ። ገና ስንት ዓመት በስደት እንደሚኖሩም ለማወቅ ያዳግታል። ቀደም ብለው ገንዘብና ንብረት ምንጣፍ እንኳን ሳይቀር አሸሽተው ወታደሩን በትነው መጥፋታቸው



የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሪዎቹ ላይ ዕምነት እንዲያጣ አድርጓታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ የሚናገሩትና የሚሰጡት ትችት እያስናቃቸው እየመጣ ነው።

የሚገርመው ነገር ስለ ኮሎኔል መንግሥቱ ወሬ ሲነሳ "እሱ አገር ወዳድ ነው! ቆራጥ ነው! ምንም ገንዘብ አይነካም! ብዙ ሥራ ሠርቷል!" የሚሉ ሰዎች መኖራቸው ነው። አንድ ሰው እንደምንም ብሎ የመሪነትን ሥልጣን ለመያዝ ከቻለ ደጋፊ፣ አድናቂ፣ ወይም አምላኪ እንደሚኖረው ብዙ አጋጣሚዎች አሳይተውናል። አገር መውደድ ማለት ባንዲራ መሳም ነው ወይስ አገር አስገንጥሎ መጥፋት ነው ወይስ ላይሞቱ እሞትልሻለሁ ብሎ መደንፋት ነው? የፖለቲካ ሰዎች ብዙዎቹ አይታወቅባቸውም እንጂ ሰውን ከማጥምንት አያርፉም። አሜሪካን አገር በምርጫ ወቅት ልጆችን ከእናቶቻቸው ጉያ እየተቀበለ የማይስም ምረጡኝ ባይ የለም። ከተመረጠ በኋላ ግን ልጅ ያለበት ቦታ አይደርስም።

አገር ወዳድነትስ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የነበሩት ባለሥልጣኖች ላይ በብዛት ታይቷል። አንዳቸውም እንኳን በንብረት ከአገር በማሸሽ አልተወነጀሉም። ብዙዎቹ እስር ቤት ኾነው ያሳስባቸው የነበረው ጉዳይ የእነሱ በግል እንደታሰሩ መገደል ሳይሆን በተፈጠረው የተዘበራረቀ የመንግሥት አስተዳደር ኤርትራ ትገነጠል ይሆን ብለው መጨነቅ ነበር። ደርግ ሁሉም ነገር በዘመቻና በኮሙኒስት አስተሳሰብ ብቻ የሚመራ ስለሚመስለው የኤርትራን ችግር በኃይል እፈታዋለሁ ብሎ ስላሰበ ጅቡቲን አስረክቢኝ ብሎ ከፈረንሳይ ጋር እንደመከራከር ለተባበሩት መንግሥታት አሳልፎ ሰጣት። አምባሳደር አቶ አሃዱ ሳቡሬ በወቅቱ በጅቡቲ የኢትዮጵያ በአምባሳደር ደረጃ ቆንሲል ጄኔራል የነበሩት ደርግ የጅቡቲን ጉዳይ እንዲያዘገይ ቢመክሩ ከሥልጣናቸው ተነስተው ታሰሩ። ጅቡቲን ፈረንሳይ ለኢትዮጵያ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ሆና ሳለ የኢትዮጵያ ኮሙኒስት መሆን ነገሩን ያበላሸ ይመስላል። የተባበሩት መንግሥታት በቅኝ ገዥዎች የተቋቋመ የእነሱን ሕልም የሚፈታ፣ የእነሱን ተግባር ሕጋዊ የሚያደርግ፣ ድርጅት መሆኑን እንኳን ባለመጠርጠር ደርግ የወሰደው እርምጃ ኢትዮጵያ ከነበራት ዕድል አንዱን አጣች። በመጨረሻም ኤርትራን ያስገነጠለው የደርግ መንግሥት ነው የሚባለው ወታደሩ የተበተነውና አገሪቱ የተገነጠለችው በደርግ ውድቀት ምክንያት ስለኾነ ነው።

ኤርትራውያኖች ወደድንም ጠላንም ኢትዮጵያዊ መሆናቸው የተፈጥሮ ሁኔታ እንጂ የፖለቲከኞች ጉንጎና ወይም የኃይል ማነስ የሚያስቀረውም ወይም የሚሰጠውም ፀጋ አይደለም። ስለኾነም አንድ ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን ወቅቱን ጠብቆ መዋሃዳቸው አይቀርም። ሶማሌዎች እንኳን ምንም የደቡብ ሕንድ ጎሣ ደም በመጠኑ የተደባለቀባቸው ቢሆኑም ከኢትዮጵያ ጎሣዎች አንዱ እንጂ የሶማሌ መንግሥት በቅኝ ገዥዎች የተፈጠረና የአንድ የጥቂር መንግሥትን ለመቦጫጨቅና አቅመቢስ መንግሥቶች እንዲኖሩ የጎነጎኑት ዘዴ ነው። ስለኾነም ጠቅላላው የአፍሪካ ቀንድ በጥቅሉ አንድ ኢትዮጵያ ተብሎ በሠላምና በመግባባት በጥሩ አስተዳደር አንድ ላይ እንደሚኖር አያጠራጥርም። አንዳንድ ግለሰቦች ሲቆጩ፣ የሚከተለውን ግጥም በመዝናኛ ቦታ ላይ ለአዝማሪ ይሰነዝራሉ።

እኛ እንደተማርነው በታሪክ ሲጣራ
ጅቡቲም የኛ ናት እንኳንስ ኤርትራ።

እንዲህ ዓይነቱ አባባል የራሱ ችግር ቢኖርበትም፣ ውስጠ ምስጢሩ ጅቡቲም ኤርትራም የኢትዮጵያ አካል መሆናቸውን ለመግለጽ ነው።



# ምዕራፍ ፳፮

## የሕዝብ ቅሬታዎች

የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን እንደሚወድ በብዙ አጋጣሚዎች ይንጸባረቃል። በአገር ውስጥ ያሉ ይቅርና በውጭም አገር የተደላደሉት ኢትዮጵያውያኖች ፖሊቲካው ላይ እጅግም ባይጠቅሙም ሲከራከሩ የሚውሉት ስለ አገራቸው ነው። አገር ተወረረ ሲሉት ኢትዮጵያዊ ህሉ ውድ ሕይወቱን ለመሰዋት አያወላውልም። ነገር ግን አገሪቱ ለእያንዳንዱ ዜጋ የምታደርገው ነገር በአንጻሩ ሲታይ ለዜጎችዋ ከምትሰጠው የነፃ ትምሕርት ሌላ እጅግም ነው። ሌሎችም ልማቶች በጣም ውስን ስለሆኑ ሕዝቡ እርካታን አላገኘበትም። እንዲያውም በሕዝቡ አመለካከት መንግሥት በግብር ስም ሕዝብን እየገፈፈ የሚኖር አካል አደርጎ ይመለከተዋል።

ቀደም ባለው ዘመን ወታደር የሚሞትለት ለአገሩ ሳይሆን ለአሳዳሪው ነበር። አሳዳሪው ከከዳ አበሮ ይከዳል፣ አሳዳሪው ከጠላት ከወገነ እሱም አብሮ ይወግናል። በዚህም አስተሳሰብ ይመስላል በጦርነት ላይ አሳዳሪው ከወደቀ ወታደሩ ይበተናል። ለምሳሌ አፄ ዮሐንስ ስለቆሰሉ ድል በማድረግ ላይ የነበረው ወታደር ሸሽት ጀምሮ ራሱንም አገሩንም ጎዳ። ጃንሆይ ከማይጨው ተመልሰው ወደ ውጭ አገር ስለሄዱ ወታደሩ ተበተነ። እንዲሁም በቅርብ ዘመን ኤርትራ ውስጥ ለኮሎኔል መንግሥቱ ታማኝ ለመምሰል የጦር አዛዡን የጄኔራል ደምሴ ቡልቶን ራስ ቆርጠ ሲዞር የነበረው ጦር አሳዳሪው ኮሎኔል መንግሥቱ ሲኮበልሉ ተፈታ።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ከአሳዳሪው አገር ትበልጣለች የሚል አስተሳሰብ በወታደሩ ልብ የሠረፀ ስለነበረ አሳዳሪውን ወንጅሎ ኢትዮጵያን ለማዳን ወታደሩ በዕውነተኛ አገር ወዳድነት ተነስቶ ነበር። ነገር ግን ሠራዊቱ ተመልሶ በሌላ አሳዳሪ እጅ ስለወደቀ የአዲሱ አሳዳሪ መገልገያ መሣሪያ ሆኖ ኖሮ መጨረሻ ላይ ተፈረካከሰ።

አገርን ከሁሉ በላይ አድርጎ የሚመለከትና ሲታገልም የኖረ ብዙም መከራ የተቀበለ ትክክለኛ ግን ብስለት የሚያንሰው ቡድን የተማሪ ኃይል ብቻ ነው። የተማሪ ኃይል ዕውነትንና አገርን መርህ የሚያደርግ አካል ስለኾነ ሁል ጊዜ ይኖራል ይታገላልም። አዲስ አሳዳሪ በመጣ ቁጥር የሚያጉላላውም ተማሪውን ነው። ተማሪው ግን መጀመሪያ ዴሞክራሲን በራሱ ላይ ቢያሰፍን ከተለያዩ የርዕዮተ ዓለም፣ የጎሣና የፖለቲካ ድርጅቶች መሣሪያነት ይድናል። ይኸንን ካላደረገ ግን አገርንም ወገንንም ከመጥቀም ይልቅ ጎጂ ይሆናል።

## ሥራ ፈትነት

በንጉሡ ነገሥቱ የመጨረሻው ዘመን ተምሮ ለሥራ ዝግጁ የሆነው ሥራ ለማግኘት ካለመቻሉም በላይ ከባላገር ወደ ከተማ የሚገባውና ከተማ ውስጥም አድጎ ለሥራ የሚደርሰው የሚቀበለው ድርጅትም ኾነ ግለሰብ ስለታጣ ሥራ ፈቱ እየበዛ ሄደ። በተለይ ከየባላገሩ የሚመጡት ወጣት ሴቶች የተዘጋጀላቸው ሌላ ሥራ ስላልነበረ መጠጥ ቤትና የዳንስ ቤቶች በብዛት ስለተከፈቱ እዚያው ሥራ ላይ ይሰማራሉ። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አስረሽ ምችው እየበዛ የሴትኛ አዳሪው ቁጥር ከመጨመሩም በላይ የአባለዘር በሽታ በጣም ተስፋፋ። መንግሥት የሴትኛ አዳሪን መኖር በይፋ ባይቀበለውም ትልቅ መቅሰፍት እየኾነ መጣ። ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ይህንን መቅሰፍት ለማጥፋት የጉልበት እርምጃ መውሰድ ጀምሮ ነበር። የኤኮኖሚን መቅሰፍት በቅጣት መቋቋም የማይቻል ስለኾነ የተሻሻለ ነገር አልተገኘም።

በዚሁ የመጨረሻ ዘመን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ብዙ ተፈታኝ ሲኖር አልፈሃል እየተባለ የሚነገረው ተማሪ ብዛት ዩኒቨርሲቲው ሊቀበለው የሚችለውን ቁጥር ያህል ብቻ ስለነበረ የወዳቂው ቁጥር ከሚያልፈው በጣም ጨመረ። ተማሪ ከፈተና ሲወድቅ የራሱም ኾነ የቤተሰቡ ክብር ስለሚነካ ሕይወታቸውን ያጠፉ ልጆች ብዙ ነበሩ። በኋላ ላይ ነገሩ ለሁሉም ግልጽ ሲሆን ራስ ላይ አደጋ ማስከተሉ ቀረ። አልፈሃል ግን ዩኒቨርስቲው ሊቀበል የሚችለው ከዚህ በላይ ያገኙትን ብቻ ነው እንደማለት መንግሥት ሲግደረደር የብዙ ልጆች ሞራል ተነካ። ለወዳቂዎቹም ሥራ የሚባል ነገር ሊገኝ አልተቻለም።



የኢትዮጵያ ትልቁ የኤኮኖሚ አውታር እርሻ ስለኾነ የመሬት ይዞታው ቢሻሻል ኖሮ ለብዙ ሰው ሥራ እንደሚፈጥር አያጠራጥርም። መንግሥት ግን የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም፣ ሕዝቡን ለመቆጣጠር ሲል የመሬትን ይዞታ ኢትዮጵያ ውስጥ ለዝንት ዓለም አልለቅም በማለቱ ድህነት ያማቀቀው ሕዝብ እንደኾነ ይኖራል። ደርግ ለችግሩ መፍትሄ የሚሰጥ መስሎት ጥቂት ባለርስቶችን ወርሶ በጠቅላላው የኢትዮጵያ መሬት ሁሉ የመንግሥት በመሆኑ እንዲያውም ጭራሹኑ ሕዝቡ መብት የሚባል ነገር እንዳይኖረው አደረገ።

## ኤምባሲዎች

የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በውጭ አገር የመሪዎችን ዝና ለማስተጋባት እንጂ የኢትዮጵያዊ ግለሰቦችን ችግር ለማቃለል ወይም የአገሪቷን ጥቅም ለመጠበቅ ተብለው የተመሠረቱ አይመስሉም። ስለሆነም አንድ ኢትዮጵያዊ ፓስፖርቱ እንዲታደስ ሲጠይቅ ከማደስ በስተቀር ኢትዮጵያዊውም ወደ ኤምባሲው የሚሄድበት ምክንያት የለውም፣ ኤምባሲውም እንዲመጡበት አይፈልግም። ኢትዮጵያውያን ኤምባሲዎች በሊሉባቸው አገሮች እንደሚኖሩና የመኖሪያ ፍቃድና የፓስፖርት ማሳደስም ችግር እንዳለባቸው እየታወቀ ፓስፖርቱ ለአምስት ዓመት መታደስ ሲችል ከሁለት ዓመት በላይ በምንም መልኩ አይታደስም። እንዲያውም አንድ ኢትዮጵያዊ በሌሎች ብዙ አገሮች የሌለ ችግር ተጥሎበት እንደ እስረኛ ከአገሩ ለመውጣት ቪዛ ያስፈልገዋል።

በንጉሡ ዘመን ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በጣም ያነሰ ስለነበረ ይህ ሃቅ አይታወቅም ነበር። ብዙ ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን በጨረሱ ማግስት ወደ አገራቸው ስለሚመለሱ አንዳንድ በመርከብ ተደብቀው ከሄዱ ኢትዮጵያውያን በስተቀር እጅግም የሚያሳስብ ብዛት ያለው ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ አልነበረም። በጎረቤት አገሮች በአረብ ነጋዴዎች በባርነት ተዘርፈው የሚሸጡትን ኢትዮጵያውያን ቁጥር ለማወቅም ኾነ ነገሩን ለማንሳት የፈለገ የመንግሥት አካል አልነበረም። አንድ ኢትዮጵያዊ በሌላ አገር ውስጥ ቢበደል መንግሥት ለግለሰብ ብሎ ከሌላ መንግሥት ጋር ሙዝግብ ውስጥ አይገባም። ስለሆነም ኢትዮጵያውያን በጎረቤት

አፍሪካና በየአረቡ አገር እንደተጉላሉ ነው። ብዙ አገሮች ግን ስለዜጋቸው መብት ትግል ያደርጋሉ። በተለይ እሥራኤልና አሜሪካ ለአንድ ዜጋ መብት ብለው ጦርነት እስከማንሳት ይዳዳቸዋል።


በጠቅላላው የኤምባሲ ሰዎች ሊያደርጉ የሚችሉትን ያህል እንኳ ለማድረግ ቅንነቱ የላቸውም። አቶ ሕይወት ኀዳሩ "የቺ ቀን ተረሣች" በምትለው መጽሐፋቸው ላይ በሳቸው የደረሰውን በገጽ 7 ላይ እንደሚከተለው አትተዋል። "መጋቢት 16 ቀን 1924 ዓ.ም በአሥመራ ወደ ቆንስላችን ሂጄ በፓስፖርቱ ላይ ወደ ሱዳን ለመግባት የሚያስችለኝ ይጻፍልኝ፣ ለአሥመራ ባለሥልጣኖችም እንዲጻፍልኝ ይደረግልኝ። እዚያ ሂጄ ትምሕርቴን ለመቀጠል እፈልጋለሁ ብላቸው ቆንሲሉ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ "ወደ አዲስ አበባ ብትሄድ ይሻላል" ስላሉኝ• "አዲስ አበባ የሚያደርስ ገንዘብ የለኝም" ብላቸው "ልብስህን ሸጠህ ሂድ" ያሉኝም ትዝ አለኝ" ብለው አውስተዋል። አሁንም ቢሆን ከዚህ የተለየ ነገር ከኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አይጠበቅም።

ኤምባሲዎቹ የመሪውን ፎቶግራፍ በግርግዳ ላይ ከመስቀላቸው በስተቀር ስለአገሪቱ ለመመራመር የሚፈልግ ሰው እንኳን ቢጎበኛቸው የሚያሳዩት ምንም ነገር አብዛኞዎቹ የላቸውም። የኤምባሲው ሠራተኞችም ቀርበው የሚያነጋግሩት እንኳን ራሱን የቻለውን ኢትዮጵያዊ እንጂ ሌላውን አያቀርቡትም።

የየኤምባሲዎቹም የውስጥ ይዞታ የሚያኮሩ አይደሉም። በእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ የሚደረደሩት መቀመጫዎች መናኛ ከመሆናቸውም በላይ በጣም ያረጁ ወይም የወላለቁ ናቸው። ክፍሉ ንጽሕናው በሥርዓት አይጠበቀም። የመዋኛ ቦታ ያላቸው እንኳን ውሃውን በንጽህና መያዝ ስለማይችሉ ገንዳውን ባዶ ይደረጋሉ። የሠራተኞቹም ቋንቋ ችሎታ በውጭ አገር ላለ ኤምባሲ ሠራተኛነት እንደማይመጥኑ ያስረዳል። የሌላ አገር ዜጋ የኤምባሲው ሠራተኞችም ሁኔታዎችን በማገማመት ኢትዮጵያውያን ሲመጡ አለባበሳቸውን አገናዝበው እስከመከልከል ይደርሳሉ። ስለሆነም ካልተገደደ በስተቀር አንድ ኢትዮጵያዊ ወደ ኤምባሲው የመሄድ ሕልም እንኳን የለውም። ብዙ ኢትዮጵያውያን ለጉብኝት አንድ አገር ሲሄዱ ምናልባት የኢትዮጵያ አየር መንገድን ቢሮ ወይም ዛሬ ጊዜ



ደግሞ የባህል ምግብ ቤትን ሄደው ይጎበኙ እንደ ኾነ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የት ነው ብለው እንኳን አይጠይቁም።



በ1922 ዓ.ም የተሾሙ አምባሳደሮች በማዕረግ ልብሳቸው
በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ ፊትለፊት (አሁን የግብጽ ኤምባሲ)

ይህን ሁኔታ ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ያለፈውን መንግሥት ለመውቀሻ ተጠቅሞበታል። ነገር ግን ደርግ የባሰውን ሰው ማሸሽ ጀመረ እንጅ ያሻሻለው ነገረ አልነበረም። እንዲያውም በውጭ አገር ነዋሪው እየበዛ የሄደው ደርግ በሰው ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን ስቆቃ በመሸሽ ስለነበረ ኤምባሲው ዘንድ የሚመጡት ኢትዮጵያውያኖች ሁሉ የመንግሥት ጠላት እየመሰሏቸው ሠራተኞቹ ይሸሹ ነበር። ቀደም ብሎ ሌሎች አፍሪካውያኖች ኢትዮጵያዊ ነን ማለት እንዳልሞከሩና ኢትዮጵያዊነት እንዳላኮሩ ሁሉ በደርግ ዘመን አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ያለውዴታቸው ፓስፖርታቸውን እየመለሱ የሌላ አገር ዜግነት የወሰዱትም ኢትዮጵያዊነታቸው ሊያስከብራቸው ባለመቻሉ ይመስላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በውጭ እየበዛ ሲሄድ የታየው ሁኔታ በአገሩም በውጭ አገርም መብቱ አለመከበሩን ነው።

እንደነአሜሪካ ኤምባሲ የመሳሰሉ በአገራችን ያሉት የሌላ አገር ኤምባሲዎች ግን ሲፈልጉ ከአጥራቸው ውጭ ያለውን መንገድ ይዘጋሉ ወይም እንደ እንግሊዝ ኤምባሲ ያሉት በነፃ የተሰጣቸው ፈረስ የሚያስጋልብ መሬት እያላቸው ቪዛ የሚጠይቃቸውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ አውራ መንገድ ላይ በዝናብና በፀሐይ ላይ ሲያሰልፉት ለሌሎች ዜጎች ቅድሚያ በመስጠት የበለጠ ክብር ይሰጡዋቸዋል። አፄ ምኒልክ ሰፊ መሬት የሰጧቸው ለኤምባሲ አገልግሎት እንጂ ለፈረስ መጋለቢያ አልነበረም። ለዚያውም በምትኩ ለንደን ላይ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ያደረጉት ነገር የለም። የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በተለይም በለንደን የሚገኘው አንድ አፓርትሜንት ውስጥ በኪራይ ሲኖር ገና ለገና የእንግሊዝ መንግሥት ያኮርፋል ተብሎ ቅኝ ግዛቶቻቸው ከነበሩት አገሮች ባነሰ ሁኔታ ቢመለከቱንም ክብራችንን ለማስጠበቅ አልደፈርንም። የሚሰጡን ዕርዳታ ከድህነት የሚያወጣን ስላልሆነ በድህነት ከነክብራችን ብንቀመጥ ይመረጣል።

አልፈው ተርፈው የኢትዮጵያ ዜጋን ገብቶ እንዲያነጋግራቸው እንኳን የተለየ ገንዘብ ሲያስከፍሉ ተዉ የሚላቸው አልተገኘም። የሚያስከፍሉት ገንዘብ ቤት የሚያሸጥ ሲሆን ጉቦም በመቀበል የተባረሩ ሠራተኞች እንደነበሯቸው ይታወቃል።

## የኑሮ ውድነት

ኢትዮጵያውያን በመደጋገፍ የሚኖሩ እንጂ አንዱ እየበላ ሌላው ፍግም የሚልበት ዓይነት አኗኗር ባሕላቸው አይደለም። ስለሆነም አንድ ሥራ ያለው ሰው ቢያንስ በቤቱ ሌላ አምስት ሰው ያስተዳድራል። ለዚህ ነበር ክቡር አቶ መኮንን ሃብተወልድ አንድ ሠራተኛ ምንም ቢያጠፋ ከሥራ የማያስወጡት።

ገንዘብ የመግዛት ኃይሉን በየዓመቱ ስለሚቀንስ የዕቃ ዋጋ እየናረ እንደሚሄድና የሰውም ፍላጎት እየጨመረ እንደሚሄድ የታወቀ ሲሆን በሥራ ላይ ያለው ሰው ደመወዝ ግን በዛው ልክ እየጨመረ ለመሄድ አልቻለም። ስለዚህ በየቤቱ ሁሉም ማጉረምረሙ ባይቀርም ሊያሻሽለው ስለማይችል ችግሩ ሲገነፍል ሁሉም የራሱን ችግር እየተገነዘበ አብሮ እሮሮውን ማሰማት ይጀመርና ሁኔታውን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ይሆናል።



ኢኮኖሚውን የሚያሻሽል ሥራ እንደመሥራትና ችግሩን ከመሠረቱ ለማረም ከማሰብ ይልቅ መንግሥት ኃይል በመጠቀም ብቻ ለመቋቋም ምርጫው ስለሚሆን ለዚሁ ጉዳይ የሚውሉ ልዩ የወታደር፣ ፖሊስና የጸጥታ ኃይል እያቋቋመ ገንዘቡን ችግር ፊቺ ባልሆነ ነገር ያባክነዋል።

## የዓለም አቀፍ ቢሮዎች መከፈት

በወቅቱ ተሠራ ተብሎ እንደትልቅ ነገር የሚጠቀሰው የተባበሩት መንግሥታት የኤኮኖሚ ኮሚሽንና የአፍሪካ አንድነት ማኅበር መቋቋምና ዋና ጽሕፈት ቤቱ ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ አበባ ላይ መሆኑ ነው። ክቡር አቶ አዲስ ዓለማየሁ በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ አምባሳደር በነበሩበት ወቅት ይህንኑ ቢያሳስቡም የሚሰማቸው ጠፍቶ በነገሩ ተናደውበት ነበር። በኋላ ግን በብዙ ድካም ጽሕፈት ቤቱ አዲስ አበባ እንዲሆን በተቻለበት ወቅት የሳቸውን ስም አንስቶ ያመሰገናቸው ሰው አልነበረም። የቢሮው መከፈት ጥሩ ሆኖ ሳለ ምናልባት ይህ ጉዳይ መጨረሻ ላይ ትኩረት የተሰጠው የንጉሠ ነገሥቱን ዝና ክፍ የሚያደርግ መሆኑ ስለታመነበት ይመስላል። መቼም የተሠራ ነገር ጥሩ ነውና ድርጅቱ መቋቋሙና አዲስ አበባ ውስጥ መሆኑ ንጉሠ ነገሥቱንም ኢትዮጵያንም የሚያስመሰግናቸው ሆኗል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ባላት ታሪክና ለእንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ የአፍሪካ አገሮች አማካይ በመሆኗ ምክንያት ይህ ማዕረግ ስለሚገባት ነው። ለተራበው ሕዝብ ግን የጽሕፈት ቤቱ አዲስ አበባ በመሆኑ የኑሮ መሻሻል ሊያመጣለት አልቻለም። እንዲያውም ስብሰባ በሚደረግባቸው ቀናት ሁሉ ድሃው ከከተማ እየታፈሰ የተከለለ የጥበቃ ቦታ ውስጥ (Concentration Camp) መታሰር ወይም መታጎር ብቻ ነው የተረፈው። የጥበቃውም ቦታ ብየካ መንገድ እሥራኤል ኤምባሲ ፊት ለፊት ባለው ግቢ ውስጥ ነበር። በኋላም ድሃውን ሌሊት እየሰበሰቡ እየወሰዱ አልታወቀ ቦታ መጣል ኾኖ ነበር።

መጀመሪያ ላይ ለፖስታና ለቴሌኮሙኒኬሽን ፍጆታ ከተባበሩት መንግሥታት ቢሮዎች የሚገኘውም ገቢ ቀርቷል። ምክንያቱም ዘመን አመጣሹ ኩርየር ሰርቪስ የፖስታ ቤቱን ገቢ ሲያስቀረው በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኋላ ቀርነት የተነሳ ቀጥታ ግንኙነት በሳታላይት በመጀመራቸው ነው።

ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሥራ የሚመደቡ ሰዎች ደርግ በፈጠረው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት በጥቁር ገበያ ሕዝቡን መግፈፍ ችለዋል። በተጨማሪም ለዲፕሎማቶች በተሰጠው ካለቀረጥ የመግዛትን መብት በመጠቀም ሸቀጥ ለነጋዴዎች በማቅረብ ተጠቃሚ ሆነዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ለመመደብ ባለው ሽኩቻ በአፍሪካ ሕብረት መሥሪያ ቤትም ሙስና እንደ ተጀመረ ሹክሹክታ ይሰማል።

## ሰብዓዊ መብት ያለመጠበቅ

ኢትዮጵያ ውስጥ እያንዳንዱ ዜጋ ግዴታውን መፈጸም ይጠበቅበታል። በአንጻሩ ግን ስለመብቱ ደፍሮ ቢያነሳ የሚተርፈው ድብደባ ነው። የመንግሥት ባለሥልጣን የሕዝቡ አገልጋይ መሆኑ ይቀርና የሕዝቡ ጌታ መስሎ ይታያል። አንድ ሹም ሥልጣኑን የሚያገኘው በሹመት እንጂ በምርጫ ካለመሆኑም በላይ ከደረሱ ደረጃ ከፍ የሚለውም ከበላዩ ላሉት ሹማምንት በሚያሳዩቸው ታማኝነት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ባደረገው ተጋድሎ እስካሁን መሪውን በሌላ መሪ ማስለወጥ ቻለ እንጂ የተነሳበት ዓላማ ገና አልተሳካለትም። በጠረኞች የሚተዳደር ሕዝብ እንደመሆኑ አልገዛም በሚልበት ጊዜ በጭካኔ ሲደበደብ የኖረ ስለኾነ በወገኑ በጣም ተበድሏል።

## የፍትሕ መጓደል

የመንግሥት አንዱ ትልቁ ሥራው ለሕዝብ ፍትህ መስጠት በመሆኑ ጃንሆይ በፊት የሚሠራበትን ኋላ ቀር አሠራርን በዘመናዊና በቀለጠፈ አሠራር ተክተውታል። ሕግ አስረቅቀው ሕገ መንግሥት አውጀው ፍርድ ቤቶችን አሠርተው ዳኞችን ሰይመው ዘመናዊ አሠራር ተግባር ላይ ዋለ። በነህልም መሠረት ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ያስችሉ ነበር። የሞት ፍርድንም ንጉሠ ነገሡ ካላጸደቁ አይፈጸምም። ፍርድ ቤት የሚመላለሰው ሰው ብዛትና በቀጠሮ የሚጉላላው ሰው መጨረሻ ለይ እየበረከተ ሄደ። በዚህ ላይ ደግሞ በባለሥልጣኖች ግፊት የሚበደለው ሰው በመብዛቱ ሕዝቡ



አልተደሰተም ነበር። ከዚህም በላይ ከሕግ በላይ የነበሩ ሰዎች ተግባር ሕዝቡን ለምሬት ዳርጎታል።

ለምሳሌ ያለፍርድ ለ27 ዓመት የተጋዙት አፈ ንጉሥ ገብረ መድኅን አባታቸው በዘመቻ ሰባት ቦታ ላይ በጥይት ቆስለው የዳኑ ጠረኛና ጀግና ነበሩ። አፈ ንጉሥ ገብረ መድኅን የባለውለታ ልጅ ከመሆናቸው በላይ ራሳቸውም በጠላት ጊዜ የውስጥ አርበኛ የነበሩ ጠንካራና የተማሩ ሰው ነበሩ። በዚህ የተነሳ የአርበኞች ማኅበር ሊቀ መንበር ሆነው ነበር። አፈ ንጉሥ ገብረ መድኅን ከጣሊያን ወረራ በኋላ የሜዳሊያ ሽልማት ሲደረግ አርበኛና ስደተኛ እንዴት አንድ ዓይነት ሜዳሊያ ይሸለማል ብለው ተቃወሙ።

አፈ ንጉሥ ገብረ መድኅን የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዴንት በነበሩበት ወቅት መንግሥት አንድ ብይን እንዲሽሩለት ቢጠይቃቸው እምቢ ብለው ፍርዱን ስላጸደቁ ኢሊባቦር ለሥራ ታዘው እንደሄዱ ደጃዝማች ጣሰው ዋለሉ እንዲያሥሯቸው ተደረገ። ያለፍርድ ከ1939 ዓ.ም አንስቶ 5 ዓመት ከታሠሩ በኋላ በተሞከረው የመንግሥት ግልበጣ ላይ ከተሳተፉ ሰዎች ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው በማስመሰል አስወሩባቸው። የኾነው ሆኖ ያለፍርድ 27 ዓመት ታሥረው ቆዩ። በእሳቸው ምክንያት የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ሚስተር ዳግ ሃመር ሾልድ በጉዳዩ ብዙ እንደተጻጻፉበትና እንደ ደከሙበት ቢታወቅም ምንም ሊደረግ አልተቻለም። ከእሥር ተፈተው ጥቂት እንደቆዩና ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ጋዜጠኛ ጥያቄ ሲያበዛባቸው "ወሮበላ ሁሉ! የእኔን ኢንተርቪው ለፖለቲካችሁ መጠቀሚያ ልታደርጉት አትችሉም" ብለው ስላባረሯቸው ደርግ ተቀይሞ ጡረታቸውን ከልክሏቸው እንደተንገላቱ በእርጅና ሞቱ።

አፈንጉሥ ገብረ መድኅን ጃንሆይን በግል ተቃውመው አያውቁም። ሥራቸውን በሚሠሩበት ጊዜ ትክክል ያልሆነ ትዕዛዝ ሲደርሳቸው ኅሊናቸው የሚቀበለውን ብቻ በመሥራታቸው ለብዙ ዓመት ያለፍርድ ታሰሩ። ወዳጆቻቸው የሆኑ ሰዎች ጃንሆይን ነባክዎ ምሕረት ያድርጉላቸው ብለው ቢጠይቋችው "ለመቼ ቀን ሊሆነን ነው?" ብለው በመናገር የራሳቸውን አመለካከት ብቻ የሚያራምዱ መኾናቸውን በይበልጥ አንፀባረቁ።



አፈንጉሥ ገብረ መድኅን ከሃያ ሰባት ዓመት እሥር በፊትና በኋላ

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ያለፍርድ የታሠሩና የተገላሉ ሰዎች ቁጥር በርካታ ነበር። በተለይ የባላባት ልጆች ይፈሩ ስለነበረ አደብ ገዝተው ያልተቀመጡ ተገላልተዋል። ለምሳሌ የራስ ኃይሉ ልጅ የነበሩት ፊታውራሪ አድማሱ ኃይሉ ያለፍርድ ታሥረው እግራቸውም ተቆርጦ በእንግልት ኖረው ሞተዋል። ፊታውራሪ አድማሱ ኃይለኛ ሰው እንደነበሩና ጃንሆይ የታሠሩበት ቦታ ሊጠይቋቸው ቢሄዱ "ምን ልታደርግ ነው የመጣኸው!" ብለው በንዴት አጠገባቸው የነበረውን የአምቦ ውሃ ጠርሙስ ወርውረው ስተዋቸዋል። "አህያ ማሠሪያዋን በጠሰች የምትግጠውን ሳር አሳነሰች" እንዲሉ ሰውየው ርቀው እንዲታሠሩ ተደርጎ በዚያው ሞቱ። በልጃቸው ጠንቅም ራስ ኃይሉ ለማሊያን ባንዳ ሆነው ከተወረሰው ንብረታቸው የቀረችውን እንደገና ስለተወረሱ መጨረሻ ላይ በድህነትና በሃዘን ኖረዋል። ራስ ኃይሉ አንድ ቀን እንደሚከተለው እንጎራጉሩ ይባላል።

እኔ ተው እያልኩህ አንተ እየተቆጣህ
ለኔም መቀመጫ ላንተም መቆሚያ እጣህ



# ምዕራፍ ፳፯

## ራስ ተፈሪያን

በጃማይካ ደሴት የሚኖሩ ጥቁሮች በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አንድ አፍሪካዊ ንጉሥ ይመጣል የሚል ከአካባቢያቸው ፖለቲካ ጋር የተቀላቀለ ሃይማኖት መስበክ ጀምረው ነበር። ለነገሩ ከፖለቲካ የጸዳ የሃይማኖት አመራር በምድር ላይ የለም።

እምነቱ ብሉይ ኪዳንን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ ከመናገራቸውም ሌላ እኛ ጥቁሮች ሃጢያተኛ አይሁዶች ነን፤ እግዚአብሔር እንደገና የፈጠረን ሊቀጣን ፈልጎ ሲሆን በሚልክልን ንጉሥ አማካይነት ወደ ገነቷ አፍሪካ በነፃነትና በምሕረት እንመለሳለን ብለው ያምናሉ። እንዲሁም ራስ ተፈሪ ሕያው አምላክ ናቸው ይላሉ። ጥቁሮች ወደ ቃል ኪዳን ምድራቸው ኢትዮጵያ መመለሳቸው አይቀሬ ቢሆንም የመመለሻው ጊዜ የሚወሰነው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ነው ብለው ይጠባበቃሉ። ኢትዮጵያ በሚለው ስያሜ ላይ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች በመስጠታቸው በመካከላቸው ልዩነት አለ። ከፊሎቹ ኢትዮጵያ እናት አገራቸው መሆንዋን ሲያምኑ የተቀሩት ደግሞ ኢትዮጵያ ማለት ያው መላው አፍሪካ ማለት ነው ይላሉ። በጠቅላላው የሚስማሙበት ጉዳይ ግን ኢትዮጵያ የተስፋ ምድር መኾንዋን ነው። የአመላለሱ ሁኔታ ለእውነተኞቹ አማኞች ካልሆነ ለተቀረው ሕዝብ ምስጢር ነው። ይሁንና ጃንሆይ ሻሸመኔ አካባቢ ለራስ ተፈሪያን አማኞች መሬት ስጥተው እዛው ኑሮ የጀመሩ እንደአሉ የታወቀ ነው።

የአፍሪካ አገሮች በሙሉ በቅኝ ገዥዎች ተይዘው በነበሩ ጊዜ ነፃ አገር ተብለው የሚታወቁት ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ብቻ ነበሩ። ላይቤሪያ ከአሜሪካ የሚመለሱ ጥቁሮች የሚሰፍሩባት አገር ስለነበረች የቅኝ ገዥዎች ሊይዟት አልደፈሩም። ኢትዮጵያ ግን የመጣውን የነጭ ኃይል ድል አድርጋ ወግና ሥርአቷን ጠብቃ ከነክብሯና ማዕረጓ የምትኖር

ከመሆኗም በላይ እንደሌሎች ጥንታዊና ታሪካዊ አገሮች የራሷ የኾነ የንግሥና ወግ ያላት የጥቁር መንግሥት ሆና ተገኘች።

በ1916 ዓ.ም ራስ ተፈሪ መኮንን የአውሮፓን አገሮች በመጎብኘታቸው የተነሳ ስማቸውም እየታወቀ ሲሄድና እንዲሁም ንግሥና በኢትዮጵያ ታሪክ ከእሥራኤል ንጉሦች ከዳዊትና ሰሎሞን ጋር በመያያዙ በጃማይካ ያሉት የአዲሱ ፖለቲካዊ ሃይማኖት ምሁሮች 'ይህ የምንጠብቀው መሲህ ራስ ተፈሪ ነው፣ እኛም የራስ ተፈሪ ተከታዮች ነን' ብለው ማስተማር ጀመሩ። በተለይ የሃይማኖቱ ንቅናቄ መሪ ማርከስ ጋርቬይ ሲሆን ሌሎችም አስተማሪዎች ተነስተው ዕምነቱን በማስፋፋት ከጃማይካ ድንበር አልፎ በሌሎች አገሮችም ተስራፉ።

ከሥርዓታቸውም አንዳንዶቹ የምግብ ሕግ ሲሆን ሥጋ አለመብላትን ይጨምራል። ጠጉርንና ጺምን ማሳደግና ጋንጃ ብለው የሚጠሩትን ሃሺሽ (ዕጸ ፋሪስ) ማጨስ ይፈቅዳል።



ማርከስ ጋርቬይ

ራስ ተፈሪያኖች በጥሩው ዘፈናቸው ስሜት ያነሳሳሉ። ስለኾነም የታወቁት የጃማይካ ዘፋኞች ቦብ ማርሊን ጨምሮ ራስ ተፈሪያን ናቸው።

ማርከስ ጋርቬይ የንጉሠ ነገሥቱ በጣልያን ጦር ተሸንፈው መሰደዳቸው በጣም ያስቆጣው ነገር ነበር። እንደገና በድል ከተመለሱም በኋላ እንዲሁ እንዳወገዛቸው ሕይወቱ አለፈ።

ጃንሆይ የጃማይካን አገር ለመጎብኘት በሄዱ ጊዜ ዝናብ ጠፍቶ ከርሞ ልክ እሳቸው ከአይሮፕላን ሲወርዱ ስለዘነበ ሕዝቡ ዕውነትም ቅዱስ ናቸው ብሎ በበለጠ እምነቱን አጠናከረ። በዘመኑ ጃማይካ በእንግሊዝ ሥር ስለነበረች አገረ ገዥው አይሮፕላን ውስጥ ገብቶ ለጃንሆይ "ሕዝቡ በእርስዎ መለኮትነት ያምናል። ስለኾነም መለኮት አለመሆንዎንና ሰው መሆንዎን ይናገሩ" ቢላቸው "ተዋቸው በፈለጉት ይመኑ" ብለው ነገሩን ዘግተውታል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአሜሪካንን አገር ሲጎበኙ በራስ ተፈሪያን አማኞች እንደመሲህ በመታየታቸው ምክንያት



ጋዜጠኞች "ነቢይ ነዎት?" ብለው ቢጠየቋቸው አለመሆናቸውን ተናገሩ።

በጃማይካ ጉብኝት ወቅት እሳቸውን ለመቀበል በተደረገው ሥነሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በብዛት ሲውለበለብ ዓይተው የእምነቱ ተከታዮች መለያ ቀለም ቀይ ብጫና አረንጓዴ እንዲሆን አድርገውታል። በቅርቡ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን በመመልከት አረንጓዴውን ከላይ ማድረግ ጀምረዋል። የኢትዮጵያ ባንዲራ እስከ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ቀዩ ከላይ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ አረንጓዴውም ከላይ ቢሆን ሁለቱም ተቀባይነት ነበራቸው። ራስ መኮንን ጣሊያን አገር ሄደው በነበረበት ወቅት ሦስቱ ቀለማት ተለያይተው መውለብለባቸው ቀርቶ በአንድነት መያያዝ እንዳለባቸው ተገንዝበው ወደ ሐረርጌ ሲመለሱ አረንጓዴውን ከላይ አድርገው በአንድነት ሦስቱን ቀለሞች በመስፋት ማውለብለባቸው በአፄ ምኒልክ ዘንድ ተሰማ። አፄ ምኒልክ ይኸንኑ በመቀበላቸው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ሆነ። ከጊዜ ብዛት የቦሊቭያ ባንዲራ ቀዩ ከላይ መሆኑ ሲታወቅ ኢትዮጵያ በምትመዘገብበት የዓለም አቀፍ ማኅበሮች ሁሉ ይኸው አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ረድፍ የጸና ሆኗል።


ጃንሆይ በመሠረቱ የኢትዮጵያ ባንዲራ በሊጣው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ መሆኑን እምነውበት ቀጥለውበታል። ይህም ማለት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ብቻ እንደነበረ ነው የምንረዳው። የጃንሆይ መንግሥት ለብዙ ተቋሞች ዓርማ፣ ምልክትና ሰንደቅ ዓላማ ሲሰጥ ለቤተ መንግሥቱ የይሁዳ አንበሳ ምልክት ቢጫው ቀለም ላይ ተደረገ። ስለሆነም ቤተ መንግሥት ውስጥና ጃንሆይ መኪና ላይ የሚውለበለበው ሰንደቅ ዓላማ ላይ የአንበሳውን ምስል ቢጫው ላይ ማድረግ ተጀመረ። በዓለም መንግሥታት በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማነት የተመዘገበውና የሚታወቀው ግን ሦስቱ ቀለማት ብቻ ነው። ደርግ ግን ዋናው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሕብረተ ሰብዓዊት ኢትዮጵያ መንግሥትን ዓርማ ጨመረበት። እንደዚሁም ኢሕአዴግ ደግሞ የደርግን ምልክት አንስቶ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥትን ዓርማ አደረገበት። ስለኾነም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያለው ዓርማ የባንዲራው አንዱ አካል ተደርጎ ስለሚቆጠር ሌላ አገር ሦስቱን ቀለም ብቻ በሊጣው የእኔ ሰንደቅ ዓላማ ነው ብሎ ቢነሳ ለመከላከል ያስቸግራል። ለምሳሌ የቦሊቪያና የጋና ሰንደቅ ዓላማ አንድ ዓይነት

ሲሆኑ የጋናው ከቦሊቪያው የሚለየው መሃከሉ ባለው ጥቁር ኮከብ ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት አቡነ ባስልዮስ እስከ አቡነ መርቆርዮስ ድረስ ምልክታቸው አረንጓዴ ቀለም ላይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከነፈረሱ ይሳልበትና ዙሪያው በወርቅ አዘቦ መርገፍ የተከበበ ስለነበረ በመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ጽሕፈት ቤትና መኖሪያ ቤት እንዲሁም መኪናቸው ላይ የሚውለበለበው ይኸው ባንዲራ ነበር።

በ1967 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ከሥልጣን ወርደው ታስረው ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ተገድለው፣ ቀብራቸው በምስጢር ከመፈጸሙ የተነሳ የራስ ተፈሪያን አማኞች መሲሁ አልሞተም፣ አልተቀበረም፣ አረገ እንጂ፣ ብለው ያምናሉ። ለሚከራከራቸውም ከብሉይ ኪዳን ይጠቃቅሳሉ። ዛሬ እጅግ የተዋበ የንጉሠ ነገሥቱ ፎተግራፎችና የይሁዳ አንበሳ ያለበት የኢትዮጵያ ባንዲራ በብዛት የሚሰራጨው በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በካሪቢያን ደሴት አገሮች ተንሰራፍተው በሚገኙት በራስ ተፈሪያን ሱቆች ውስጥ ነው።

በጃማይካኖችና በኢትዮጵያውያን መካከል በዚሁ አዲስ ሃይማኖት ምክንያት መቀራረብና መወያየት ስለተጀመረና ኢትዮጵያውያን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሰውነት ሰበዓዊ ፍጡርነት አበክረው በማስገንዘባቸው ለማይጠራጠሩ ብዙ ጃማይካኖች ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በመቀየር በክርስትና ሃይማኖት እየተጠመቁ ይገኛሉ። ቤተክህነት ግን የቅዱስ ያሬድን ቅዳሴ በእንግሊዝኛ ባለማዘጋጀቷ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት በሌላው ዓለም ለማስፋፋት ያላሰበችበት መሆኑን ያሳያል።





# ምዕራፍ ፳፫

# ሃይማኖትና ንጉሠ ነገሥቱ

ተፈሪ መኮንን የተወለዱት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ቤተሰብ ነው። በዘመኑ ይደረግ እንደነበረው እንደ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ቤተ ሰብ ልጁን ትምሕርት የሚያስጀምረው በሃይማኖት አባት መምህርነት እንደመሆኑ መጠን ተፈሪም በራስ መኮንን መኖሪያ ቤት አባ ወልደ ኪዳን የሚባሉ መምህር ተቀጥረውላቸው ፊደል ቆጥረውና የጸሎት መጽሐፍቶችን በአማርኛና በግዕዝ ማንበብና መጻፍ ተምረዋል። አሥር ዓመት ሲሞላቸው አባ ሳሙኤልና ዶክተር ቪታሊያ በተባሉ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች የፈረንሳይኛ ቋንቋ ደህና አድርገው ተማሩ። ተፈሪ ወደ መንግሥት ሥልጣን ላይ የወጡት የሁለት ዓይነት ዕምነት ተከታይ አስተማሪዎች በትምሕርት ካነጿቸው በኋላ ነው።

ጃንሆይን በአንድ ወቅት ታዋቂው ጋዜጠኛ አሳምነው ገብረ ወልድ ቃለ መጠይቅ ሲያደርግላቸው ማኪያቬሊን የሚያደንቁት እንደኾነ መግለጻቸው ይታወሳል። ማኪያቬሊ ደግሞ ለመሪዎች ከሰጣቸው ምክር አንዱ "ሃይማኖተኛ ምሰል" የሚል ነው። ስለኾነም መሪዎች ዋንኛው ሃይማኖታቸው ሥልጣናቸው መሆኑን ሳንዘነጋ በኢትዮጵያ ታሪክ ግን ብዙዎቹ ንጉሦች የሃይማኖት ትምህርትን ይማሩ ስለነበረ፣ ዕምነታቸው ከመመሰጣቸው የተነሣ መጨረሻ ላይ ሥልጣናቸውን ለልጆቻቸው እየተው የመነኮሱ ነገሥታት ከአጼ ካሌብ ጀምሮ ብዙ እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል።

ይኸ እንዳለ ሆኖ ጃንሆይ በሥልጣን ላይ እንደወጡ በቤተ መንግሥቱ የፖለቲካ ንቅናቄ ስለነበረ ጠላትም ወዳጅም ማፍራት ስለጀመሩ

ጠላቶቻቸው ስማቸውን ለማጥፋት "ተፈሪ ካቶሊክ ነው" እያሉ መናገር አብዝተው ነበር። ይህንንም ያሉበት ምክንያት ተፈሪ በካቶሊክ አስተማሪዎች ይማሩ እንደነበረ ስለሚያውቁ ነው። ከዚህም በላይ ጃንሆይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሐዋርያው ጳውሎስን ትምሕርት መጥቀስ ያዘውትሩ ስለነበረ ነው።


ጃንሆይ ከአንድ ባህታዊ ጋር

ተፈሪ የዚህ ትርጉሙ ምን እንደኾነ የተገነዘቡ ስለ ነበሩ ለጠላቶቻቸው ዕድል ላለመስጠትና ኦርቶዶክስ መሆናቸውን ማንም እንዳይጠራጠር ለማድረግ በቤተ ክርስቲያን በዓላት ላይ አዘውትረው ይገኙ ጀመር። እንዲያውም ሥልጣን ሲይዙ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ የማሾሙን ጉዳይ ተከታትለው ዳር ስላደረሱት ሙሉ ተመስገኑበትና የተቃዋሚዎቻቸው ፕሮፓጋንዳ እንደተኮላሸ ቀረ።

እንግሊዝ አገር በስደት በነበሩበት ወቅትም ዳዊት ደጋሚያቸውን አባ ሃናኝና የንስሐ አባታቸውን እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስን አስከትለው ስለነበረ የሃይማኖቱን ነገር ችላ አላሉትም። እንዲያውም ከኢየሩሳሌም የመድኃኔ ዓለምን ታቦት አስመጥተው እንግሊዝ አገር በመኖሪያ ግቢያቸው ስዕል ቤት ውስጥ ጸሎት ይደረስ ነበር። ከስደት እንደተመለሱ ታቦቱን አስመጥተው ቤተ ክርስቲያን አሠርተውለታል። ይህ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ምስካዬ ሕዙናን ወይም ስደተኛው መድኃኔ ዓለም የሚባለው ከስድስት ኪሎ በስተሰሜን ተፈሪ መኮንን (እንጦጦ አጠቃላይ) ትምሕርት ቤት መግቢያ ላይ ያለው ነው።

ጃንሆይ ባለማቋረጥ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በየንግሥ በዓሉ ይገኙ ነበር። የሃይማኖት ሰዎችንም ያከብሩ ነበር በቤተ ክርስቲያን ከቅዳሴ በፊት ገብተው ከተቀመጡና ትንሽ ጸሎት ካደረሱ በኋላ ባለሥልጣኖቻቸውን እየጠሩ ስለመንግሥት ሥራ ይወያዩ። ከቀድሞዎች ንጉሦች የሚለዩት ታቦት ወጥቶ በቆመ ጊዜ እሳቸው ወንበር



ተደርጎላቸው መቀመጣቸው ነው። ከዚህም ልምድ በመነሳት ይመስላል በአሁኑ ወቅት ጳጳሶችም መቀመጥ ጀምረዋል።

በመጀመሪያ ኢትዮጵያ የእራሷን ተወላጅ ፓትርያርክ አድርጋ እንድትሾም ከእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ጋር ስምምነት ሲደረስ የመጀመሪያው ፓትርያርክ የንጉሠ ነገሥቱ የንስሐ አባት እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ግብጽ አገር ሄደው ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ተብለው ተሹመው መጡ። እሳቸውም በሞት ሲለዩ ምክትላቸው ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ተብለው በሲኖዶሱ ተሾሙ። አቡነ ቴዎፍሎስ የተማሩና ዘመናዊ ስለነበሩ ብዙዎች ካህናት እንዲሾሙ አለመፈለጋቸውንና እንዲሁም ጎጃሜ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ቅብዓት ናቸው ተዋህዶ አይደሉም እያሉ አስቸገሯቸው። እሳቸው ግን ይህን ሁኔታ ሲቃወሙ ራሳቸው ተዋህዶ መሆናቸውንና የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ኮፕት መባል እንደሌለበት በይፋ አስታውቀው ነበር። ተቃዋሚዎቻቸው ካህናት ሹመታቸውን ባይፈልጉም የጃንሆይ ግፊት በዘመኑ ቀላል ስላልነበረ አቡነ ቴዎፍሎስ መጨረሻ ላይ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ተቀበሉ። ምንም እንኳን የሃይማኖት መሪዎች አመራረጥ ላይ መንግሥት እጁን ማስገባት ባይኖርበትም የአገሪቱ መሪዎች የአብዛኛውን ሕዝብ የሃይማኖት መሪዎችን አሿሿም ችላ ብለው አያውቁም።


አቡነ ቴዎፍሎስ

ስለሆነም አቡነ ባስልዮስ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ መሆናቸው የታወቀ ስለሆነ የሹመታቸው መሠረቱ ይኸው መሆኑ በንግግራቸው ተንጸባርቋል። "እኔ አባ ባስልዮስ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሊቀ ጵጵስና ተመርጬ ጃንሆይ ሹመቱን ፈቅደውልኝ አሁን በግርማዊነትዎ ፊት ቀርቤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለግርማዊነትዎ አገልጋይ መሆኔን ስገልጥ በፊትዎ የታመንኩ አገልጋይ ነኝ። ሃይማኖትና ዕውነት ይመሰክሩልኛል" በማለት ጉዳዩን አደባባይ አወጡት።

አቡነ ቴዎፍሎስም ሹመታቸው ሲጸድቅ ጃንሆይ ዘንድ ቀርበ ብለው "መርጠው ስለሾሙኝ በጣም አመሰግናለሁ" ሲሉ የሰሙ ካህናት ለካስ በምርጫ አይደለም ያሸነፉት በማለት ከዚህ ዕለት ጀምረው ጥምድ አድርገው ያዟቸው።

የደርግ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ አቡነ ቴዎፍሎስ ደርግን ሳያማክሩ ስድስት ጳጳስ በመሾማቸውና የማይወዷቸው ካህናትም አሳልፈው ስለሰጧቸው በግፍ ለመገደል በቁ። ከሾሙዋቸው ስድስት ጳጳሶች መካከል አንዱ በዘመናችን ያሉት ፓትርያርክ አቡነ ጳወሎስ ናቸው፤ ነቡነ ቴዎፍሎስ የአቡነ ጳውሎስን ሁኔታ ተመልክተው "ፓትርያርክነቱንስ ትደርስበታለህ ሽክሙን አትችለውም እንጂ" ብለዋቸው ነበር ይባላል።

ከ350 ዓ.ም ጀምሮና እንዲሁም በተለይ ከግራኝ አሕመድ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ የነበሩት ንጉሦች ቤተ ክርስቲያን ማሠራት የታሪክ ግዴታቸው ስለነበረ ጃንሆይ ለምን ቤተ ክርስቲያን አሠሩ ማለት አስቸጋሪ ነው። በዚህም ተግባር ጃንሆይ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ብዙ ውለታ ውለዋል። በኮሌጅ ደረጃ የመንፈሳዊ ትምሕርት ቤት አሠርተዋል። ካህናቱ የጃንሆይንና የቅርብ ዘመን ንጉሦችን ስም በየአጋጣሚው ይዘክራሉ ለመዘከር ያልፈለጉት የአፄ ቴዎድሮስን ብቻ ሲሆን በአውሮፓ ያሉ የኦርቶዶክስ ካህናት በዚህ ጉዳይ ላይ በቅርቡ ተወያይተው የአፄ ቴዎድሮስንም ስም ለመጨምር አቋም ወስደዋል።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት የሃይማኖት ነፃነት የሰፈነ ስለነበረ ብዙ ዓይነት ሃይማኖቶች መሠረት መጣል ጀምረዋል ከነዚህም ዋንኛው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ሲሆን ጃንሆይ በስደት በነበሩበት ወቅት በእንግሊዝ አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጸሐፊ የነበሩት አቶ አማኑኤል አብርሃም የሚባሉ የፕሮቴስታንት ሚሲዮን ውስጥ የተማሩና እምነቱንም የተቀበሉ ሃይማኖት አጥባቂ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። በሥራቸውም ከመወደዳቸው የተነሳ ጃንሆይ አትኩረው ይመለከቷቸው ነበር። አንድ ጊዜ እንዲያውም በአንድ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ሥነ ሥርዓት ላይ ጃንሆይን ይዘዋቸው ሄደው ለምዕመናኑ ስለኢትዮጵያ የክርስትና ታሪክ ከተናገሩ በኋላ የንጉሡንም መኖር አስገንዝበውና አስተዋውቀው በክብር እንዲሸኙ አድርገዋቸዋል። ጃንሆይም አቶ አማኑኤል አብርሃምን "አኮራኸን" ብለው ካሞገሷቸው በኋላ አንድ ቀን



አንድ ትንሽ መጽሐፍ ቅዱስ ከኪሳቸው አውጥተው ለአቶ አማኑኤል አብርሃም ሸለሟቸው።

በአቶ አማኑኤል አብርሃም ጠያቂነትና አቅራቢነት ብዙ ርስትና ፈቃድ ለፕሮቴስታንት ሃይማኖት ጃንሆይ ሰጥተዋል በዚህ ስጦታ አንዳንድ ባለሥልጣኖች ደስተኛ አልነበሩም፤ እንዲያውም አቡነ ባስሊዮስ በነገሩ አለመደሰታቸውን ሰዎች ተችተውበታል የብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያም እንዲቋቋም በንጉሡ ነገሥቱ ልዩ ትእዛዝ ተፈቅዷል እሳቸውም አዘውትረው የሚያዳምጡት ጣቢያ እንደነበረ አልሸሸጉም። በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት በስተቀር መስበክ ሲከለከል በአፄ ዮሐንስ ዘመን ሚሲዮናውያኖች እንዲባረሩ ሲደረግ በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ግን በዚህ ረገድ ለውጥ ታይቷል። ለምሳሌ የአሜሪካው ታዋቂ የፕሮቴስታንት የወንጌል ሰባኪ ቢሊ ግርሃም አዲስ አበባ መጥቶ ስታዲዮም ውስጥ የዕምነቱ ተከታይ ያልነበረው ተማሪ ሁሉ በትእዛዝ ተሰብስቦለት እንዲሰብክ ተደረገ። ጃንሆይ በዘመናቸው ይፈሩና ይከበሩ ስለነበረ ቢሊ ግርሃም በዘመኑ ተከታይ እጅግም ሳይኖረው መንግሥት ተባብሮት ሲሰብክ የተቃወመ አልነበረም። ለሁለተኛም ጊዜም የካቲት 29 ቀን 1952 ዓ.ም ለስብከት ተመልሶ መጥቶ ጃንሆይ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት የሻይ ግብዣ ካደረጉለት በኋላ ከወርቅ የተሠራ የመታሰቢያ ስጦታ አድርገውለታል። በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በቅርቡ ቦንኬ የሚባል የጀርመን ሰባኪ ሲመጣ የኦርቶዶክስ ምዕመናን እንዳይሰብክ መከላከላቸው ይታወሳል።


የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን መስፋፋት ሁኔታ ሲመለከቱት የጃንሆይ የጎላ ዕርዳታና ከውጭ ከሚመጣው የገንዘብ ኃይል ጋር ለሃይማኖቱ መሠረት ጥሎለታል ለማለት ይቻላል። የሳቸውን ዘመነ መንግሥት አልፎ ሕዝቡ የመኖር ችግር ሲበረታበትና የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም አስተዳደሯንና ሰባኪዎቿን ዘመናዊ ማድረግ ሲሳናት ያየው በተለይ ወጣቱ ትውልድ ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት መቀየር ጀመረ። በደርግ ዘመነ መንግሥት ደግሞ የመኖር ውጥረት የበረታበት ወቅት ስለነበረ አንዳንድ ሰዎች ይህን ሃይማኖት ለሕይወት ማትረፊያነት የተጠቀሙበት መስሏቸው ነበረ በማለት ሲተቹ "ለብዙ ሰዎች መደበቂያነት አገልግሏል" ይላሉ። ይህንንም ያሉበት ምክንያት በደርግ ዘመነ መንግሥት "እኔ ክርስቲያን ነኝ አልዘምትም፣ ፓለቲካም ውስጥ አልገባም ወዘተ.." የሚሉ ሰዎች ስለነበሩ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ጥንት የጀስዊትስ ሰባኪያን ኢትዮጵያን በሃይማኖት ሲያምሱ ኖረው መጨረሻ ላይ ከተባረሩ ከብዙ ዘመን በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል። እንዲያውም ራሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱ የተማሩት በካቶሊክ ፍሬሮች ስለነበረ እንደልብ በየቦታው ሚሲዮናቸውን ለማስፋፋት ዕድሉ አልተነፈጋቸውም። እነዚህ የጀስዊትስ ሰባኪያን መንግሥቱን የካቶሊክ ሃይማኖት እንዲቀበል ለማድረግ ባደረጉት ጥረት ንጉሥ ሱስንዮስን መለወጥ ችለው ነበር። ስለሆነም ለስምንት ዓመት በዚህ ሽኩቻ የሕዝብ እልቂት ተካሄዷል። መጨረሻ ላይ ሲባረሩ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ለሁለት ከፍለው አንዱን የፀጋ ልጆች ሌላውን ቅባት ብለው አስተምረውና ኢትዮጵያ ውስጥ መርዝ ተክለን ብለው ፎክረው ከሄዱ በኋላ በዚሁ ምክንያት የኦርቶዶክስ ተከታዮች ሲቸገሩበትና ሲጋደሉበት ኖረዋል።

ከክርስትና ሃይማኖት ውጭ በጃንሆይ ዘመን መንግሥት መሠረት የጣለ ሃይማኖት ባሃይ ነው፥ በሃይ ሃይማኖት ከእስልምና ሃይማኖት የፈለቀ፣ ከመቶ ሰማንያ ዓመት በፊት የተፈጠረ ሳይንስን ያገናዘበና ለምሁር ቶሎ የሚመስጥ ሃይማኖት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተዋወቀው በተግባረ ዕድ ትምሕርት ቤት አስተማሪ የነበረው ፓኪስታናዊ ሚስተር ሙናጅም ነው። ስለሆነም ብዙ የተማሩ አማኞች ለማግኘት ችሏል።

በሌላ በኩል ወደ 35 % አካባቢ አማኝ ያለው የእስልምና ሃይማኖት የሚገባውን ድጋፍ ከንጉሠ ነገሥቱ ሳላገኘም የሕዝቡ በትምሕርት አለመግፋት ለጃንሆይ በሃይማኖት በኩል የተስተካከለ አስተዳደር ለመፈጸም አዳግቷቸዋል። ስለኾነም "ልጅ ኢያሱን ዓይተህ ተቀጣ" ከሚለው የተማሩ ይመስል በዚህ ጉዳይ የተቆጠቡ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፳፱

# ያለፉትን ማስታወስ

መንግሥት ተለውጦ በሌላ ሲተካ ተተኪው ከበፊቱ መንግሥት የከፋ ከሆነበት ሕዝቡ ያለፈውን መንግሥት ግፉም እንደ ነበረ አድርጎ ያቀርበዋል። ደርግ የበለጠ ጨቋኝ ነው ለማለት ተማሪ "ኃይልዬ ማረኝ! ማረኝ!" እያለ ዘምሯል። ይኽ ማለት ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጥሩ ነው ለማለት አልነበረም። ሁለቱን ሲያወዳድር ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይሻል ነበር ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን የሚይዘው መንግሥት መልካም ነገሮችን መሥራት ሲያቅተው ያለፉትን መውቀስና በእነሱም ላይ ድክመትን ማላከክ እንደ ልማድ ሆኗል። ይኽ የጎላው በደርግ ዘመነ መንግሥት ነው። ደርግ ያለፈውን መንግሥት የተሻለ ሁኔታ ሕዝቡ እንዳይገነዘብ ሥነ ልቦናውን ለመቀየር ብዙ ጥሮ ተሳክቶለትም ነበር። በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት የነበረው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው። ጃንሆይን ታላቅ መሪ ለማስመሰል ያለፉትን ባለታሪኮች መዘንጋት ሲሆን በዚያው መጠን የአገር ውስጥ ባለታሪኮችን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር መሪዎችንም ማጋነን በተዘዋዋሪ መንገድ የተከለከለ ነበር።